# ኢትዮጵያ፡-የ2014 የሰብዓዊ መብት ሪፖርት

## አጭር ማጠቃለያ

ኢትዮጵያ በፌዴራላዊ ሥርዓት የምትመራ አገር ነች። ብሔርን መሠረት ባደረጉ አራት ፓርቲዎች የተዋቀረው የኢትዮጵያ ሕዝቦች አብዮታዊ ዴሞክራሲያዊ ግንባር (ኢሕአዴግ) የመንግሥትን ስልጣን ተረክቦ ያስተዳድራል። የቀድሞው ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊን ህልፈት ተከትሎ በመስከረም 2005 ዓ.ም. የተወካዮች ምክር ቤት ኃይለማርያም ደሳለኝን በጠቅላይ ሚኒስትርነት መረጠ። በ2002 ዓ.ም. በተካሄደው አገር አቀፍ የፓርላማ ምርጫ፣ ኢሕአዴግ እና አጋር ድርጅቶች ካሉት 547 የፓርላማ መቀመጫዎች 545ቱን በማሸነፍ በተከታታይ ለአራተኛ የአምስት ዓመት የሥራ ዘመን በሥልጣን ላይ ለመቆየት ችለዋል። ምንም እንኳ ምርጫዎቹን እንዲታዘቡ የተፈቀደላቸው (አንጻራዊ በሆነ አነጋገር) በቁጥር አነስተኛ የሆኑ ዓለም አቀፍ ታዛቢዎች የድምፅ አሰጣጡ ቴክኒካዊ ገጽታዎች በብቃት ተከናውነዋል ብለው ቢደመድሙም፣ አንዳንዶች ደግሞ ከምርጫው አስቀድሞ ለነጻ እና ፍትኃዊ ምርጫ የተመቻቸ ሁኔታ እንዳልነበረ ጠቅሰዋል። በአጠቃላይ የጸጥታ ኃይሎች ተጠሪነት ለሲቪል ባለስልጣናት ቢሆንም፤ በሶማሌ ክልል ልዩ ፖሊስ እና የአካባቢ ሚሊሻዎች አልፎ አልፎ በራሳቸው ሲንቀሳቀሱ ታይተዋል።

ሃሳብን በነጻነት የመግለጽ  እና የመደራጀት መብት ላይ የተደረጉ ክልከላዎች እና በሕትመት ሚዲያው ላይ መደረግ የቀጠሉ እገዳዎች በጣም ጎልተው የታዩ የሰብዓዊ መብት ችግሮች ሲሆኑ፤ በተቃዋሚ የፖለቲካ ፓርቲ አባላት እና ጋዜጠኞች ላይ ፖለቲካዊ ይዘት ያላቸውን ክሶችና የፍርድ ውሳኔዎች ማሳለፍ፣ እስር፣ ይዞ ማቆየት፣ ማዋከብ እና ማስፈራራት ተስተውሏል። መንግሥት በበጎ አድራጎት ድርጅቶች እና ማሕበራት አዋጅ አማካኝነት በሲቪክ ማህበራት እና መንግስታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች እንቅስቃሴዎች ላይ የጣለው እገዳ እንደቀጠለ ነው።

ሌሎች የሰብዓዊ መብት ችግሮች፤ የጸጥታ ኃይሎች በእስረኞች ላይ ፈፅመዋቸዋል የተባሉ የዘፈቀደ ግድያዎች፣ ማሰቃየት ፣ ድብደባ፣ ማዋከብ እንዲሁም እጅግ የከፋ አንዳንዴም ለሕይወት አስጊ የሆነ የማረሚያ ቤት ሁኔታ፣በዘፈቀደ በቁጥጥር ሥር ማዋል እና ማሰር፤ ያለ ክስ ማሰር እና ከፍርድ ሒደት በፊት ለተራዘመ ጊዜ አስሮ ማቆየት፤ ደካማ፣ የተጨናነቀ እና

በፖለቲካ ተጽዕኖ ስር የወደቀ ፍርድ ቤት፣ ሕገ-ወጥ ፍተሻን ጨምሮ የዜጎችን ግላዊ መብቶች መጣስ፣በመንግሥት የሰፈራ መርሃግብር አፈጻጸም ወቅት ተፈጸሙ የተባሉ የመብት ጥሰቶች፣ በአካዳሚያዊ ነጻነት ላይ የተደረጉ ክልከላዎች፤ በመሰብሰብ በመደራጀት እና ከቦታ ቦታ በመንቀሳቀስ ነጻነት ላይ የተጣሉ ገደቦች፣ በሃይማኖታዊ ጉዳዮች ጣልቃ የመግባት ሁኔታዎች፤ ዜጎች መንግስታቸውን መቀየር የሚችሉበትን አቅም መገደብ፤ በፖሊስ፣ በአስተዳደር ኃላፊዎች እና በፍርድ ቤቶች የሚፈጸም ሙስና፤ አመጽ እና በሴቶች ላይ የሚደርስ ማህበራዊ መድልኦ እንዲሁም የሕጻናት መብት ጥሰት፤ የሴት ልጅ ግርዛት፤ ሕገወጥ የሰዎች ዝውውር፤ በአካል ጉዳተኞች ላይ የሚደርስ ማህበራዊ መገለል፤ አነስተኛ የሕዝብ ብዛት ባላቸው ጎሳዎች መካከል የተነሱ ግጭቶች፤ ባላቸው ወሲባዊ ዝንባሌ የተነሳ እና ኤች አይ ቪ/ ኤድስ በደማቸው የሚገኝ ሰዎችን ማግለል፤ በሰራተኛ መብቶች ላይ የተጣሉ ገደቦች፣ የግዳጅ ስራ፣ እንዲሁም ሕፃናትን በግዳጅ ማሠራትን ጨምሮ የሕፃናት ጉልበት ብዝበዛን ያካትታሉ።

አጥፊዎችን ሕግ ፊት ያለማቅረብ ችግር ነበር። በአንዳንድ አጋጣሚዎች ካልሆነ በስተቀር፣ መንግሥት ከሙስና ውጪ ጥፋት የፈጸሙ ባለስልጣናት ላይ ክስ የመመስረትም ሆነ የቅጣት እርምጃ አልወሰደም።

በሶማሌ ክልል በሚንቀሳቀሰውና በተከፋፈለው አማጺ ተገንጣይ ብሔር ተኮር ቡድን ማለትም የኦጋዴን ብሔራዊ ነጻነት ግንባር (ኦብነግ) አንጃዎች የመብት ጥሰቶች ተፈጽመዋል።

## ክፍል አንድ - የሰው ልጅን ክብር መጠበቅ፣ ከሚከተሉት ነጻ የመሆን መብቶችን ጨምሮ፣

### ሀ. በዘፈቀደ ወይም ከሕግ ውጪ ሕይወትን ማጥፋት

የጸጥታ ኃይሎች ግድያዎችን እንደፈጸሙ ተነግሯል።

ሚያዝያ 22 ቀን፣በአዲስ አበባ በስተ ምዕራብ በሚገኘው የአምቦ ከተማ ሰልፍ የወጡ ሰላማዊ ተማሪዎች ላይ በተወሰደው የኃይል እርምጃ ቢያንስ የስምንት ሰዎች ሕይወት ሊያልፍ ችሏል። ሂዩማን ራይትስ ዋች በሪፖርቱ እማኞችን ጠቅሶ እንዳመለከተው የፀጥታ ኃይሎች ሰላማዊ ሰልፈኞች ላይ ተኩስ ከፍተዋል።

በነሐሴ ወር የኢድ አልፈጥር በዓል በተከበረበት ወቅት በቁጥጥር ሥር የዋሉ ግለሰቦች በእስር ላይ ሳሉ ሕይወታቸው እንዳለፈ ተዓማኒ መረጃ ቢኖርም፤ ከጉዳዩ ጋር በተያያዘ ተጨማሪ መረጃ ማግኘት አልተቻለም።

በመንግሥት ኃይሎች (በዋነኝነትም በክልል መንግስታት በሚደገፉ ሚሊሻዎች) እና በርዝራዥ የኦብነግ ኃይሎች መካከል በተበታተነ መልኩ የሚደረጉ ውጊያዎች ቀጥለዋል። በጎሳ ቡድኖች መካከል የተነሱ ግጭቶች የአካል ጉዳት እና ሞት አስከትለዋል።

በጥቅምት 3 ቀን 2007 ዓ.ም. በደቡብ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልላዊ መንግሥት (ደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/መ) መሣሪያ የታጠቁ አካላት ከ40 የሚበልጡ የመንግሥት የፀጥታ ኃይሎችን እንደገደሉ በጋምቤላ ከተማ የሚገኙ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችና መገናኛ ብዙሃን ዘግበዋል። ዘገባዎቹ እንዳመለከቱት ግጭቱ የተከሰተው በኢትዮጵያ የፌዴራልና የክልል የፀጥታ ኃይሎችና በመዠንግር ብሔረሰብ አባላት መካከል ነበር።

### ለ. የሰዎች መሰወር

ከዚህ ቀደም ከነበሩት ዓመታት በተለየ መልኩ በዚህ ዓመት በጸጥታ ኃይሎች እና አማጺ ቡድኖች መካከል የተነሱ ግጭቶችን ተከትሎ የሰላማዊ ዜጎች መሰወርን የሚገልጹ ሪፖርቶች እምብዛም አልነበሩም።

በጥር ወር 2005 ዓ.ም. መንግሥት በሕገወጥ መንገድ የተገነቡ ቤቶችን ለማፍረስ ያወጣውን ዕቅድ ተቃውመው ሰልፍ መውጣታቸውን ተከትሎ በትግራይ ክልል ሰሜናዊ ክፍል የአላማጣ ከተማ ነዋሪ የሆኑ 12 ግለሰቦች በጸጥታ ኃይሎች ታስረዋል። እስከ ዓመቱ መጨረሻ ድረስ ታሳሪዎቹ የት እንዳሉ አልታወቀም።

## ሐ. ማሰቃየት እና ሌላ ጭካኔ የተሞላበት፣ ኢ-ሰብአዊ፣ ወይም ሰብአዊ ክብርን የሚያዋርድ አያያዝ ወይም ቅጣት

ሕገ-መንግሥቱ እና ሕጉ እንዲህ ያሉ ተግባራትን (ማሰቃየትን እና ማንገላታትን) የሚከለክሉ ቢሆንም፤ የጸጥታ ኃይሎች በእስር ላይ ያሉ ሰዎችን እንዳሰቃዩ አልያም በደል እንዳደረሱባቸው ሪፖርቶች አመልክተዋል።

በሚያዝያ ወር ሁለት የዞን 9 ጦማርያን/ጋዜጠኞች የመንግሥት የፀጥታ ኃይሎች ድብደባ አድርሰውብናል፤አግባብነት በሌለው መልኩ ተይዘናል ሲሉ ከሰዋል። አንደኛው ጋዜጠኛ ፖሊስ ፊቱ ላይ እንደመታው የገለፀ ሲሆን፤ ሁለተኛው ውስጥ እግሩ ላይ ድብደባ እንደተፈፀመበት ተናግሯል (ክፍል 2፣ሀን ይመልከቱ)። ፌደራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በየጊዜው የማረሚያ ቤቱን የሥራ ኃላፊዎች ማብራሪያ እንዲሰጡበት ሲጠይቅ ቆይቷል።

አዲስ አበባ በሚገኘው ማዕከላዊ የፖሊስ ወንጀል ምርምራ ዋና መሥሪያ ቤት፣ መርማሪ ፖሊሶች [በቁጥጥር ሥር የዋሉ እስረኞች] ጥፋተኝነትን እንዲያምኑ ለማድረግ አዘውትረው ድብደባን እንደሚፈጽሙ ከተለያዩ ምንጮች የተገኙ ዘገባዎች ያመለክታሉ። ሂውማን ራይትስ ዎች በማዕከላዊ ማሰቃየትን ጨምሮ ጥሰቶች እንደተፈጸሙ ሪፖርት አድርጓል። ድርጅቱ በጥቅምት ወር ባወጣው ሪፖርት በዚሁ ማዕከል ድብደባዎች፣ አስጨናቂ አያያዞች ማለትም የታሳሪዎችን እጅ ከኮርኒስ ጋር አስሮ ማንጠልጠል፣ ለረዥም ጊዜ በካቴና አስሮ ማቆየት፣ ታሳሪዎች ላይ ውሃ ማፍሰስ፣ የቃል ማስፈራሪያዎች እና ለብቻ ማሰር እንደሚፈጸሙ ገልጧል። ባለሥልጣናት የዲፕሎማቲክ ማኅበረሰብ አባላት እና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች የማዕከላዊ ወንጀል ምርመራ ቢሮን እንዳይጎበኙ መከልከላቸውን ቀጥለዋል።

የተባበሩት መንግሥታት የፀረ-ማሰቃየት ኮሚቴ (UN Committee Against Torture) በ2003 ዓ.ም. ባወጣው ሪፖርት፣ በፖሊስ፣ በማረሚያ ቤት ኃላፊዎች እና መከላከያ ሠራዊቱን ጨምሮ

በሌሎች የፀጥታ ኃይል አባላት፣ የፖለቲካ አመለካከት ልዩነት ባላቸው ግለሰቦች እና በተቃዋሚ ፓርቲ አባላት፣ በተማሪዎች፣ በሽብር ተጠርጣሪዎች፣ እንዲሁም እንደ ኦብነግ እና ኦነግን የመሰሉ ነውጠኛ ተገንጣይ ቡድኖችን ይደግፋሉ ተብለው በሚጠረጠሩ ሰዎች ላይ "የማሰቃየት ዘዴን አዘውትሮ መጠቀምን" አስመልክቶ የሚደርሱት "በርካታ እና ተደጋጋሚ አቤቱታዎች" "እጅግ የሚያሳስቡት" መሆኑን ገልጿል። ኮሚቴው በሪፖርቱ፣ እንዲህ ያሉ ተግባራት ብዙዉን ጊዜ በፖሊስ ጣቢያዎች፣ በማቆያ ማዕከላት፣ በፌደራል ወህኒ ቤቶች፣ በወታደራዊ ሠፈሮች፣ እና በይፋ በማይታወቁ ወይም በምስጢራዊ የማቆያ ስፍራዎች በሹመኞች እና በእነርሱ አነሳሽነት፣ አልያም በእነርሱ ይሁንታ እንደሚፈፀሙ ሪፖርት አድርጓል። ተመሳሳይ የመብት ጥሰቶች በዓመቱ ውስጥ ከ2003 ዓ.ም. ጀምሮ ኢትዮጵያ እንዳይገባ የተከለከለው አምነስቲ ኢንተርናሽናል በኬንያ፣ በዩጋንዳ እና በሱማሌላንድ ያሉ የኦሮሞ ብሔር ተወላጅ የሆኑ ስደተኞችን አነጋግሮ ባገኘው መረጃ ላይ ተመርኩዞ ባቀረበው ሪፖርት መንግሥት በአሸባሪነት የከሰሳቸውን በሺዎች የሚቆጠሩ የብሔሩን ተወላጆች በዘፈቀደ እንደሚያስር እና አንዳንዴም የማሰቃየት ቅጣት እንደሚፈጽምባቸው አመልክቷል።

## የማረሚያ ቤቶች እና የማቆያ ማዕከላት ሁኔታ

ማረሚያ ቤቶች እና የቅድመ-ክስ ሒደት ማቆያ ማዕከላት ይዞታ በአስከፊ ደረጃ ላይ የሚገኝ እና በአንዳንድ ሁኔታዎችም ለሕይወት አስጊ እንደሆነ ነው። ባለስልጣናት በእስረኞች ላይ ድብደባ እንደሚፈጽሙ የሚገልጹ በርካታ ሪፖርቶችም ቀርበዋል። በአንዳንድ ሁኔታዎች ድብደባውን ተከትሎ እስረኞች በቂ የሕክምና ክትትል አይደረግላቸውም።

<u>**አካላዊ ይዞታ፡-**</u> በ2004 ዓ.ም. 111,640 ሰዎች በእስር ቤቶች የሚገኙ ሲሆን፤ ከእነዚህም 2,500 ሚሆኑት ሴቶች፤ 600 ደግሞ ከእናቶቻቸው ጋር የታሰሩ ሕጻናት ይገኙበታል። ወጣት አጥፊዎች አልፎ አልፎ ከአዋቂዎች ጋር የሚታሰሩ ሲሆን፣ ጨቅላ ሕጻናትም እንዲሁ ከእናቶቻቸው ጋር ታስረዋል። በአጠቃላይ ወንድ እና ሴት ታራሚዎች የተለያየ ቦታ ይታሰራሉ።

በማረሚያ ቤቶች በተለይ በመኻታ ቦታዎች አስከፊ የሆነ መጨናነቅ ማየት የተለመደ ነው፡፡ መንግሥት ለአንድ እሥረኛ ለምግብ፣ ለውሃ እና ለጤና እንክብካቤ በቀን ዘጠኝ ብር ገደማ መድቧል፡፡ የገንዘቡ መጠን ከቦታ ቦታ ልዩነት ልዩነት ነበረው፡፡ ብዙ እስረኞች ይህን ከመንግሥት የተመደበላቸውን ገንዘብ የቤተሰብ አባላት በሚያቀብሏቸው የዕለት ምግብ ወይም በአካባቢው ካሉ ሻጮች በሚገዙት ምግብ ይደጉማሉ፡፡ ይህም ሆኖ የማረሚያ ቤት ኃላፊዎች አንዳንድ እስረኞች ቤተሰቦቻቸው ምግብ እንዳይቀርብላቸው እንደከለከሉ ተጠቁሟል፡፡በፌደራል ማረሚያ ቤቶች የሚሰጠው የህክምና አገልግሎት አስተማማኝ አይደለም፡፡ በክልል ማረሚያ ቤቶች የሕክምና አገልግሎት የለም በሚባል ደረጃ ላይ ይገኛል፡፡ እንደአብዛኛው የአገሪቱ ዜጋ ሁሉ እስረኞችም የመጠጥ ውሃ የማግኘት ችግር አለባቸው፡፡ የውሃ እጥረት ለንጽህና መጓደል መንስዔ ሆኗል፤ አብዛኛዎቹ ማረሚያ ቤቶችም  የመፀዳጃ ቦታ ችግር አለባቸው፡፡ ብዙ እስረኞች በማቆያ ሥፍራ ሳሉ ከባድ የጤና ችግሮች ቢያጋጥሟቸውም፣ የሚያገኙት ህክምና በቂ አልነበረም፡፡ የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር በ2004 ዓ.ም. ያወጣው መረጃ እንደሚያመለክተው በአገሪቱ በተለያዩ እስር ቤቶች ከሚገኙ እስረኞች 62 በመቶ የሚሆኑት የአእምሮ ጤና መታወክ የገጠማቸው ሲሆን፤ ለብቻ መታሰር፣ የእስር ቤቶች መጨናነቅ እና በቂ የጤና ክብካቤ አለማግኘት በምክንያትነት ተጠቅሰዋል፡፡

አገሪቱ ስድስት የፌደራል እና 120 የክልል ማረሚያ ቤቶች ነበሯት፡፡ አንድ ሀገር በቀል መንግሥታዊ ያልሆነ ድርጅት ከሌሎች እስር ቤቶች በእጅጉ የሚሻሉ ሞዴል እስር ቤቶችን በአዳማ እና መቀሌ ከተሞች አቋቁሞ አስረክቧል፡፡ ዴዴሳ፣ ብር ሸለቆ፣ ጦላይ፣ ሆርማት፣ ብላቴ፣ ታጠቅ፣ ጂጂጋ፣ ሆለታ እና ሰንቀሌ የሚገኙትን ጨምሮ በመላ አገሪቱ በርካታ ይፋዊ ያልሆኑ የማቆያ ማዕከላት አሉ፡፡ አብዛኛዎቹ የሚገኙት በወታደራዊ ሰፈሮች ነው፡፡

ክስ ከመመስረቱ በፊት ተጠርጣሪዎች ፖሊስ ጣቢያዎች ውስጥ በሚገኙ ማቆያ ቤቶች የሚታሰሩ ሲሆን፤ በነዚህ ማቆያ ማዕከላት ያለው አያያዝም ከቦታ ቦታ ይለያያል፡፡ በፖሊስ ጣቢያዎች  የቅድመ ክስ እስር ሂደትን በተመለከተ የወጡ ሪፖርቶች  በማቆያ ቤቶቹ የንጽሕና መጓደል፣ እንዲሁም ፖሊስ በእስር ላይ ባሉ ሰዎች ላይ ድብደባ እንደሚፈጽም ያመለክታሉ፡፡

<u>አስተዳደር</u>፡- ግልጽ አሰራር ባለመኖሩ እስርን የሚመለከት መዝገብ በበቂ ሁኔታ ተይዟል ለማለት ያስቸግራል፡፡ ኃላፊዎች አመጽ የሌለበት ወንጀል ለፈጸሙ ጥፋተኞች አማራጭ

የቅጣት ዘዴዎችን አልዘረጉም። በእስር ቤቶች ለሚነሱ ቅሬታዎች ምላሽ የሚሰጡ የዕንባ ጠባቂ ባለሙያዎች አልነበሩም። በአንዳንድ እስር ቤቶች ለእስረኞች አገልግሎት የሚሰጡ የሕግ ድጋፍ ማዕከላት ነበሩ። ኃላፊዎች የታሳሪዎችን አቤቱታዎች ሳንሱር ሳያደርጉ ለፍርድ ቤቶች እንዲያቀርቡ ፈቅደዋል። ፍርድ ቤቶች አንዳንዴ እንዲህ ዓይነት አቤቱታዎችን ሳይቀበሉ ቀርተዋል። በአንዳንድ አጋጣሚዎች የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብት ኮሚሽን እና የፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽን የመብት ጥሰት አቤቱታዎችን የመረመሩ ቢሆንም፤ ከእስረኞች ጋር ያደረጓቸው ውይይቶች ብቻ ለብቻ ወይም በግል ስላልተካሄዱ የእስረኞቹን በነጻነት የመናገር ዕድል ውስን ሊያደርገው እንደሚችል ተነግሯል።

የታሳሪዎች የመጎብኘት መብት በህግ የተደነገገ ቢሆንም፣ ፖሊስ በተለይ በቅድመ ክስ እስር የተያዙትን በዘመድ ወዳጅም ሆነ በህግ አማካሪዎች እንዳይጎበኙ ያደርጋል። ለምሳሌ ያህል የአረና ትግራይ መሪ የሆነውና ከሐምሌ ወር ጀምሮ በእስር ላይ የሚገኘው አብርሃ ደስታ ጠበቃ ደንበኛውን በ28 ቀን አንዴ ብቻ እንዲያገኘው ተደርጓል። ሆኖም አንዳንድ ፖሊስ ጣቢያዎች ክስ ያልተመሰረተባቸው ታሳሪዎች ቤተሰብና የሕግ አማካሪን ጨምሮ በማንም እንዳይጠየቁ ከልክለዋል። በአንዳንድ ሁኔታዎች ቤተሰቦች እስረኞችን መጠየቅ የሚችሉበት ጊዜ በዓመት ውስጥ ለጥቂት ጊዜ እንዲሆን ተደርጎ ነበር። በሽብር ተግባር የተከሰሱ እስረኞች ቤተሰቦች ታሳሪዎችን እንዳያገኙ የተከለከሉባቸውን አጋጣሚዎች የጠቀሱ ሲሆን፤በሽብርተኝነት የተከሰሱም እንዲሁ ከጠበቆቻቸው ወይም ከፓርቲዎቻቸው ተወካዮች ጋር እንዳይገናኙ መደረጋቸው ሪፖርት ተደርጓል። የማረሚያ ቤት ኃላፊዎች ጋዜጠኛ ርዕዮት ዓለሙን እንዲጠይቁ የተፈቀደላቸው ግለሰቦች ቁጥር ውስን እንዲሆን አድርገዋል።

በአጠቃላይ እስረኞች እምነታቸውን በነፃነት እንዲያራምዱ ቢፈቀድላቸውም፣ እንደ ማረሚያ ቤቱ አስተዳደር ውሳኔ ሁኔታው ከማረሚያ ቤት ማረሚያ ቤት አንዳንዴም በአንድ ማረሚያ ቤት ውስጥ ባሉ ክፍሎች መካከል ይለያያል። እስረኞች በማረሚያ ቤት ውስጥ ተገቢ የፀሎት ስፍራ እንደተከለከሉ የተናገሩባቸው አጋጣሚዎች ነበሩ። እስረኞች ፣ ፍርድ ቤት በሚቀርቡበት ጊዜ፣ ስለ እስር ቤቱ ሁኔታ ወይም ስለ አያያዛቸው ክሱን ለሚሰማው ዳኛ አቤቱታ እንዲያቀርቡ ተፈቅዶላቸዋል።

<u>የገለልተኛ አካል ክትትል</u>፡- በዓመቱ ዓለም አቀፍ የቀይ መስቀል ኮሚቴ በሀገሪቷ ውስጥ የሚገኙትን ማረሚያ ቤቶች ጎብኝቷል። መንግሥት ዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብት ተሟጋች ድርጅቶች ማረሚያ ቤቶችን እንዳይጎበኙ አድርጓል።

የክልል ባለስልጣናት የመንግሥት እና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ተወካዮች ሶስተኛ ወገን በሌለበት አዘውትረው እስረኞችን እንዲጎበኙ ፈቅደዋል። የማረሚያ ቤቶች ኃላፊዎች የሲቪክ ማህበራት ተወካዮች የቤተሰብ አባላት ታራሚዎችን፤በተለይም ይፋ ባልሆኑ ሥፍራዎች የታሰሩትን እንዳያገኙ ማድረጋቸው ተነግሯል። መንግሥታዊ ድርጅት የሆነው፣ በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የገንዘብ ድጋፍ የሚተዳደረውና ምክር ቤቱ አሠራሩን የሚገመግመው የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብት ኮሚሽን የፌዴራል እና የክልል ማረሚያ ቤቶችን በመጎብኘት፤ በስፋት ይፈጸማሉ ስለሚባሉ የሰብዓዊ መብት ጥሰቶች የማረሚያ ቤቶች ኃላፊዎችንና እስረኞችን አነጋግሯል። አንድ አገር በቀል በጎ አድራጎት ድርጅት የተለያዩ ማረሚያ እና የማቆያ ማዕከላትን የመጎብኘት ፈቃድ ተሰጥቶታል።

<u>መሻሻሎች</u>፡- አንዳንድ የመንግሥት እና የማረሚያ ቤት አስተዳደር አካላት የበጎ-አድራጎት ድርጅቶች የማረሚያ ቤቶችን ሁኔታ ለማሻሻል ለሚያደርገው ጥረት ትብብር አድርገዋል። አንድ ድርጅት ያሠራው የሕግ ድጋፍ ማዕከል ግንባታ በ2005 ዓ.ም. መጠናቀቅን ተከትሎ፤ የእስረኞች አያያዝና የማረሚያ ቤት ሁኔታዎች እንደተሻሻሉ ሪፖርቶች ቢያመለክቱም ዝርዝር መረጃ ማግኘት አልተቻለም።

**መ. በዘፈቀደ በቁጥጥር ሥር ማዋል ወይም ማሰር**

ምንም እንኳ የአገሪቱ ሕገ-መንግሥት እና ሕጉ በዘፈቀደ በቁጥጥር ስር ማዋል እና ማሠርን ቢከለክሉም፣ መንግሥት ሕጎቹን በማስፈጸም ረገድ ተደጋጋሚ ቸልተኝነት ይታይበታል። በመላ አገሪቱ ፖሊስና የጸጥታ ኃይሎች ሰዎችን በዘፈቀደ በቁጥጥር ስር እንዳዋሉ እና እንዳሰሩ የሚጠቁሙ በርካታ ሪፖርቶች ቀርበዋል።

በሶማሌ ክልል የሚሰሩ ሲቪሎች፣ አለም አቀፍ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች እና የዕርዳታ ድርጅቶች የመንግሥት የጸጥታ ኃይሎች እና የአካባቢ ሚሊሻ አባላት የሰብዓዊ መብት ጥሰቶች እንደፈጸሙና ሰዎችን በዘፈቀደ እንዳሰሩ ሪፖርት አቅርበዋል።

## የፖሊስ እና የፀጥታ መዋቅር ሚና

የፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽን ተጠሪነቱ ለፌዴራል ጉዳዮች ሚኒስቴር ሲሆን፤ የሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱም ተጠሪነቱ ለፓርላማው ነው። የዚህ ተጠሪነት ተዋረድ የላላ ነው። የአገሪቱ ዘጠኝ ክልሎች እያንዳንዳቸው ለክልሉ ሲቪል ባለሥልጣናት (አስተዳደር) ተጠሪ የሆነ የክልል ወይም ልዩ የፖሊስ ኃይል አላቸው። በመላ አገሪቱ የሚገኙ የአካባቢ ሚሊሻዎች ከክልልና ከፌደራል ፖሊስ እንዲሁም ከአገሪቱ ሠራዊት ጋር ልል በሆነ ቅንጅት ይንቀሳቀሳሉ - የቅንጅታቸው ደረጃም እንደየክልሉ ይለያያል። በአመዛኙ እነኝህ ሚሊሻዎች የአካባቢው የኢሕአዴግ የፖለቲካ ሹማምንት ተቀጥላ ሆነው ይሠራሉ።

የፀጥታ ኃይሎች ሥራቸውን በብቃት ያከናውናሉ፤ ነገር ግን በሕግ ያለመጠየቅ አሳሳቢ ችግር ነበር። የተፈፀሙ የሕግ ጥሰቶችን ለማጣራት የፌዴራል ፖሊስ የሚጠቀምባቸው ስልቶች አይታወቁም። የሶማሌ ክልል ልዩ የፖሊስ ኃይል ግድያዎችን ጨምሮ የሰብዓዊ መብት ጥሰቶችን እንደፈጸመ የሚገልጹ በርካታ አቤቱታዎች መቅረባቸውን ቀጥለዋል። መንግሥት በዘፈቀደ ማሰርን እና በሰላማዊ ሰዎች ላይ ድብደባ መፈፀምን በመሳሰሉ በፀጥታ ኃይሎች የተፈፀሙ የመብት ጥሰቶች ላይ ያደረጋቸውን ምርመራዎች ውጤት በይፋ የሚገልጸው በጣም አልፎ አልፎ ነው።

መንግሥት ለፖሊስ እና ለመከላከያ ሠራዊት አባላት በሰብአዊ መብት ላይ ያተኮሩ ስልጠናዎች ለመስጠት የሚያደርገውን ጥረት ቀጥሏል። የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብት ኮሚሽን ብሔራዊ የሰብዓዊ መብቶች የድርጊት መርሀ ግብር እንደሚያመለክተው ከ2005-2006 ዓ.ም. 1,622 ለሚሆኑ የፖሊስ መኮንኖች እና 577 የማረሚያ ቤቶች ኃላፊዎች መሠረታዊ የሰብዓዊ መብት ጽንሰ ሃሳቦች እና የታራሚ አያያዝ ላይ ያተኮረ ሥልጠና ሰጥቷል። መንግሥት በሕገ-መንግሥቱ እንዲሁም በዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብቶች ሕግጋት እና ስምምነቶች ዙሪያ

ተጨማሪ ትምህርቶችን በማካተት በሰብአዊ መብት ላይ የሚሰጠውን ሥልጠና እና ሥርዓተ-ትምህርት ለማሻሻልና በበቂ ባለሙያዎች እንዲሰጥ ለሚያደርገው ጥረት ከአንዳንድ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችና እና ከኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብት ኮሚሽን የሚደረጉ ድጋፎችን መቀበል ቀጥሏል።

**በቁጥጥር ሥር የማዋል ሥነ ሥርዓት እና በእስር ላይ ስላሉ ሰዎች አያያዝ**

ምንም እንኳ ሕገ-መንግሥቱ እና ሕጉ በቁጥጥር ሥር የዋሉ ሰዎች በ48 ሰዓታት ውስጥ ፍርድ ቤት ሊቀርቡና ክስ ሊመሠረትባቸው እንደሚገባ ቢደነግጉም፤ኃላፊዎች ይህን ድንጋጌ ሁልጊዜ ተግባር ላይ አያውሉም። ከበድ ያለ ጥፋት በመፈፀም የተጠረጠሩ ሰዎች የፍርድ ቤት ይሁንታ ሲገኝ ክስ ሳይመሠረትባቸው ለ14 ቀናት፣ እንዲሁም የምርምራ ሒደቱ ካልተጠናቀቀ፣ ለተጨማሪ 14 ቀናት በእሥር ሊቆዩ ይችላሉ። በፀረ-ሽብርተኝነት ሕጉ መሠረት ፖሊስ ሰዎችን የ28 ቀናት ጊዜ ፍርድ ቤቱን እየጠየቀ እስከ አራት ወራት ክስ ሳይመሠርትባቸው ለማቆየት እና ምርመራ ሊያደርግ ይችላል። ሕጉ በይፋ ከሚታወቅ ማረሚያ ቤት ውጪ እስረኞች እንዳይታሰሩ ቢከለክልም፤ የአካባቢ ሚሊሻዎች እንዲሁም መደበኛ እና መደበኛ ያልሆኑ ሕግ አስከባሪ አካላት በይፋ የማይታወቁ በርካታ ቦታዎችን ለማሰሪያነት ተጠቅመዋል።

ህጉ የዋስ መብት ፈቅዷል። ነገር ግን በነፍስ ማጥፋት፣ በአገር ክህደት እና በሙስና ለተከሰሱ ሰዎች የዋስትና መብት ተፈጻሚ አይደለም። በአብዛኛው የመንግሥት አካላት ለዋስትና የሚጠይቁት የገንዘብ መጠን በ500 እና በ10,000 ብር መካከል ሲሆን፣ ይህም ከአብዛኞቹ ዜጎች የመክፈል አቅም በላይ ነው። በራሳቸው ወጪ የግል ጠበቃ ለመቅጠር አቅም ለሌላቸው እስረኞች መንግሥት ጠበቃ ያቆምላቸዋል፤ ይህ የሚሆነው ግን ጉዳያቸው ፍርድ ቤት ሲቀርብ ብቻ ነው። ባለስልጣናት ተጠርጣሪዎች በቅድመ ፍርድ ሂደት በእሥር ላይ ሳሉ፣ እጅግ ውሱን በሆነ ደረጃ ከሕግ አማካሪ ጋር እንዲገናኙ ፈቅደዋል ወይም ከነጭራሹ ከልክለዋል። ከዚህ ሌላ በተጠርጣሪዎች የጤንነት ሁኔታ ላይ ሙሉ መረጃ አልሰጡም፤ ቤተሰብም እንዲጠይቃቸው አለፈቀዱም።

<u>**በዘፈቀደ በቁጥጥር ሥር ማዋል**</u>፦ ባለሥልጣናት በተደጋጋሚ ያለ ፍርድ ቤት ማዘዣ ሰዎችን በቁጥጥር ሥር አውለዋል። ለምሳሌ፦የመንግሥት የፀጥታ ኃይሎች ሚያዝያ 22 በአዲስ አበባ የተቃዋሚ ፓርቲው የአንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትሕ ፓርቲ ሊቀመንበር የሆኑትን አቶ

ዘካርያስ የማነብርሃንንና የፓርቲው ልሳን የሆነው የፍኖተ ነፃነት ጋዜጠኛ ነቢዩ ኃይሉን ለድርጅታቸው የድጋፍ ሰልፍ ለማካሄድ ሲቀሰቅሱ፣ ከተፈቀደላችሁ ክልል ወጥታችኋል በሚል በቁጥጥር ሥር ካዋሏቸው በኋላ፣ ክስ ሳይመሰርቱ ግንቦት 4 ቀን ለቀዋቸዋል፡፡

**<u>ቅድመ-ክስ እሥር</u>**፡- አንዳንድ እሥረኞች ክስ ሳይመሠረትባቸው እና ፍርድ ቤትም ሳይቀርቡ ለበርካታ ዓመታት መታሠራቸውን ተናግረዋል፡፡ በቅድመ ክስ እስር ላይ ያሉ ታሳሪዎች ብዛት ወይም በእስር የቆዩበት አማካይ የጊዜ ርዝመት ምን ያህል እንደሆነ የሚገልጽ መረጃ አልተገኘም፡፡ በአብዛኛው የፍርድ ሂደት መጓተት የሚከሰተው በተራዘሙ የሕግ ሥነ-ሥርዓቶች፣ በታራሚዎች ብዛት፣ በፍትህ ሥርዓቱ የቅልጥፍና ማነስ ችግር እና በሰው ኃይል እጥረት ሳቢያ ነው፡፡

**<u>ምህረት</u>**፡- ለረዥም ዘመናት ሲወርድ ሲዋረድ በመጣው በኢትዮጵያ አዲስ ዓመት ለእስረኞች ምህረት የማድረግ ልማድ መሠረት የፌዴራል መንግሥት መስከረም 1 ቀን ለ995 እስረኞች ምህረት አድርጓል፡፡ የክልል መንግስታትም እንደዚሁ በዓመቱ ውስጥ ለእስረኞች ምህረት አድርገዋል፡፡ ለምሳሌ በ2005 ዓ.ም. የደ/ብ/ብ/ሕ/ክ መንግሥት ለ1,984 እስረኞች፤ የኦሮሚያ ክልላዊ መንግሥት ለ2,604 እስረኞች፤ እንዲሁም የአማራ ክልላዊ መንግሥት ለ2,084 እስረኞች ምህረት አድርገዋል፡፡

### ሠ. ፍትሃዊ የክስ ሂደት መነፈግ

ሕጉ ነጻ እና ገለልተኛ የዳኝነት ሥርዓት እንዲኖር ደንግጓል፡፡ ምንም እንኳ የፍትሀ ብሔር ፍርድ ቤቶች በተሻለ ነጻነት ቢንቀሳቀሱም፣ የወንጀል ፍርድ ቤቶች ግን ደካማ፣ ከአቅማቸው በላይ የሥራ ጫና ያለባቸው እና ለፖለቲካዊ ተጽዕኖ የተጋለጡ ናቸው፡፡ ሕገመንግስቱ ለሃይማኖታዊ እና ለባህላዊ ወይም ልማዳዊ ፍርድ ቤቶች እውቅና ይሰጣል፡፡

## የክስ ሂደት

በሕጉ መሠረት፣ የተከሰሱ ሰዎች ጉዳያቸው በፍርድ ቤት ግልጽ እና ፍትሃዊ በሆነ ሂደት የመዳኘት እና ተቀባይነት ባለው የጊዜ ገደብ ውስጥ ፍርድ የማግኘት፣ ጥፋተኝነታቸው እስካልተረጋገጠ ድረስ ንፁህ ተደርጎ የመታሰብ፣ በመረጡት የሕግ አማካሪ (ጠበቃ) የመወከል፣ እንዲሁም ይግባኝ የመጠየቅ መብት አላቸው፡፡ ሕጉ ለተከሳሾች በራስ ላይ ያለመመስከር መብት ከመስጠት በተጨማሪ የመከላከያ ምስክሮችን እና ማስረጃዎቻቸውን የማቅረብ፣ ለአቃቤ ሕግ ምስክሮች መስቀለኛ ጥያቄ የማቅረብ፣ እንዲሁም በመንግሥት እጅ የሚገኙ ማስረጃዎችን የማግኘት መብት ይሰጣል፡፡ ነገር ግን፣ መንግሥት በተግባር [የተከሳሾችን] መረጃ የማግኘት መብት ሁልጊዜ አያከብርም፡፡ የፍርድ ሥርዓቱ በ‹‹ጁሪ›› (ገለልተኛ የማኅበረሰብ ተወካዮች የፍርድ ሂደቱን ተከታትለው ተከሳሹ ጥፋተኛ ነው አይደለም የሚል ብይን የሚሰጡበት አሠራር) አይጠቀምም፡፡ የፍርድ ቤቶች የቅልጥፍና ጉድለት እና ብቃት ያለው የሰው ኃይል እጥረት አብዛኛውን ጊዜ የክስ ሂደቶች ከሚገባው በላይ እንዲጓተቱ እና የሕጉን አፈጻጸም በትክክል ለማወቅ አዳጋች እንዲሆን አድርጎታል፡፡ መንግሥት ለሥር ፍርድ ቤቶች ዳኞች እና ዐቃቤያነ ሕግ በዋነኝነት ውጤታማ በሆነ የፍትህ አስተዳደር ላይ ያተኮረ ሥልጠና መስጠቱን ቀጥሏል፡፡ አብዛኛውን ጊዜ ተከሳሾች ክስ የመስማት ሂደቱ እስኪጀመር ድረስ የቀረበባቸውን ክስ አለማወቃቸው ተከላካይ ጠበቆች ክሱን ለመከላከል በበቂ መልኩ እንዳይዘጋጁ ያደርጋቸዋል፡፡

ምንም እንኳ በጠበቆች እጥረት ምክንያት የአገልግሎት አድማሱ እና ጥራቱ ውሱን ቢሆንም፣ የተከላካይ ጠበቃዎች ጽ/ቤት ጠበቃ የመቅጠር አቅም ለሌላቸው ሰዎች በነጻ የሕግ ምክር አገልግሎት ሰጥቷል፡፡ በመላ አገሪቱ በዋነኝነትም በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ውስጥ የሚገኙ በርካታ ነጻ የሕግ ማማከር አገልግሎት የሚሰጡ ማዕከላት ለደንበኞች የሕግ ምክር ሰጥተዋል፡፡ የአንዳንድ ክልሎች ሕግ አውጪ አካላት እንደ ሕግ ተማሪዎች እና መምህራን ያሉ በጎ ፈቃደኞች ያለምንም ክፍያ ባለጉዳዮችን ወክለው ፍርድ ቤት እንዲቆሙ የሚፈቅዱ ሕግጋትን አውጥተዋል፡፡

ጥር 26 ቀን የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በሐምሌ 2004 ከተደረጉ የተቃውሞ ሰልፎች ጋር በተያያዘ ተከሰው የነበሩ 19 ሙስሊሞችን የክስ ሂደት ለሕዝብ ክፍት አድርጓል፡፡ የክስ ሂደቱ ቀደም ሲል የብሔራዊ ጸጥታና የምስክሮች ደህንነት ስጋቶችን በመጥቀስ ለሕዝብ ዝግ እንዲሆን ተደርጎ ነበር፡፡

በገጠር አካባቢዎች የሚኖሩ ብዙ ዜጎች በመደበኛ የዳኝነት ስርዓት የመዳኘት ዕድላቸው ውስን በመሆኑ ግጭቶችን የሚፈቱት በባህላዊ መንገድ ነው። በሕግ ረገድ በአንድ ጉዳይ ላይ የሚከራከሩ ወገኖች ጉዳያቸው በባህላዊ ወይም ሃይማኖታዊ ፍርድ ቤት መታየት ከመጀመሩ በፊት ተከራካሪዎቹ እንዲህ ባለው ፍርድ ቤት ለመዳኘት የግድ መስማማት አለባቸው፤ ከተከራካሪ ወገኖች ማናቸውም በማንኛውም ጊዜ ለመደበኛው ፍርድ ቤት ይግባኝ ማለት ይችላል። የሸሪዓ (እስላማዊ) ፍርድ ቤቶች ሙስሊሞችን የሚመለከቱ ሃይማኖታዊ እና ቤተሰባዊ ጉዳዮችን ሊዳኙ ይችላሉ። የሸሪዓ ፍርድ ቤቶች ከመንግሥት የተወሰነ የገንዘብ ድጋፍ የሚደረግላቸው ሲሆን፤ በአብዛኛው ሙስሊሞች በሚኖሩባቸው በሶማሌ እና በአፋር ክልሎች ለሚነሱ በርካታ ጉዳዮች ዳኝነት ሰጥተዋል። በተጨማሪም እንደ የአገር ሽማግሌዎች ሸንጎ ያሉ ሌሎች ባሕላዊ የፍትሕ ሥርዓቶች መስራታቸውን ቀጥለዋል። አንዳንድ ሴቶች በልማዱ መሠረት ሴቶች በሽማግሌዎች ሸንጎ ላይ ስለማይሳተፉ እና በገጠር አካባቢም ጠንካራ የሆነ የጾታ መድልዎ በመኖሩ በባህላዊው የፍትሕ ሥርዓት ነጻ እና ፍትሃዊ ዳኝነት የማግኘት ዕድላቸው አነስተኛ ነው የሚሉ ቅሬታዎች ይሰማሉ።

የሐሮማያ ዩኒቨርስቲ የፍትሕ ተደራሽነትና ንቃተ ሕግ የተሰኘ ፕሮጀክት በሰኔ ወር 2006 ዓ.ም. የጀመረ ሲሆን፤ፕሮጀክቱ ከዚህ ቀደም ያልነበሩ የሕግ መፍትሔዎችንና ከለላዎችን በኦሮሚያና በሐረሪ ክልሎች፣ በምሥራቅ/ምዕራብ ሐረርጌ ዞኖች አቅም ለሌላቸው ማህበረሰቦች ሰጥቷል። በዓመቱ መጨረሻም 128,357 አቅም አልባ ዜጎች(73,905 ሴቶች እና 54, 452 ወንዶች) ከነዚህ ቀደም ሲል ካልነበሩ አገልግሎቶች ተጠቃሚ ሊሆኑ ችለዋል።

## የፖለቲካ እስረኞች እና በቁጥጥር ሥር ያሉ ሰዎች

የፖለቲካ እሥረኞችን ብዛት በተመለከተ የሰብዓዊ መብት ድርጅቶች እና ዲፕሎማቲክ ሚሽኖች የሚሰጡት ግምት ልዩነት ነበረው። መንግሥት እሥረኞች በአለም ዓቀፍ የሰብዓዊ መብት ድርጅቶች እንዲጎበኙ አልፈቀደም። መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ባቀረቧቸው ሪፖርቶች ሰዎች በመላ አገሪቱ ባሉ ይፋዊ ባልሆኑ ሥፍራዎች፣በተለይም በወታደራዊ ካምፖች፤እንዲሁም በግል ቢሮዎችና መኖሪያ ቤቶች መታሰራቸውን አመልክተዋል።

በፀረ ሽብር ሕጉ አማካኝነት የተፈረደባቸው ኢትዮጵያውያን ጋዜጠኞች፣የተቃዋሚ ፖለቲካ ድርጅት አባላት እና የመብት ተሟጋቾች ዓመቱን ያሳለፉት በማረሚያ ቤት ነው።

በየካቲት ወር በአዲስ አበባ የሚገኘው የፌዴራሉ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የአንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትሕ አባል የሆኑትን አቶ አሥራት ጣሴን "ከ[ኢትዮጵያ] ፍርድ ቤቶች ፍትሕ መጠበቅ የለብንም" የሚል የግል አስተያየታቸውን ያሰፈሩበትን ጽሑፍ በማሳተም ችሎት ተዳፍረዋል በሚል ከሷቸዋል። ዳኛው በአቶ አሥራት ላይ የአምስት ወራት የእስር ቅጣት የጣሉባቸው ቢሆንም፤ወዲያው እስሩ በሁለት ዓመት እግድ ተፈፃሚ እንዲሆን ወስነዋል።

ፖሊስ ሰኔ 29 ቀን በአዲስ አበባና በመቀሌ በተናጠል ባደረጋቸው እንቅስቃሴዎች አራት የተቃዋሚ ፖለቲካ ፓርቲ አመራር አባላትን በቁጥጥር ሥር አውሏል። መረጃዎች እንደሚጠቁሙት ሀብታሙ አያሌውን፣ዳንኤል ሽበሺን፣የሽዋስ አሰፋንና አብርሃ ደስታን ፖሊስ በሕጉ መሠረት በቁጥጥር ሥር ባዋላቸው በ48 ሰዓታት ውስጥ ዳኛ ፊት አላቀረባቸውም። የታሳሪዎቹ ጠበቃና ሌሎች የፖለቲካ ፓርቲ መሪዎች ፖሊስ ታሳሪዎቹን እንዳናገኛቸው ከልክሎናል ሲሉ ቅሬታ አሰምተዋል። እስከ ዓመቱ መጨረሻ ፖሊስ በተጠርጣሪዎቹ ላይ መደበኛ ክስ አልተመሠረባቸውም።

በ2004 ዓ.ም. መንግሥት የሽብርተኝነትና የሀገር ክህደት ፍርደኛ የሆኑት የእስክንድር ነጋ እና የአንዱአለም አራጌ ንብረቶች ለተከሰሱባቸውና ቅጣት ለተላለፉባቸው ወንጀሎች መፈጸሚያነት

መዋላቸውን ለማጣራት በመፈለጉ የንብረት ይታገድልኝ ጥያቄ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ማቅረቡን አስታውቆ ነበር። ፍርድ ቤቱ እስከ ዓመቱ መጨረሻ በጉዳዩ ላይ ውሳኔ አልሰጠም።

**የፍትሐ ብሔር ዳኝነት ሥነ ሥርዓት እና የመፍትሔ እርምጃዎች**

ሕጉ ዜጎች የሰብዓዊ መብት ጥሰቶች ሲፈፀሙባቸው ለፍትሐ ብሔር ፍርድ ቤቶች አቤቱታ የማቅረብ መብት ይሰጣል፤ ሆኖም በዓመቱ ውስጥ እንዲህ ያሉ ጉዳዮች አልቀረቡም።

## ረ. በግል ነጻነት፣ በቤተሰብ፣ በመኖሪያ ቤት ወይም በመልዕክት ልውውጥ ላይ የሚፈፀም የዘፈቀደ ጣልቃ-ገብነት

ሕጉ የመንግሥት አካላት የግለሰብ ንብረትን ለመፈተሽ የፍርድ ቤት ማዘዣ ይዘው እንዲቀርቡ ያዛል፤ ነገር ግን ፖሊሶች ብዙውን ጊዜ ሕጉን አያከብሩም፤ ፍርድ ቤቶች ያለ ፍተሻ ትዕዛዝ የተገኘ ማስረጃን ተቀባይነት መንፈጋቸውን የሚያሳይ ሰነድም አልነበረም።

ፖሊስ ሽብርተኞች ናቸው ባላቸው ግለሰቦች ላይ ማስረጃ ለማሰባሰብ በአዲስ አበባ የሚኖሩ ሙስሊሞችን ቤቶች በምሽት እንደበረበረ የሚገልጹ ሪፖርቶች ዓመቱን ሙሉ በየጊዜው ሲቀርቡ ነበር። መንግሥት ፖሊሶቹ የፍተሻ ፈቃድ እንደነበራቸው ተናግሯል።

የተቃዋሚ ፖለቲካ ፓርቲ መሪዎች የስልክ ጠለፋ እና ሌሎች በኤሌክትሮኒክ መሳሪያዎች የታገዙ ስለላዎች እንደሚካሄዱባቸው ጥርጣሬ እንዳላቸው ሪፖርት አድርገዋል። ከዚህ ሌላ የመንግሥት ሰላዮች እንደሆኑ የሚነገርላቸው ሰዎች በአገሪቱ ፓርላማ በሽብርተኝነት የፈረጃቸው ድርጅቶች ተወካዮች እንደሆኑ አስመስለው ለተቃዋሚ ፖለቲካ መሪዎች ስልክ በመደወል እና የገንዘብ ዕርዳታ እንደሚያደርጉ ቃል በመግባት በሕገ ወጥ ድርጊቶች እንዲሳተፉ እንደገፋፏቸው ተነግሯል።

መንግሥት የተወሰኑ ግለሰቦችን እንቅስቃሴ ተከታትለው ሪፖርት እንዲያደርጉ ገንዘብ የሚከፈላቸው መረጃ አቀባዮችን የማሰማራት ስልትን በስፋት ተጠቅሟል የሚሉ ሪፖርቶች አሉ። የገዢው ፓርቲ ካድሬዎች እና የሚሊሽያ አባላት፣ ሳይፈቀድላቸው መኖሪያ ቤታቸው ድረስ ዘልቀው መግባታቸውንና ማስፈራራታቸውን የተቃዋሚ ፓርቲ አባላት ሪፖርት አድርገዋል።

የፀጥታ ኃይሎች በመንግሥት ለጥያቄ የሚፈለጉ ሰዎችን ቤተሰቦች በቁጥጥር ሥር አውለዋል።

የፌደራል መንግሥት እና የክልል መንግሥታት በአፋር፣ በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ፣ በጋምቤላ፣ በደ/ብ/ብ/ሕ/ክ እና በሶማሌ ክልሎች ‹‹የመንደር ምሥረታ›› ዕቅዶችን በሥራ ላይ ማዋል ቀጥለዋል። ዕቅዶቹ በተበታተነ አኳኋን የሚኖሩ የገጠር ሕዝቦችን ለተደጋጋሚ ድርቅ ከተጋለጡ ደረቅ አልያም ከፊል-ደረቅ አካባቢዎች አንስቶ በክልል መንግሥታት ወደተዘጋጁ ቦታዎች በአንድ አካባቢ ማስፈርን ያካትታሉ። የመንደር ምሥረታው ዓላማዎችም (የጤና አገልግሎት፣ የትምህርት እና የንፁህ መጠጥ ውሃ አቅርቦትን የመሳሰሉ) የመንግሥት አገልግሎቶችን አቅርቦት ማሻሻል፣ ማኅበረሰቦችን ከተፈጥሯዊ አደጋዎች እና ጥቃቶች መከላከል፣ እንዲሁም አካባቢን ክፉኛ የሚጎዱ አሉታዊ የአስተራረስ ልማዶችን መለወጥ ናቸው ተብለው ተገልፀዋል። አንዳንድ ታዛቢዎች ግን፣ መርሀ ግብሩ ለንግድ እርሻ የሚውል መጠነ-ሰፊ መሬት በሊዝ ማከራየት የሚቻልበትን ሁኔታ ለማመቻቸት የታለመ ነው ሲሉ ገልጸዋል። መንግሥት የመንደር ምሥረታ መርሀ ግብሩ ሙሉ በሙሉ በፈቃደኝነት ላይ ተመሥርቶ እንደሚፈፀም ተናግሯል።

ዓለም አቀፍ ለጋሾች ከ2003 ጀምሮ በተመሠረቱት መንደሮች ካደረጓቸው ከ18 የሚበልጡ ጉብኝቶች በመነሳት፤ በዚህ መርሀ ግብር የሰብዓዊ መብት ጥሰት መፈጸሙን የሚያረጋግጥ ማስረጃ ማግኘት እንዳልቻሉ ሪፖርት አድርገዋል። ነገር ግን መርሀ ግብሩን ለመተግበር በነበረው ችኮላ የተነሳ ለሰፋሪዎች ቃል በተገባላቸው መሠረት በአዲሱ አካባቢ በቂ መሠረተ ልማቶች ማሟላት ያለመቻልን የመሳሰሉ ችግሮች መኖራቸውን ተመልክተዋል። ሰፋሪዎች እና ቤተሰቦች የምግብ እርዳታ፣ መሠረታዊ አገልግሎቶች እና መሬት እንደሚያገኙ ባለሥልጣናት በሰጧቸው ማረጋገጫ ላይ ተመሥርተው ለመሥፈር የተስማሙ ቢመስልም፤ በአንዳንድ ሁኔታዎች ግን በአዲሱ ስፍራ በቂ መሰረታዊ አገልግሎቶች እና መጠለያ ሳይዘጋጅላቸው ከለመዱት ቀያቸው የተንቀሳቀሱ ማህበረሰቦች ነበሩ። ዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብቶች ድርጅቶች በመንደር የማስፈር ሂደቱ ላይ ያላቸውን ስጋት መግለጻቸውን ቀጥለዋል። ኦክላንድ ኢንስቲትዩት በየካቲት ወር ባወጣው ሪፖርት የጦር ኃይሉ በኦሞ ሸለቆ የሚገኙ ማህበረሰቦችን በኃይል እንዳፈናቀላቸው እና የሰብዓዊ መብት ጥሰቶች እንደፈጸመባቸው አስታውቋል። ኦክላንድ ኢንስቲትዩት በሐምሌ ወር ያወጣው ሪፖርት እንደሚያረጋግጠው፤

በጥር 2004 ዓ.ም. በታችኛው የኦሞ ሸለቆ በተደረገ ግምገማ የማህበረሰቡ አባላት ስለተፈጸሙባቸው የሰብዓዊ መብት ጥሰቶች ለለጋሽ አገራት ተወካዮች አስረድተዋል፡፡

## ክፍል 2፡- የሲቪል መብቶች እና ነጻነቶች ከበሬታ

### ሀ. የመናገር እና የፕሬስ ነፃነት

የመናገር እና የፕሬስ ነጻነት በሕገ-መንግሥቱ እና በሕግ የተደነገገ ቢሆንም፤ ባለስልጣናት ጋዜጠኞችን እና መንግሥትን ይተቻሉ ብለው የጠረጠሯቸውን ሰዎች በቁጥጥር ሥር አውለዋል፣አስረዋል ብሎም ክስ መስርተውባቸዋል፡፡ አንዳንድ ጋዜጠኞች፣አርታኢዎችና አሳታሚዎች እንዳይያዙ በመፍራት አገሪቱን ለቀው ተሰደዋል፡፡ በዓመቱ መጨረሻ ቢያንስ 16 የሚሆኑ ጋዜጠኞች በእስር ላይ የነበሩ ሲሆን፤አሥሩ በዓመቱ ውስጥ የታሰሩና ክስ የተመሠረተባቸው ናቸው፡፡ ከአንዱ በስተቀር ሁሉም የዋስትና መብት ተነፍገው በእስር እንዲቆዩ ተደርገዋል፡፡ አራት ጋዜጠኞችና አሳታሚዎች ተከሰውና በፍርድ ቤት ጉዳያቸው ታይቶ በሌሉበት ተፈርዶባቸዋል፡፡

<u>**የመናገር ነፃነት**</u>፡- ባለሥልጣናት ሰዎች በመንግሥት ላይ ትችት በመሰንዘራቸው በቁጥጥር ሥር አውለው አስፈራርተዋቸዋል፡፡ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች መንግሥት የሚተቹትን ግለሰቦች እንደሚያስቃያቸው አመልክተዋል፡፡መንግሥት ጋዜጠኞችን እና ተቃዋሚ ፖለቲከኞችን በማስፈራራት፣ በማሰር እንዲሁም የተቃዋሚ ፖለቲካ ቡድኖችን እንቅስቃሴ በመከታተልና ጣልቃ በመግባት የሚሰነዘርበትን ትችት ለማፈን ሙከራ አድርጓል፡፡ ባለሥልጣናት በርካታ ጋዜጠኞች፣ጦማርያንና የግል ፕሬስ ውጤቶች ላይ ክስ መሥርተዋል፡፡አንዳንድ ሰዎች በጸጥታ ኃይሎች (የመብት) ጥሰት እንደተፈጸመባቸው ከተናገሩ ባለስልጣናት የቂም በቀል እርምጃ ይወስዱብናል ብለው ይፈራሉ፡፡

<u>**የፕሬስ ነፃነት**</u>፡- መንግሥት የግል ጋዜጦችን መዝጋት ቀጥሏል፡፡ ሐምሌ 28 የፍትሕ ሚኒስቴር ባወጣው መግለጫ ዕንቁ፣ፋክት፣አዲስ ጉዳይ፣ሎሚ፣ ጃኖና አፍሮ ታይምስ የተሰኙ የግል ህትመቶች በተደጋጋሚ ሕገ መንግሥታዊ ሥርዓቱን በኃይል ለመናድ አነሳስተዋል" ሲል

ከሷቸዋል፡፡ አንዳንዶቹ በማስረጃነት የተጠቀሱ ጽሑፎች የመንግሥትን ድርጊቶች የሚተቹ ነበሩ፡፡ አብዛኞቹ እነዚህን ድርጊቶች መቃወም እንደሚገባ ቢያመለክቱም የኃይል እርምጃ አስፈላጊነትን አይደግፉም፤ምናልባትም ከኃይል እርምጃ ጋር የተገናኙ ጉዳዮችን ካነሱም በጣም አልፎ አልፎ ነው፡፡ መንግሥት ይህን መግለጫ ባወጣ በሳምንቱ በሕትመት ውጤቶችና በሠራተኞቻቸው ላይ የወንጀል ክስ መሥርቶባቸዋል፡፡ የፌዴራሉ ፍርድ ቤት የአዲስ ጉዳይ፣የሎሚና የፋክት መጽሔቶች ኃላፊዎች በሌሉበት ክሳቸውን በመስማት ፈርዶባቸዋል፡፡ ኃላፊዎቹ ሁከት በመፍጠር፣ መሠረተ ቢስ አሉባልታ በማተምና በማሰራጨት፣እንዲሁም ሕገ መንግሥታዊ ሥርዓቱን ሕገወጥ በሆነ መንገድ ለማስወገድ በማሴር የተከሰሱ ሲሆን፤ከሦስት ዓመት ከሦስት ወር እስከ ሦስት ዓመት ከአሥራ አንድ ወር እስራት ተፈርዶባቸዋል፡፡

ቀሪዎቹ 18 የግል ጋዜጦች በአዲስ አበባ ከ144,000 በላይ ጠቅላላ የስርጭት ብዛት ነበራቸው፡፡ መንግሥት ከሚያሳትማቸው ዕለታዊ የአማርኛ እና የእንግሊዝኛ ጋዜጦች፣እንዲሁም በየዕለቱ የሚታተመው የግል የእንግሊዝኛ ጋዜጣ ዴይሊ ሞኒተር በስተቀር፤ አብዛኞቹ ጋዜጦች በየሳምንቱ ወይም በሳምንት ሁለት ጊዜ የሚታተሙ ነበሩ፡፡

ሬዲዮን ጨምሮ ለአብዛኛው ሕዝብ ዋነኛ የዜና ምንጭ የሆነውና አገር አቀፍ ሥርጭት ያለው ብቸኛ የቴሌቪዥን ጣቢያ በመንግሥት ቁጥጥር ሥር ነው፡፡ በዋና ከተማይቱ ስድስት የግል የኤፍ.ኤም. ራዲዮ ጣቢያዎች የሚገኙ ሲሆን፤ በትግራይ ክልል አንድ የግል ሬዲዮ ጣቢያ እንዲሁም በክልሎች ቢያንስ 19 የማኅበረሰብ ራዲዮ ጣቢያዎች ፕሮግራሞቻቸውን ያሰራጫሉ፡፡ በመንግሥት ይዞታ ሥር ያለው የኢትዮጵያ ሬዲዮ በአገሪቱ ሰፊ የስርጭት ሽፋን የነበረው ሲሆን፤ ከገዢው ፓርቲ ጋር ግንኙነት ያለው ሬዲዮ ፋና ተከታዩ ነበር፡፡

በመንግሥት ቁጥጥር ሥር ያሉ መገናኛ ብዙኃን በአመዛኙ የመንግሥትን እና የገዢውን ኢሕአዴግ ዕይታ [አቋም] አንፀባርቀዋል፡፡ መንግሥት በየጊዜው ከውጭ አገራት የሚተላለፉ ስርጭቶችን አፍኗል፡፡ ሕጉ የፖለቲካ እና የሃይማኖት ድርጅቶች እንዲሁም የውጭ አገር ዜጎች የኤሌክትሮኒክ መገናኛ ብዙኃን ባለቤት እንዳይሆኑ ይከለክላል፡፡

<u>ሁከት እና ወከባ</u>፡- መንግሥት ጋዜጠኞችን ማሠር፣ ማዋከብ እና ለፍርድ ማቅረቡን ቀጥሏል፡፡ ይህም ከተዘጋው የሙስሊሞች ጉዳይ መጽሄት ጋር በተያያዘ በጸረ-ሽብር ሕጉ የተከሰሱ ሶስት

ሰዎችን ይጨምራል። በማዕከላዊ ማረሚያ ቤት የታሰሩ አንዳንድ ጋዜጠኞች ስቃይ እንደሚደርስባቸው ተነግሯል።

ሚያዝያ 17 እና 18 ፖሊስ በአዲስ አበባና ከአዲስ አበባ በስተምዕራብ በሚገኘው የአምቦ ከተማ ከዞን 9 የመብት ተከራካሪ ቡድን ጋር ግንኙነት አላቸው በሚል ስድስት ጦማርያንና ሦስት ነፃ ጋዜጠኞችን በቁጥጥር ሥር ካዋለ በኋላ መኖሪያ ቤቶቻቸውን በመበርበር ላፕቶፕ ኮምፒዩተሮችን ጨምሮ የተለያዩ የግል ንብረቶችን ይዟል፤የቤተሰብ አባላትና ደጋፊዎቻቸው እስር ቤት ሄደው እንዳይጠይቋቸው ከልክሏል። በሐምሌ ወር የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በተጠርጣሪዎቹ ላይ በፀረ ሽብር አዋጁ መሠረት የቀረበባቸውን ክስ የተቀበለ ሲሆን፤የዋስትና መብት ነፍጓቸዋል። የፍርድ ሂደት እስከ ዓመቱ መገባደጃ ቀጥሎ ነበር።

ጥቅምት 19 ፍርድ ቤት በተመስገን ደሳለኝ ላይ "በማነሳሳትና ትክክለኛ ያልሆነ መረጃ በማሰራጨት" ወንጀል የሦስት ዓመት እስራት በይኖበታል። ባለሥልጣናት በተዘጋው የፍትሕ ጋዜጣ ዋና አዘጋጅ ተመስገን ላይ ከ2004 ዓ.ም. ጀምሮ ክስ ሲመሠርቱ ቆይተዋል።

**ቅድመ-ምርመራ (ሳንሱር) ወይም በይዘት ላይ የተጣሉ ገደቦች**፡- መንግሥት በሚያደርሰው ወከባ የተነሳ ጋዜጠኞች በአንዳንድ ምስጢራዊ ጉዳዮች ላይ ከመዘገብ ተቆጥበዋል። ጥቂት የማይባሉ የግል ጋዜጦች በመንግሥት መደበኛ ያልሆነ የኤዲቶሪያል ቁጥጥር ይደረግባቸው እንደነበር አመልክተዋል፤ ለዚህም [ከመንግሥት ባለሥልጣናት የተዘጋጁ] ጽሑፎችን አትመው እንዲያወጡ የሚቀርብላቸውን ጥያቄ እና ታትመው የወጡ መንግሥትን የሚተቹ ጽሑፎችን አስመልክቶ ከመንግሥት ባለሥልጣናት የሚደርሷቸውን የስልክ ጥሪዎች ጠቅሰዋል። የግሉ ዘርፍ እና የመንግሥት ጋዜጠኞች በዕለት ተዕለት ሥራቸው ራሳቸውን ሳንሱር አድርገዋል።

**የስም ማጥፋት ሕግጋት/ብሔራዊ ደኅንነት**፡- መንግሥት የፀረ-ሽብር ሕጉን ትችትን ለማፈን ተጠቅሞበታል። ፓርላማው በ 2003 ሽብርተኛ ድርጅቶች ብሎ በፈረጃቸው አምስት ቡድኖች (ግንቦት 7፣ ኦብነግ፣ ኦነግ፣ አል-ቃዒዳ እና አል-ሸባብ) ዙሪያ መዘገብ ፈርተዋል፤ ለዚህም የተጠቀሰው ምክንያት በእነዚህ ቡድኖች ዙሪያ ዘገባዎችን ማቅረብ በሕግ የሚያስቀጣ ይሁን አይሁን ግልጽ አለመሆኑን ነው። የአገር ውስጥ እና የውጭ አገር የዜና ወኪሎችን ጨምሮ በርካታ ጋዜጠኞች ራስን ሳንሱር የማድረግ ዝንባሌ እያደገ መምጣቱን ጠቁመዋል።

መንግሥት የስም ማጥፋት ሕግጋትን ትችትን ለማፈን ተጠቅሞበታል፡፡
የካቲት 4 ቀን ፖሊስ አንድ የቀድሞ የፓርላማ አባልን የሕይወት ታሪክ ከመጻፍ ጋር በተያያዘ በስም ማጥፋት ወንጀል ጠርጥሮ ለጥያቄ ይፈለጋሉ በሚል የአንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትሕ የድርጅት ጉዳዮች ኃላፊ የነበሩትን አቶ ዳንኤል ተፈራን በጊዜያዊነት በቁጥጥር ሥር ቢያውልም፤ክስ ሳይመሠርትባቸው ለቋቸዋል፡፡

ጥር 20 በሀዋሳ ከተማ የሚገኘው የሲዳማ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በስም ማጥፋት የተከሰሱትን የኢትዮ-ምኅዳር ጋዜጣ ዋና አዘጋጅ፣አዘጋጅና አሳታሚ በነፃ አሰናብቷቸዋል፡፡ የሀዋሳ ዩኒቨርስቲ ባለሥልጣናት በሳምንታዊው የአማርኛ ጋዜጣ ላይ ክስ የመሠረቱት በሰኔ ወር 2005 ዓ.ም. ካሳተመው በዩኒቨርስቲው ሠራተኞች የሚፈፀሙ የሙስና ተግባራትን ከሚያጋልጥ ጽሑፍ ጋር በተያያዘ ሲሆን፤የመገናኛ ብዙሃን ዘገባዎች እንዳመለከቱት ዳኛው ተከሳሾች "በሕዝብ ተቋማት የሚፈፀሙ ብልሹ አሠራሮችን በማጋለጣቸው ትክክለኛ ሥራ ሠርተዋል" ብለዋል፡፡

## የኢንተርኔት ነፃነት

በመንግሥት ባለቤትነት የተያዘው ኢትዮ ቴሌኮም ብቸኛው የኢንተርኔት አገልግሎት ሰጪ ድርጅት ነበር፡፡ መንግሥት የኢንተርኔት ተደራሽነትን በመቆጣጠር ብሎጎችን፣ የተቃዋሚ ድረገፆችን እና የግንቦት 7፣ ኦነግ፣ እና ኦብነግ ድረገፆችን ጨምሮ በርካታ ድረገፆችን (ኢትዮጵያ ውስጥ) እንዳይከፈቱ አግዷል፡፡ መንግሥት እንደ አል ጀዚራ ያሉ የዜና ገጾችን ለአጭር ጊዜ እንዳይታዩ አግዷል፡፡ እንደ ፌስቡክ፣ ትዊተር እና ያሁ ያሉ ድረ ገጾችም ለአጭር ጊዜ ታግደው ነበር፡፡ በውጭ አገር ነዋሪ የሆኑ ተቃዋሚዎች የሚያስተዳድሯቸው እንደ አዲስ ነገር፣ ናዝሬት፣ ኢትዮጵያን ሪቪው፣ ሳይበር ኢትዮጵያ፣ ቋጠሮ የአማርኛ መጽሔት፣ ትንሣኤ ኢትዮጵያ፣ እና የኢትዮጵያ ሚዲያ ፎረምን የመሳሰሉ በርካታ የዜና ብሎጎች እና ድረገፆች (ኢትዮጵያ ውስጥ) ተደራሽ አልነበሩም፡፡ ባለስልጣናት የኢንተርኔት ተጠቃሚዎች ከመንግሥት ቁጥጥር ውጭ ሆነው አገልግሎቱን እንዲያገኙ የሚያስችለውን "የቨርቹዋል ፕራይቬት ኔትዎርክ" (Virtual Private Network) አቅራቢዎችን አግደዋል፡፡ መንግስት የስልክ ጥሪዎችን፣የመልዕክት ልውውጦችንና ኢ-ሜይሎችን የጠለፈ ሲሆን፤ በዚሁ መነሻነት የታሰሩም እንዳሉ ተነግሯል፡፡

በዓለም አቀፉ የቴሌኮሙኒኬሽን ሕብረት መረጃ መሠረት በ2004 ዓ.ም. ወደ 1.9 በመቶ የሚጠጉ ግለሰቦች ኢንተርኔት ተጠቅመዋል።

በ2005 ዓ.ም. "ሲቲዝን ላብ" (Citizen Lab) የተባለ ካናዳ ውስጥ በቶሮንቶ ዩኒቨርሲቲ የሚገኝ የምርምር ማዕከል ኢትዮጵን ጨምሮ 25 አገራት ከ"ፊንፊሸር የስለላ" (Finfisher) ሶፍትዌር ጋር የተገናኙ ሰርቨሮችን እንደሚጠቀሙ አመልክቷል። በሪፖርቱ መሠረት "የሰብዓዊ መብት አያያዛቸው አጠያያቂ በሆኑ አገራት ያሉ የሰብዓዊ መብቶች ተሟጋቾች እና ተቃዋሚ ፖለቲከኞችን ለማጥቃት በጥቅም ላይ እየዋለ በመሆኑ ፊንፊሸር መጥፎ ዝና ሊያተርፍ ችሏል።" በአገሪቱ በ"ፊንስፓይ" (Finspy) የተደረገ ዘመቻ "የተጠቃሚዎችን ኮምፒውተሮች ለመበከል የኢትዮጵያዊውን ተቃዋሚ ፓርቲ የግንቦት 7 ምስሎች በማታለያነት ተጠቅሟል።" ተብሏል።

## አካዳሚያዊ ነፃነትና ባህላዊ ሁነቶች

መንግሥት የአካዳሚ ነጻነትን ገድቧል። ይህም በሥርዓተ-ትምህርት፣ በመምህራን ምደባዎች እና በተማሪዎች የትምህርት መስክ ምርጫዎች ላይ መወሰንን ይጨምራል። ባለስልጣናት በዩኒቨርሲቲ እና በከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች የመናገር፣ ሐሳብን የመግለጽ እና የመሰብሰብ ነፃነቶችን በተደጋጋሚ ገድበው ነበር።

ገዢው ፓርቲ በትምህርት ሚኒስቴር አማካይነት በድህረ ምረቃ መርሀ ግብር ምደባ ወቅት ለፓርቲው ታማኝ ለሆኑ ተማሪዎች  ቅድሚያ መስጠት እንደቀጠለ ምንጮች ገልጸዋል። በየትኛውም የትምህርት ዘርፍ ከተመረቁ በኋላ ስራ ለመቀጠር የፓርቲው አባል ለሆኑ ተማሪዎች ቅድሚያ እንደሚሰጥ አንዳንድ የዩኒቨርስቲ መምህራን ተናግረዋል።

መምህራን በይፋ ከሚታወቁ የትምህርት ዕቅዶች ወጣ ብለው እንዳያስተምሩ ባለሥልጣናት ከልክለዋል። የኢህአዴግ አባላት ያልሆኑ መምህራን ወደማይፈለጉ ቦታዎች የሚዘዋወሩበት ዕድል ሰፊ እንደሆነ እና በደረጃ ዕድገት ወቅትም እንደማይካተቱ በርካታ ሪፖርቶች ጠቁመዋል። የኢሕአዴግ አባል ያልሆኑ መምህራን ያለ ፕሮግራም የሚጠሩ ስብሰባዎችን አልተካፈላችሁም በሚል ከሥራቸው እንደሚባረሩ የሚገልጹ አንዳንድ ሪፖርቶች ቀርበዋል።

የመምህራን የሰው ኃይል ምደባ ግልጽነት የጎደለው ከመሆኑም ሌላ፤ የድርጅት አባልነትን፣ ብሔርን ወይም ሃይማኖትን መሠረት ያደረጉ መድሎዎች እንደሚፈፀሙ በመግለጽ የአካዳሚክ ማኅበረሰቡ አባላት ቅሬታቸውን አሰምተዋል።

ብዛት ያላቸው ታማኝ ምንጮች፣ መምህራን፣ የአሥረኛ ክፍልና ከዚያም በላይ የሆኑ ተማሪዎች ስለ አብዮታዊ ዴሞክራሲ ጽንሰ-ሐሳብ እና ስለ ኢሕአዴግ የፓርቲ ርዕዮተ-ዓለም ሥልጠና መውሰድ ይጠበቅባቸው ነበር። በነሐሴ ወር የትምህርት ሚኒስቴር 116,000 አዳዲስ እና 250,000 ነባር የዩኒቨርስቲ ተማሪዎች አስገዳጅ የሆነ የመንግሥት ፖሊሲ ሥልጠና መውሰድ እንደሚኖርባቸው አስታውቋል።

የግል ዩኒቨርስቲዎች በሕግ እና በመምህራን ትምህርት ዘርፍ የዲግሪ መርሀ ግብር እንዳይሰጡ ትምህርት ሚኒስቴር ያወጣው መመሪያ ይከለክላል። በተጨማሪም የግል ዩኒቨርሲቲዎች ሥርዓተ ትምህርታቸውን ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ቀደም ሲል ካወጣው የተፈጥሮ ሣይንስ እና የማኅበራዊ ሣይንስ የአካዳሚ መርሃ-ግብሮች የ70 ለ30 ድልድል ፖሊሲ ጋር እንዲያጣጥሙ መመሪያው ያዛል። በዚህ የተነሳ በመንግሥት ዩኒቨርሲቲዎች ማህበራዊ ሳይንስ የሚያጠኑ ተማሪዎች ቁጥር እየቀነሰ መጥቷል። የግል ዩኒቨርስቲዎች ሥርዓተ-ትምህርት ደግሞ በአመዛኙ በማኅበራዊ ሳይንስ ላይ ያተኮረ ነበር።

የተቃውሞ አመለካከት በማራመድ ወይም በሰላማዊ ሰልፎች በመሳተፍ የተጠረጠሩ የኦሮሞ ብሔር ተወላጅ የሆኑ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ተማሪዎች ላይ ተደጋጋሚ ክትትልና የዘፈቀደ እስር እንደተፈጸመ ሪፖርቶች አመልክተዋል። አምነስቲ ኢንተርናሽናል በ2006 ዓ.ም. ባወጣው ሪፖርት በነዚህ ጥርጣሬዎች የተነሳ ተማሪዎች ከትምህርት ቤት እንደተባረሩ ወይም እንደታገዱ አመልክቷል።

## ለ. ሰላማዊ የመሰብሰብና የመደራጀት ነፃነት

### የመሰብሰብ ነፃነት

ምንም እንኳ ሕጉና ሕገ-መንግሥቱ የመሰብሰብ ነፃነትን ቢፈቅዱም፣ መንግሥት ይህንን መብት አላከበረም። ታላላቅ ሕዝባዊ ስብሰባዎችን ወይም ሰላማዊ ሰልፎችን ማካሄድ ቢያስፈልግ፤ አስተባባሪዎች ሁኔታውን ከ48 ሰዓታት በፊት ለመንግሥት ማሳወቅና ፈቃድ ማግኘት ይጠበቅባቸዋል። ባለስልጣናት ፈቃድ መከልከል ባይችሉም፤ ስብሰባዉ ወይም ሰልፉ ከተጠየቀው በተለየ ቦታ ወይም ሰዓት እንዲካሄድ ሊጠይቁ ይችላሉ። ይህም የሚሆነው ሰልፉ የሕዝብ ደህንነትን ወይም የመንቀሳቀስ ነጻነትን የሚስተጓጉል ሆኖ ሲገኝ ነው ። ባለስልጣናት አንድ ድርጊት በሌላ ጊዜ ወይም ቦታ እንዲካሄድ ከወሰኑ ይህንኑ ጥያቄው በቀረበ 12 ሰዓታት ውስጥ ለድርጊቱ አዘጋጆች በጽሁፍ ማሳወቅ እንዳለባቸው ሕጉ ይደነግጋል።

መንግሥት አንዳንድ የተቃዋሚ ፓርቲ ሰልፎችን የከለከለ ቢሆንም፤የተወሰኑትን ፈቅዷል። የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በዓመቱ ከተጠየቁት 22 የሰልፍ ጥያቄዎች ለ13ቱ ፈቃድ ሲሰጥ፣9 ጥያቄዎችን ሳያስተናግድ ቀርቷል። አስተባባሪዎች መንግሥት ጣልቃ ይገባ እንደነበር፤ባለሥልጣናት አብዛኛዎቹ ሰልፎች የጊዜና የቦታ ለውጥ እንዲደረግባቸው አድርገዋል ሲሉ ወቅሰዋል። ባለሥልጣናቱ እነዚህን ለውጦች ሲያደርጉ የሕዝብ ደህንነትን ለመጠበቅ እንደሆነ ቢገልጹም፤አስተባባሪዎች ይህ አሳማኝ አይደለም የሚል ወቀሳ አቅርበዋል። በሚያዝያና በግንቦት የአዲስ አበባ ከተማን በዙሪያዋ ወዳሉ የኦሮሚያ ክልል በኦሮሚያ ክልል ከተሞች ለማስፋፋት የሚያስችለውን የጋራ ልማት ረቂቅ ማስተር ፕላንን በመቃወም በክልሉ በሚገኙ በርካታ የዩኒቨርስቲዎች ሰልፎች ተካሂደዋል። የፀጥታ ኃይሎች በሰልፈኞች ላይ ድብደባና ግድያ መፈጸማቸውን ሪፖርቶች አመልክተዋል።

የአካባቢ መስተዳድር ባለሥልጣናት (ሁሉም ማለት ይቻላል) የኢሕአዴግ አባላት በመሆናቸው፣ በየከተማው የሚገኙ የማዘጋጃ ቤት አዳራሾችን ይቆጣጠራሉ። ተቃዋሚ ፓርቲዎች ለሕጋዊ የፖለቲካ ስብሰባ አዳራሾችን በሚጠይቁበት ወቅት እነዚህ የአካባቢ ባለሥልጣናት እንደሚከለክሏቸው አልያም የስብሰባውን መርሀ ግብር እንደሚያስተጓጉሉባቸው ጠቅሰው በርካታ ስሞታዎችን አቅርበዋል። የሆቴሎች እና የትልልቅ አዳራሾች ባለቤቶች በግልጽ

የማይታወቁ ውስጣዊ ደንቦችን በመጥቀስ የፖለቲካ ፓርቲዎች አዳራሾቻቸውን እንዳይጠቀሙ ስለመከልከላቸው በርካታ የታመኑ ሪፖርቶች ቀርበዋል፡፡

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደርን ጨምሮ የክልል መስተዳድሮች ለትልልቅ ስብሰባዎች ፈቃድ ለመስጠትም ሆነ አስፈላጊውን የፀጥታ ኃይል ለመመደብ እምብዛም ፈቃደኛ አልነበሩም፡፡

መንግሥት ከተቃውሞ ሰልፎች ጋር በተያያዘ ሰዎችን አስሯል፡፡ ለምሳሌ ያህል ሰማያዊ ፓርቲ በጎንደር ጥር 25 ቀን ሰልፍ እንደሚያካሄድ በማስዋወቅ ላይ የነበሩ የፓርቲው አባላት ጥር 22 ቀን ለአጭር ጊዜ በቁጥጥር ሥር ውለዋል፡፡ከዚህ ሌላ ባለስልጣናት የአንድነት ለዴሞክራሲ እና ለፍትህ ፓርቲ አባላትን በሚያዝያ ወር ውስጥ ሰልፍ ለመጥራት በሚዘጋጁበት ወቅት ለእስር ዳርገዋቸዋል፡፡

የመገናኛ ብዙሃን ዘገባዎች እንዳመለከቱት፣ በሰሜናዊቱ የዓዲግራት ከተማ የመንግሥት ባለሥልጣናት በዓዲግራት ጥር 18 ሰላማዊ ሰልፍ ለማካሄድ በዝግጅት ላይ የነበሩ ሁለት የተቃዋሚው የአረና ትግራይ ፓርቲ አባላትን በቁጥጥር ሥር ሲያውል፤የተቀሩት ላይ ድብደባ ፈጽመዋል፡፡ የመንግሥት ኃይሎች በፈፀሙባቸው ድብደባ በደረሰባቸው ጉዳት የተነሳ የአረና ትግራይ አባል የሆኑት አቶ አስገደ ገብረስላሴ ሆስፒታል ገብተዋል፡፡

በመጋቢት ወር ፖሊስ ሕገወጥ ስብሰባ አካሂዳችኋል በሚል በደቡብ ክልል በወላይታ ሶዶ ከተማ በግለሰብ መኖሪያ ቤት ስብሰባ ላይ የነበሩ የአንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትሕ ፓርቲ አባላትን ለአጭር ጊዜ በቁጥጥር ሥር አውሏል፡፡ ሪፖርቶች እንዳመለከቱት ፖሊስ የተሰባሳቢዎቹን ሞባይል ስልኮች ኬሚካል ውስጥ በመጨመር ከጥቅም ውጭ አድርጓቸዋል፡፡

ሐምሌ 11 ቀን በአንዋር መስጊድ ተካሂዶ በነበረ ተቃውሞ ፖሊስ በአብዛኛው የእስልምና እምነት ተከታዮችንና ሁለት የሰማያዊ ፓርቲ ፣በድምሩ 14 ሰዎችን በቁጥጥር ሥር አውሏል፡፡ ከነዚህ አንዳንዶቹ ከፖሊስ ጋር በተፈጠረው ግጭት ጉዳት የደረሰባቸው ሲሆን፤ሁሉም ግለሰቦች ከአንድ ወር እስር በኋላ ሊፈቱ ችለዋል፡፡

**የመደራጀት ነፃነት**

ምንም እንኳ ሕጉ የመደራጀት ነፃነትን እና በሰላማዊ የፖለቲካ እንቅስቃሴ የመሳተፍ ያልተገደበ መብት ቢሰጥም መንግሥት ይህን መብት ገድቧል።

ከተባበሩት መንግሥታት ሰላማዊ የመሰብሰብ እና የመደራጀት መብት ልዩ ራፖርተር የወጣ ሪፖርት እንደሚያመለክተው፤ "የእነዚህ ሕጎች [የበጎ አድራጎት ድርጅቶች እና ማህበራት አዋጅ] በሥራ ላይ መዋል ማህበራትን በማቋቋም እና ሥራ በመሥራት ላይ የከፋ ተጽዕኖ አሳድረዋል።"

የበጎ አድራጎት ድርጅቶች እና ማኅበራት አዋጅ መንግሥታዊ ላልሆኑ ድርጅቶች ምንጫቸው ያልታወቀ ዕርዳታ እንዳይቀበሉ ይከለክላል። በዚህም ምክንያት ለጋሾች በሙሉ ስማቸው ለሕዝብ ይፋ እንደሚሆን ተገንዝበዋል። ይኸው አሠራር ለፖለቲካ ፓርቲዎች በሚደረጉ ልገሳዎች ሁሉ ላይ በተመሳሳይ መልኩ ተፈፃሚ ነበር።

በአገሪቱ ለመሥራት የሚፈልጉ ዓለም አቀፍ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ማመልከቻቸውን በውጭ አገራት በሚገኙ የኢትዮጵያ ኤምባሲዎች በኩል ማቅረብ ይጠበቅባቸዋል። በመቀጠልም ማመልከቻው በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር በኩል ለበጎ አድራጎት ድርጅቶች እና ማኅበራት ኤጀንሲ ይቀርባል።

**ሐ. የሃይማኖት ነፃነት**

ስለ ሃይማኖት ነፃነት ሙሉ መግለጫውን ከዓለም አቀፍ የሃይማኖት ነፃነት ሪፖርት www.state.gov/j/drl/irf/rpt ድረገጽ ያገኛሉ።

**መ. የመንቀሳቀስ ነፃነት፣ ተፈናቃዮች፣ የስደተኞች ጥበቃ እና ሀገር አልባ ሰዎች**

ምንም እንኳ ሕጉ በአገር ውስጥ የመንቀሳቀስ፣ ወደ ውጭ አገር የመጓዝ፣ የመሰደድ፣ እና ወደ ሀገር የመመለስ ነፃነትን ቢያጎናፅፍም፣ መንግሥት ከእነዚህ ነፃነቶች አንዳንዶቹን ገድቧል።

መንግሥት ከተባበሩት መንግሥታት የስደተኞች ጉዳይ ከፍተኛ ኮሚሽነር (UNHCR) ጽ/ቤት እና ከሌሎች የረድኤት ድርጅቶች ጋር በመተባበር በአገር ውስጥ ለተፈናቀሉ ሰዎች፣

ለስደተኞችና ከስደት ተመላሾች፣ ለጥገኝነት ጠያቂዎች፣ለአገር አልባ ሰዎች እና ለሌሎች ሰዎች ጥበቃ የማድረግ ሥራዎችን አከናውኗል። ሆኖም ባለስልጣናት፣ ታጣቂ ቡድኖች እና የጸጥታ አለመስፈን ችግሮች አንዳንድ ጊዜ የረድኤት ድርጅቶችን የመሥራት አቅም፤በተለይም የፀጥታ ችግር ባሉባቸው የድንበር አካባቢዎች፤ ውስን እንዲሆን አድርገዋል።

የረድኤት ድርጅቶች በዓመቱ የመጀመሪያው መንፈቅ ለሥራቸው እንቅፋት የሆኑ 32 መሰናክሎችን የጠቀሱ ሲሆን፤ባለፈው ዓመት በተመሳሳይ ወቅት 36 ክስተቶች ያጋጠሙ አጋጥመው ከነዚህ አብዛኛዎቹ የተከሰቱት በሱማሌ ክልል ነበር። ካጋጠሙ እክሎች መካከል በረድኤት ድርጅቶች ሠራተኞች ላይ ጥቃት መፈጸም እና ጥላቻ ማሳየት፣ ንብረት ዘረፋ፣ በሰብዓዊ ዕርዳታ መርሀ ግብሮች ሥራ ውስጥ ጣልቃ መግባት እንዲሁም ለረድኤት ሥራ ወደ አገር እንዲገቡ በሚፈለጉ ግለሰቦች እና ቁሳቁሶች ላይ ክልከላ መጣል ይገኙባቸዋል። ይህ መረጃ በአብዛኛው በረድኤት ሥራ ላይ ያተኮረ እንጂ፤ በአገር ውስጥ በተፈናቀሉ ሰዎች ወይም ስደተኞች ላይ ባተኮሩ ተግባራት ላይ ብቻ የተገደበ አልነበረም።

የሶማሌ ክልላዊ መንግሥት ለበርካታ ድርጅቶች ወደ ኖጎብ (ቀድሞ ፊቅ) ዞን እንዲገቡ እና በሰብዓዊ የረድኤት ሥራዎች እንዲሰማሩ የፈቀደ ቢሆንም፤በመንግሥት ወታደሮች እና በኦብነግ መካከል በቀጠሉ ግጭቶች እንዲሁም የአልሸባብ ኃይሎች በሶማሌ ክልል ዶሎ አዶ በሚገኙ የስደተኛ ካምፖች አካባቢ እንደሚንቀሳቀሱ በመሰማቱ፤ ወደ አካባቢዎቹ መጓዝ አስቸጋሪ ነበር። መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች የክልሉን ባለሥልጣናት ፈቃደኝነት ቢያገኙም ሥራ ወደሚሠሩባቸው አካባቢዎች እንዳይገቡ የተከለከሉባቸው አጋጣሚዎች ተስተውለዋል። መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች በብዙ አጋጣሚዎች መርሀግብሮቻቸውን ወደሚያከናውኑባቸው አካባቢዎች የሚያደርጉትን ጉዞ በጸጥታ ችግር ምክንያት አዘግይተዋል፤ያለውን ፍላጎት ሊያጠኑም አልቻሉም። የዓለም አቀፍ ድርጅቶች የሽብር ጥቃት ሊፈፀም እንደነበረ አሳማኝ መረጃ ከተሰራጨ በኋላ የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ሠራተኞቹን በሰኔ ወር ከዶሎ አዶ አካባቢ አስወጥቶ በነሐሴ ወር ወደ ሥራቸው እንዲመለሱ ፈቅዷል። የረድኤት ሠራተኞችን በሚያመላልሱ ተሽከርካሪዎች ላይ ጥቃት፣ በረድኤት ሠራተኞች ላይ ድብደባ፣ ማዋከብ እና የዘፈቀደ እስራት መፈፀሙን ሪፖርቶች ይጠቁማሉ።

**<u>የሀገር ውስጥ እንቅስቃሴ</u>፡-** መንግሥት ሰዎች ወደሶማሌ ክልል እንዳይጓዙ፣ እንዲሁም በክልሉ ውስጥ እንዳይዘዋወሩ ጥሎ የነበረውን ገደብ ቢያለዝብም ሙሉ በሙሉ ግን አላነሳውም፤ ለዚህም ኦብነግ እና በጎረቤት ሶማሊያ የሚገኙ የአልሸባብ አሸባሪዎች የፀጥታ/የደህንነት ስጋት ይፈጥራሉ የሚል ምክንያት ማቅረቡን ቀጥሏል። (ክፍል 2. መ. ሥር ተፈናቃዮች የሚለውን ይመልከቱ)። በጦርነት በተጎዱ አካባቢዎች በነበረው የጸጥታ ስጋት የተነሳ የምግብ እና የመድሃኒት አቅርቦት ለጊዜው ተቋርጦ ነበር። መንግሥት ስደተኞች ከመጠለያ ጣቢያ ውጪ እንዲኖሩ የሚፈቅደውን ፖሊሲ ቀጥሎበት ነበር። ይህን መርሃ ግብር ከሚመራው የስደተኞች እና ከስደት ተመላሾች ጉዳይ አስተዳደር መሥሪያ ቤት በተገኘ መረጃ በነሐሴ ወር 2,993 ስደተኞች ከመጠለያ ጣቢያ ውጪ ይኖራሉ (2,806 በአዲስ አበባ እና አካባቢዋ፣187 በሽሬ)። ይህ አሃዝ በ2004 ዓ.ም. 3,412 ነበር። ይህ ፖሊሲ በሥራ ላይ ከመዋሉ በፊት መንግሥት እንዲህ ዓይነት ፈቃድ የሚሰጠው በዋነኝነት የከፍተኛ ትምህርትን ለመከታተል፣ ለሕክምና ክትትል ወይም በመጠለያ ጣቢያዎች የጸጥታ ስጋትን ለመቀነስ ነበር።

**<u>የውጭ ጉዞ</u>፡-** በ2005 ዓ.ም. መንግሥት ዜጎች ለሥራ ወደ መካከለኛው ምሥራቅ አገራት እንዳይጓዙ ጥሎት የነበረው ክልከላ በዚህም ዓመት ቀጥሏል። ክልከላው ለኢንቨስትመንት ወይም ለንግድ ጉዳዮች የሚጓዙ ዜጎች ላይ ተጽዕኖ አላሳደረም። መንግሥት ክልከላ ያደረገበትን ምክንያት ሲገልጽ በውጭ አገራት በቤት ሠራተኝነት ተቀጥረው በሚሠሩ ዜጎች ላይ የሚደርሰውን ወከባ፣ ማስፈራራት እና አሰቃቂ ጉዳት ለመከላከል ነው ብሏል።

መጋቢት 12 ቀን የብሔራዊ የደህንነትና የፀጥታ አገልግሎት ባለሥልጣናት በቦሌ ዓለም አቀፍ አውሮፕላን ማረፊያ በአንድ የውጭ መንግሥት ድጋፍ በተዘጋጀ የመማማሪያ መርሀ ግብር ላይ ለመሳተፍ ሊጓዙ የነበሩትን የሰማያዊ ፓርቲ ሊቀመንበር አቶ ይልቃል ጌትነትን ካገር እንዳይወጡ ከልክለዋቸዋል።

<u>ስደት</u>፡- በርካታ ዜጎች በሌሎች አገሮች የፖለቲካ ጥገኝነት ጠይቀዋል፤ አልያም በራሳቸው ፍላጎት በውጭ አገራት በስደት ቆይተዋል።

**በአገር ውስጥ የተፈናቀሉ ሰዎች**

በዓለም አቀፉ የስደተኞች ድርጅት (IOM) ግምት መሠረት ከሰኔ ጀምሮ 426,736 ሰዎች በአገር ውስጥ የተፈናቀሉ ሲሆን፤ ይህም ሰኔ ወር 2005 ዓ.ም. በነበረው ቁጥር ላይ የ51,091 ጭማሪ አሳይቷል፡፡ከድርጅቱ በተገኘው መረጃ መሠረት፤ በሀገር ውስጥ ከተፈናቀሉ ሰዎች 71.4 በመቶ የሚሆኑት ለረጅም ጊዜ ተፈናቅለው የቆዩ በመሆናቸው ወደ መኖሪያ ቀየ መመለስ፣ ከአካባቢው ማህበረሰብ ጋር መቀላቀል እና በሌሎች የአገሪቱ አካባቢዎችን ማስፈርን የመሳሰሉ ዘላቂ መፍትሔዎችን መስጠት በወቅቱ የሚቻል አልነበረም፡፡ ይህም በዋናነት ከግጭቶች አለመፈታት፣ የአስተዳደራዊ ውሳኔዎችን አለማሳለፍ ወይም ከአካባቢ ማህበረሰብ ጋር ለሚደረገው ቅልቅል የግብዓት አቅርቦት መጓደል፣ አልያም የሰፈራ ቦታዎች ተመራጭ አለመሆን ጋር የተያያዘ ነው፡፡

እነዚህ የሀገር ውስጥ የረጅም ጊዜ ተፈናቃዮች የጎሳና የድንበር ዘለል ግጭቶች ሰለባዎች (304,707)፣ የጎርፍ(1,477) እና የእሳተ ገሞራ(1,800) ክስተቶች ተፈናቃዮች በመባል ተከፋፍለዋል፡፡ 72 በመቶ የሚሆኑት (308,770) የሚሆኑት በሶማሌ ክልል የሚገኙ ሲሆን፤10.3 በመቶዎቹ (44,094) በኦሮሚያ፣ 9.7 በመቶዎቹ(41,489) በጋምቤላ፣1.1. በመቶዎቹ (4,580) በሐረር፣0.6 በመቶዎቹ (2,501) በደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/መ፣እንዲሁም 5.9 በመቶ(25፣302) የሚሆኑት በአፋር ክልል ይገኛሉ፡፡

በርካታ ቁጥር ያላቸው የሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች ለተራዘመ ጊዜ የሚቆዩ ነበሩ፡፡በቀረቡ ግምቶች መሠረት በሐምሌ ወር 2005 ዓ.ም. 3,500 አባወራዎች ከምሥራቅ ሐረርጌ፣በዚሁ ዓመት በየካቲት ወር 1,310 አባወራዎች ከምዕራብ ሐረርጌ የተፈናቀሉ ሲሆን፤በ2000 እና በ2001 ዓ.ም. እንደዚሁ ወደ 2000 የሚጠጉ አባወራዎች የድንበር ከተማ ከሆነችው ሞያሌ ተፈናቅለዋል፡፡ በ2001 ዓ.ም. ወደ 12,000 የሚጠጉ ለተራዘመ ጊዜ የሚቆዩ ተፈናቃዮች ግጭቶችን ሸሽተው በጋምቤላ ክልል ተጠግተው ቆይተዋል፡፡

ለተራዘመ ጊዜ የሚቆዩ ተፈናቃዮች ቁጥር በግጭትና በተፈጥሮ አደጋዎች ምክንያት ይጨምራል፡፡ በደቡብ ክልል በደቡባዊው ኦሞ ሸለቆ አካባቢ በተነሣ ግጭት 300 የሚሆኑ አባወራዎች ተፈናቅለዋል፡፡ በመጋቢት ወር በኦሮሚያ ክልል በጉጂና በቦረና ማህበረሰቦች

መካከል በተፈጠረ ግጭት ሳቢያ 120 ሰዎች ሲገደሉ፤ 30,700 የሚሆኑት ተፈናቅለው ነበር። በሚያዝያ ወር በሲቲ ዞን በአፋርና በሶማሌ ማህበረሰቦች መካከል በተፈጠረ ግጭት 900 አባወራዎች መፈናቀላቸውን፣መኖሪያ ቤቶችና ሌሎች መሠረተ ልማቶች መውደማቸውን ሪፖርቶች ጠቁመዋል። በመስከረም ወር አጋማሽ በመዠንግር ዞን በመዣንግ ብሔረሰብ ተወላጆችና ከአገሪቱ ደጋማ አካባቢዎች በመጡ ሰፋሪዎች መካከል በተነሣ ግጭት በትንሹ 600 አባወራዎች ተፈናቅለዋል። በተጨማሪም ከባድ ዝናብ ባስከተለው የጎርፍ መጥለቅለቅ ምክንያት በአፋር፣በጋምቤላ፣በደቡብና በሶማሌ ክልሎች የተፈናቀሉ ሰዎች ነበሩ።

ሳውዲ ዓረቢያ የውጭ ሀገር ሠራተኞችን በሚመለከት ባደረገቸው የህግ ለውጥ የተነሳ በዓመቱ ከህዳር አጋማሽ እስከ በመጋቢት  አጋማሽ ባለው ጊዜ፤በሀገሪቱ ውስጥ በስደት የነበሩ 163,018 ኢትዮጵያውያንን ባልተጠበቀ ሁኔታ አስወጥታለች። ከአገር የማስወጣት ዘመቻ የተጠናከረባቸው በህዳርና ታኅሣሥ ወራት በቀን 7,000 ኢትዮጵያውያን ወደ ሀገር ውስጥ ይገቡ ነበር። የሰብዓዊ እርዳታ ድርጅቶች ከመንግሥት ጋር በመተባበር ለተመላሾቹ የህክምና፣የውሃ፣የምግብና የመጓጓዣ አቅርቦት እገዛ አድርገዋል። መንግሥት ከሳውዲ ዓረቢያ መንግሥት ጋር ተቀራርቦ በመሥራት የተመላሾቹ ንብረት ከለላ እንዲደረግለትና በአግባቡ ወደ ሀገር ውስጥ እንዲገባ ሁኔታዎችን አመቻችቷል። ከመጋቢት ወር አጋማሽ ጀምሮ 94 በመቶ ለሚሆኑት ከስደት ተመላሾች የተለያየ ድጋፍ ተደርጎላቸዋል። በተጨማሪም መንግሥት ዜጎችን የመመለስ ሥራውን ለማቀላጠፍ የሙሉ ጊዜ ሠራተኞችን ከዓለም አቀፉ ማህበረሰብ ጋር በመተባበር በትራንዚት ጣቢያዎች መድቧል።

መንግሥት በአደጋ መከላከልና ምግብ ዋስትና ዘርፉ በኩል ለውስጥ ተፈናቃዮች ሰብዓዊ እርዳታ ማቅረቡን ቀጥሏል። የፌደራልና የየአካባቢው የአደጋ መከላከልና የምግብ ዋስትና ዘርፍ የሥራ ኃላፊዎች ከዓለም አቀፉ የስደተኞች ድርጅትና ከአጋሮቹ ጋር በመተባበር የውስጥ ተፈናቃዮችን ሁኔታ ሲከታተሉ ቆይተዋል። በተጨማሪም በሶማሌ ክልላዊ መንግሥት ደረጃ የክልሉ የአደጋ መከላከልና ዝግጁነት ቢሮ ከዓለም አቀፍ የስደተኞች ድርጅትና ከሌሎች ዓለም አቀፍ አካላት ጋር በመተባበር  ለረጅም ጊዜ የተፈናቀለው የቆዩ የውስጥ ተፈናቃዮችን ጉዳዮች የሚመለከት ዘላቂ መፍትሔ አምጭ ቡድን እንዲቋቋም አድርጓል።

### የስደተኞች ጥበቃ

__ጥገኝነት ስለማግኘት__፡- የአገሪቱ ሕግ ጥገኝነት መስጠት ወይም ስደተኞችን መቀበል እንደሚገባ ደንግጓል፤ መንግሥትም ለስደተኞች ጥበቃ ለማድረግ የሚያስችል ሥርዓት ዘርግቷል፡፡

በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የስደተኞች ጉዳይ ከፍተኛ ኮሚሽን ሪፖርት መሠረት፣ አገሪቱ እስከ ታህሳስ መጨረሻ ድረስ 644,168 ስደተኞችን ተቀብላ አስተናግዳለች፡፡ ከስደተኞቹ ውስጥ አብዛኛዎቹ ከደቡብ ሱዳን (248,580) የመጡ ሲሆን፣ ከሶማሊያ (244,066)፣ ከኤርትራ (111,321)፣ከሱዳን (35,606) እና ከሌሎች አገራት፣ በተለይም ከኬንያ (4,595) ነበሩ፡፡

በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የስደተኞች ጉዳይ ከፍተኛ ኮሚሽን፣ የስደተኞች እና ከስደት ተመላሾች ጉዳይ አስተዳደር መስሪያ ቤት እና የሰብዓዊ ረድኤት ድርጅቶች በሱዳን የብሉናይል ክፍለሀገር የሚካሄደውን ግጭት በመሸሽ ወደ ኢትዮጵያ ለገቡ የሱዳን ስደተኞች ድጋፍ ማድረጋቸውን ቀጥለዋል፡፡ በተጨማሪም ከደቡብ ሱዳን ጆንግሌይ ግዛት ለመጡ እና ጥገኝነት ለጠየቁ ደቡብ ሱዳናውያን መንግሥት ድጋፍ አድርጓል፡፡ በደቡብ ሱዳን በታህሳስ ወር 2006 ዓ.ም. በተነሳው የፖለቲካ ግጭት የተነሳ እስከ ታህሳስ ወር ድረስ ከ193,960 በላይ ስደተኞችበኢትዮጵ ጥገኝነት ጠይቀዋል፡፡

ኤርትራውያን ጥገኝነት ጠያቂዎች ወደ አገሪቱ መግባታቸውን ቀጥለዋል፡፡ ከነዚህም መካከል ብዙ ቁጥር ያላቸው ብቻቸውን የሚሰደዱ ታዳጊዎች ነበሩ፡፡ ብዙ ኤርትራዊያን በሱዳን እና በግብጽ በኩል አድርገው ወደ እስራኤል፣ አውሮፓ እና ሌሎች አገራት ለመጓዝ በማሰብ ለሁለተኛ ደረጃ ስደት አገራቸውን እየለቀቁ በየጊዘው ወደ ኢትዮጵያ ተሰደዋል፡፡

__ሥራ የመቀጠር ዕድል__፡- መንግሥት ለስደተኞች የሥራ ፈቃድ አልሰጠም፡፡

__የመሠረታዊ አገልግሎቶች ተደራሽነት__፡- የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የስደተኞች ጉዳይ ከፍተኛ ኮሚሽን፣ መንግሥታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች ጋር በመተባበር በመጠለያ ጣቢያዎች ውስጥ ላሉ ስደተኞች እንደ ጤና፣ ትምህርት፣ ውሃ፣ መጸዳጃ እና የግል ንጽህና አጠባበቅ ያሉ መሠረታዊ አገልግሎቶችን ሰጥተዋል፡፡ ከመጠለያ ጣቢያ ውጪ ያሉ ስደተኞችን በተመለከተም፣ መሠረታዊ አገልግሎቶችን በማግኘት ረገድ መድልዎ ስለመኖሩ የቀረቡ ሪፖርቶች አልነበሩም፡፡

<u>**ዘላቂ መፍትሔዎች**</u>፡- መንግሥት ከኤርትራ፣ ከሶማሊያ፣ ከደቡብ ሱዳን እና ከሱዳን የመጡ ጥገኝነት ጠያቂዎችን በስደተኝነት ተቀብሏል። ስደተኞች በቋሚነት ኢትዮጵያ ውስጥ እንዲኖሩ ቢፈቅድም፣ ዜግነት ማግኘት ወይም ከሕዝቡ መቀላቀል የሚችሉበትን ዕድል ግን አልሰጣቸውም። መንግሥት ኤርትራውያን ስደተኞች በገንዘብ ራሳቸውን እስከቻሉ ድረስ ከስደተኛ ካምፖች ውጪ እንዲኖሩ ፈቅዷል። መንግሥት የከፍተኛ ትምህርት ለሚከታተሉ ኤርትራውያን የተወሰነ ድጋፍ አድርጓል። እስከ ታኅሳስ ወር ድረስ 6,553 ስደተኞች [በሌሎች አገራት] ለመኖር ከአገሪቱ ወጥተዋል።

## ክፍል 3. የፖለቲካ መብት አከባበር፡- የዜጎች መንግሥታቸውን የመቀየር መብት

ዜጎች መንግሥታቸውን በሰላማዊ መንገድ የመቀየር መብት እንዳላቸው በሕገ መንግሥቱ እና በሕግ ተደንግጓል። ነገር ግን ገዢው ፓርቲ በምርጫ ረገድ ያለው የሰፋ ዕድል ይህንን መብት ገድቦታል።

### ምርጫ እና የፖለቲካ ተሳትፎ

<u>**በቅርቡ የተካሄዱ ምርጫዎች**</u>፡- ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ ነሐሴ 14 ቀን 2004፣ ከአረፉ በኋላ ገዢው ፓርቲ ኢሕአዴግ ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትሩን አቶ ኃይለማርያም ደሳለኝን የፓርቲው ሊቀመንበር በማድረግ የመለስን ቦታ ተክተው እንዲሠሩ የመረጣቸው ሲሆን፤ አስከትሎም የአገሪቱ ጠቅላይ ሚኒስትር እንዲሆኑ በእጩነት አቀረባቸው። ፓርላማው በመስከረም 2005 ኃይለማርያም ደሳለኝን የአገሪቱ ጠቅላይ ሚኒስትር አድርጎ መርጧል።

በ2002 በተካሄደው አገር አቀፍ የፓርላማ ምርጫ፣ ኢሕአዴግ እና አጋር ድርጅቶች ካሉት 547 መቀመጫዎች 545ቱን በማግኘት በተከታታይ ለአራተኛ የአምስት ዓመት የሥራ ዘመን በሥልጣን ላይ ለመቆየት አሸንፈዋል። መንግሥት ባስቀመጠው ገደብ ምክንያት የገለልተኛ ምርጫ ታዛቢዎች ተሳትፎ እጅግ በጣም ውሱን ነበር። ምንም እንኳ ምርጫዎቹን እንዲታዘቡ የተፈቀደላቸው በቁጥር አነስተኛ የሆኑ ዓለም አቀፍ ታዛቢዎች የድምፅ አሰጣጡ ቴክኒካዊ ገጽታዎች በብቃት ተከናውነዋል ብለው ቢደመድሙም፣አንዳንዶች ደግሞ ከምርጫው ዕለት አስቀድሞ ለነጻ እና ፍትኃዊ ምርጫ የተመቻቸ ሁኔታ እንዳልነበረ ጠቅሰዋል። ከ1997 አገራዊ ምርጫ ወዲህ በሥራ ላይ የዋሉ በርካታ ሕግጋት፣ መመሪያዎች እና የአሠራር ስርዓቶች በጠቅላላው የምርጫ ሒደት ለኢሕአዴግ ግልጽ የተጠቃሚነት ዕድሎችን ፈጥረውለታል። የተቃዋሚ ዕጩዎችን እና ደጋፊዎችን ማስፈራራትን ጨምሮ መንግሥት የተጠቀመባቸው

ኢ-ፍትኃዊ ስልቶች ምክንያት ኢሕአዴግ በከፍተኛ ልዩነት እንዲያሸንፍ አስተዋጽኦ ማድረጋቸውን የሚያረጋግጡ በርካታ ማስረጃዎች ነበሩ። በተጨማሪም፣ የመራጮች ትምህርት በድምፅ አሰጣጥ ቴክኒካዊ ሒደቶች ዙርያ መረጃ በመስጠት ላይ ብቻ የተገደበ ሲኾን፣ ይህም ትምህርት ከድምጽ መስጫው ዕለት ጥቂት ቀናት አስቀድሞ በብሔራዊ ምርጫ ቦርድ አማካይነት ብቻ እንዲሰጥ ተደርጓል።

ከድምጽ መስጫው ዕለት አንድ ሳምንት በፊት ታዛቢዎቹን የላከው የአፍሪካ ሕብረት ምርጫውን ነፃ እና ፍትኃዊ ሲል ገልጾታል። የተወሰኑ ታዛቢዎቹን ከድምጽ መስጫው ዕለት ጥቂት ወራት በፊት የላከው የአውሮፓ ሕብረት ምርጫው በግልጽነት ረገድ ዓለም አቀፍ ደረጃዎችን ያላሟላ እና ለተቃዋሚ ፓርቲዎች እኩል የመወዳደሪያ ሜዳ ያልነበረው ነው ሲል ደምድሟል። በአጠቃላይ የአውሮፓ ሕብረት ምርጫው "በፍርኃትና በሥጋት የተሞላ" እንደነበር፣ በተቃዋሚዎች የቀረቡት ማዋከብ እና ማስፈራራትን የተመለከቱ አቤቱታዎች ብዛት እና ተመሳሳይነትም "አሳሳቢ ጉዳይ" እንደሆነ በመጥቀስ "በአጠቃላይ የምርጫ ሒደቱ ግምገማ" ላይ እነዚህ ነጥቦች ከግምት መግባት አለባቸው ሲል አሳስቧል።

በ2005 ዓ.ም. የተደረጉ የአካባቢ እና የከተማ ምክር ቤቶች ምርጫዎችም የኢሕአዴግ የበላይነት መቀጠሉን አመልክተዋል። የኢሕአዴግ አጋር ፓርቲዎች ከ3.6 ሚሊዮን መቀመጫዎች ውስጥ ከ5 በስተቀር ሁሉንም ሲያሸንፉ፤ 33 ተቃዋሚ ፓርቲዎች ራሳቸውን ከምርጫው አግልለዋል።

<u>የፖለቲካ ፓርቲዎችና የፖለቲካ ተሳትፎ</u>፡- የፖለቲካ ፓርቲዎች በአብዛኛው ብሔርንመሠረትያደረጉ ናቸው። በገዢው ፓርቲ ኢሕአዴግ የሚመራው መንግሥት የመገናኛ ብዙኃን ነጻነትን ገድቧል፤ተቃዋሚ ፖለቲከኞችንም አስሯል። የኢሕአዴግ አባል ድርጅቶች ለአባሎቻቸው አንዳንድ ጥቅሞችን ያስገኛሉ፤ አባል ድርጅቶቹ በርካታ የንግድ ድርጅቶች ያሏቸው ሲሆን፣ የሥራ ዕድልና የንግድ ውሎችን ለታማኝ ደጋፊዎቻቸው እንደሚሰጡ በስፋት ተነግሯል። በርካታ ተቃዋሚ የፖለቲካ ፓርቲዎች የኢህአዴግ አባላት የቤቶች ወይም የሕንፃ ባለቤቶች ንብረታቸውን ለእነርሱ እንዳያከራዩ ጫና እንደሚፈጥሩ ወይም እንደሚያስፈራሯቸው በመጥቀስ ለቢሮ አገልግሎት የሚውሉ ቤቶች አልያም ሕንፃዎችን ለመከራየት መቸገራቸውን ተናግረዋል።

መምህራን እና ሌሎች የመንግሥት ሠራተኞች የተቃዋሚ ፖለቲካ ፓርቲዎች አባል ከሆኑ ከሥራ ይታገዱ እንደነበር የሚገልጹ ሪፖርቶች ቀርበዋል። የኦሮሚያ ክልላዊ መንግሥት

የተቃዋሚ ፓርቲ አባላትን፣ በተለይም መምህራንን፣ ከሥራ እንደሚያባርራቸው በመዛት ያስፈራራቸው እንደነበር የኦሮሞ ተቃዋሚ ፓርቲዎች ተናግረዋል። የመንግሥት ባለሥልጣናት በህጋዊ መንገድ የሚንቀሳቀሱ የኦሮሞ ተቃዋሚ ድርጅቶች በርካታ አባላት በምስጢር የኦሮሞ ነፃነት ግንባር አባላት ናቸው በማለት የሚከሰሱ ሲሆን፣ ከዚህ ይበልጥ ሰፋ ባለ ደረጃም የበርካታ ተቃዋሚ ፓርቲዎች አባላትን ከግንቦት 7 ጋር ግንኙነት አላቸው በማለት ይከስሳሉ። በዩኒቨርሲቲ ደረጃ የመድረክ እና የአባል ድርጅቶቹ አባላት የማስተማር ስራቸውን መስራት ችለዋል። የገዢው ፓርቲ አባላት ያልሆኑ ሥራ ፈላጊ የዩኒቨርሲቲ ምሩቃን፣ ሥራ መፈለጊያ የድጋፍ ደብዳቤ ከቀበሌያቸው እና ከአካባቢ አስተዳደር መዋቅሮች በቀላሉ እንደማያገኙ ሪፖርቶች ጠቁመዋል።

በምርጫ ቦርድ የተመዘገቡ የፖለቲካ ፓርቲዎች የአካባቢ ጽሕፈት ቤቶችን ለመክፈትና ለመጠቀም የግድ ከክልል መንግሥታት ፈቃድ ማግኘት አለባቸው።

<u>**የሴቶች እና የአናሳ ማኅበረሰቦች ተሳትፎ**</u>:- ሴቶች ወይም በሕዝብ ብዛት አናሳ የሆኑ ማህበረሰቦችን ድምጽ ከመስጠት አልያም ከወንዶች ወይም አናሳ ካልሆኑ ዜጎች እኩል በሆነ ደረጃ በፖለቲካ ከመሳተፍ የሚከለክሉ ሕጎች አልያም ባህላዊ ወይም ልማዳዊ ድርጊቶች ያልነበሩ ቢሆንም፤ ሴቶች በምርጫ ውድድርም ሆነ በሹመት የያዙት ቦታ እጅግ በጣም አነስተኛ ነበር። በመላ አገሪቱ ካሉ ምክር ቤቶች ከፍተኛ የሴቶች ቁጥር ያለው የትግራይ ክልል ምክር ቤት ነው። ከአባላቱ 48.5 በመቶ የሚሆኑ ሴቶች ናቸው።

በብሔር ላይ የተመሠረተው የመንግሥት የፌደራሊዝም ፖሊሲ በሀገሪቱ ያሉ ዋና ዋና ብሔረሰቦች በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ውስጥ የሚወከሉበትን አሠራር ፈጥሯል። በሀገሪቱ ከ80 በላይ ብሔረሰቦች ያሉ ሲሆን፣ አነስተኛ የሕዝብ ቁጥር ያላቸው ብሔረሰቦች በሕግ አውጭው ምክር ቤት ውክልና አልነበራቸውም። በ1999 በተደረገው የሕዝብ ቆጠራ መሠረት በስድስት ክልሎች (ትግራይ፣ አማራ፣ ቤኒሻንጉል-ጉሙዝ፣ ደቡብ ሕዝቦች፣ ጋምቤላ እና ሐረር) ውስጥ በፓርላማ መቀመጫ ለማግኘት የሚያበቃ የመራጭ ብዛት የሌላቸው 24 የብሔር ቡድኖች ነበሩ፤ ነገር ግን በ2002 በተካሄደው ምርጫ ከእነዚህ የብሔር ቡድኖች የታጩ ግለሰቦች በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ለሚገኙ 24 ልዩ መቀመጫዎች ተወዳድረዋል። በተጨማሪም እነዚሁ 24 የብሔር ቡድኖች እያንዳንዳቸው በፌዴሬሽን ምክር ቤት ውስጥ አንድ መቀመጫ አላቸው።

በፌዴራል መንግሥቱ ውስጥ ካሉ 22 የካቢኔ አባላት መካከል ሴቶች ሦስት ብቻ ሲሆኑ ፣ከሦስት የምክትል ጠቅላይ ሚኒስትሮች መካከል አንድ ሴት ይገኙበታል፡፡፣ በአገሪቱ ፓርላማ ካሉ 547 አባላት መካከልም 152ቱ ሴቶች ናቸው፡፡

## ክፍል 4. ሙስና እና በመንግሥት ውስጥ የግልጽነት አለመኖር

የአገሪቱ ሕግ በመንግሥት የሥራ ኃላፊዎች ለሚፈፀም ሙስና የወንጀል ቅጣት ደንግጓል፤ ምንም እንኳ መንግሥት በርካታ የሥራ ኃላፊዎችን ለፍርድ ቢያቀርብም፣ አንዳንድ ባለሥልጣናት የሙስና ተግባራት መፈፀማቸውን ቀጥለዋል፡፡ ሙስና፣ በተለይም ጉቦ መቀበል፣ በዝቅተኛ የመንግሥት መዋቅር የሥራ ኃላፊዎች ዘንድ ችግር ሆኖ ቆይቷል፡፡ በፖሊስ እና በፍርድ ቤት አካባቢ የሚፈፀም ሙስናም እንዲሁ ያልተቀረፈ ችግር ነው፡፡ አንዳንድ የመንግሥት ባለሥልጣናት መንግሥታዊ ድርጅቶችን ወደግል የማዛወር ሒደትን መጠቀሚያ ሲያደርጉት የሚታይ ሲኾን፣ የመንግሥት እና የፓርቲ የንግድ ድርጅቶች የመሬት ኪራይ (ሊዝ) እና ብድር በማግኘት ረገድ የቅድሚያ ተጠቃሚነት ዕድል ነበራቸው፡፡

<u>ሙስና፡-</u> ሙስናን መዋጋት የፍትህ ሚኒስቴር ኃላፊነት ሲሆን፤ ይህን የሚያደርገውም በዋነኛነት በፌደራል የሥነ-ምግባርና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን አማካኝነት ነው፡፡

ኮሚሽኑ በኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ዋና ዳይሬክተር፣ በምክትል ዳይሬክተሩ እንዲሁም በሌሎች የመንግሥት ባለስልጣናት እና ታዋቂ ነጋዴዎች ላይ የሙስና ወንጀሎችን ፈጽመዋል በሚል የመሠረተባቸው ክስ ሂደት ቀጥሏል፡፡ ጥር 2 ቀን 2006 ዓ.ም. የቀድሞው የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል ፕሬዚዳንት የሆኑት አቶ ያረጋል አይሸሹም በሥልጣን መባለግና በሙስና በተመሠረተባቸው ክስ የሰባት ዓመት እስራት እና የ20,000 ብር የገንዘብ መቀጮ ተጥሎባቸዋል፡፡

<u>ሀብትን ማሳወቅ፡-</u> ሕጉ ሁሉም የመንግሥት ባለሥልጣናት እና ሠራተኞች ሀብታቸውን እና የግል ንብረታቸውን በይፋ እንዲያስመዘግቡ ይጠይቃል፡፡ የአገሪቱ ፕሬዚዳንት እና ጠቅላይ ሚኒስትር ሀብታቸውን አስመዝግበዋል፡፡ በ2004 በወጣው የሀብት ማሳወቅና ምዝገባ አዋጅ መሠረት እስከ ሰኔ ወር 2006 ዓ.ም. ድረስ በግምት 80,000 የሚሆኑ የመንግሥት ባለሥልጣናትና ሠራተኞች ያላቸውን ሀብት አስመዝግበዋል፡፡

የሀብት መጠን የተመዘገበባቸው ሰነዶች በኮሚሽኑ ይዞታ ስር ይገኛሉ፡፡ በሕጉመሠረትእነዚህን ሰነዶች መመልከት የፈለገ ግለሰብ ጥያቄውን በጽሁፍ ማቅረብ ይችላል፡፡ ሆኖም የፌዴራል ስነምግባር እና ጸረ ሙስና ኮሚሽን እንዲገለጽ ካልፈለገ በቀር የቤተሰብን ንብረት የተመለከተ መረጃ ማግኘት አይቻልም፡፡ ይህንን ደንብ በማይፈጽሙ ላይ የገንዘብ እና በወንጀል የመጠየቅ ቅጣቶች በሕጉ ተካተዋል፡፡

<u>**መረጃን ለሕዝብ ተደራሽ ማድረግ፡-**</u> ህዝብ ስለ መንግሥት አሠራር መረጃዎችን የማግኘት መብት እንዳለው ሕጉ ቢደነግግም፣ የመረጃ ተደራሽነት በአብዛኛው ተገድቧል፡፡ ሕጉ መረጃ ይፋ የማይደረግባቸውን ጥቂት ሁኔታዎች ከነምክንያታቸው ይዘረዝራል፡፡ በአጠቃላይ የመረጃ ጥያቄ በጽሁፍ በቀረበ 30 ቀናት ውስጥ ምላሽ መሰጠት ያለበት ሲሆን፤ ክፍያውም ለጥያቄው ምላሽ በመስጠት ከሚወጣው ወጪ መብለጥ የለበትም፡፡ ሕጉን በማያከብሩ ባለስልጣናት ላይ ቅጣት ስለሚጣልባቸው ዘዴዎች እና የመረጃ መከልከልን ተከትሎ ይግባኝ የሚጠየቅባቸው ሁኔታዎች በሕጉ ተካተዋል፡፡ በዓመቱ ውስጥ መረጃ መስጠትን ወይም መከልከልን የተመለከተ መረጃ አልተገኘም፡፡

መንግሥት ሕግጋትና ደንቦች ሥራ ላይ ከመዋላቸው በፊት በነጋሪት ጋዜጣ እንዲታተሙ ያደርጋል፡፡ የመንግሥት ኮሙኒኬሽን ጉዳዮች ጽሕፈት ቤት ከመንግሥት፣ ከመገናኛ ብዙኃን እና ከሕዝብ ጋር የሚደረጉ ግንኙነቶችን ይመራል፡፡ የግሉ ፕሬስ አባላት ለሚያቀርቧቸው ጥያቄዎች መንግሥት ብዙ ጊዜ ምላሽ አይሰጥም በማለት ሪፖርት አድርገዋል፡፡

## ክፍል 5. በዓለም አቀፍ እና መንግሥታዊ ባልሆኑ አካላት የሚካሄድ የሰብዓዊ መብት ጥሰት ምርመራን በተመለከተ የመንግሥት አመለካከት

ምንም እንኳ በመንግሥት ከፍተኛ ገደብ ቢጣልባቸውም፣ በቁጥር አነስተኛ የሆኑ አገር በቀል የሰብዓዊ መብት ተሟጋች ድርጅቶች እንቅስቃሴ አድርገዋል፡፡ በአጠቃላይ መንግሥት አገር በቀል የሰብዓዊ መብት ድርጅቶችን እና ዓለም አቀፍ ታዛቢዎችን እንቅስቃሴ በጥርጣሬና በጥንቃቄ ተመልክቷል፡፡ በመንግሥት ቁጥጥር ሥር ያሉ መገናኛ ብዙኃን ሂዩማን ራይትስ ዎችን የመሳሰሉ ዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብት ድርጅቶችን የሚነቅፉ ዘገባዎችን አቅርበዋል፡፡

የበጎ-አድራጎት ድርጅቶች እና ማኅበራት አዋጅ፤ ከሚሰበስቡት የገንዘብ ድጋፍ ከ10 ከመቶ በላይ ከውጭ ምንጮች የሚያገኙ የበጎ አድራጎት ድርጅቶች፣ "ሶሳይቲዎች" እና ማኅበራት (መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች እና የሲቪል ማኅበረሰብ ደርጅቶች) ሰብዓዊ እና

ዴሞክራሲያዊ መብትን፣ የብሔር ብሔረሰቦች እኩልነትን፣ ሥርዓተ-ፆታን፣ ሃይማኖትን፤ የሕፃናት እና የአካል ጉዳተኞች መብቶችን፣ የግጭት አፈታት ወይም እርቅን፤ እንዲሁም የፍትህ አገልግሎት እና የሕግ አስፈፃሚ አካላት ብቃት ጉዳዮችን ለሚያራምድ ዓላማ መንቀሳቀስ የማይችሉ መሆኑን ደንግጓል። የሕጉ በሥራ ላይ መዋል መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ከሰብዓዊ መብቶች ጋር ተያያዥ በሆኑ ጉዳዮች ላይ የሚያደርጉትን እንቅስቃሴ በአስከፊ ሁኔታ የመገደብ አሉታዊ ውጤት ማሳደሩን ቀጥሏል። በሐምሌ ወር 2004 ዓ.ም.፣ የተባበሩት መንግሥታት የሰብአዊ መብቶች ከፍተኛ ኮሚሽነር፤ አዲሱ የበጎ አድራጎት ድርጅቶች እና ማኅበራት አዋጅ ከወጣ በኋላ የሲቪል ማኅበረሰቡ ምህዳር "በከፍተኛ ፍጥነት መጥበቡ" እንደሚያሳስበው ገልጿል። እስከ ታኅሣሥ ወር 2007 ዓ.ም. በዚሁ አዋጅ አማካይነት 3,056 መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች የተመዘገቡ ቢሆንም፤ከነዚህ መካከል ከሰብዓዊ መብቶች ጋር ተያያዥ በሆኑ ጉዳዮች ዙሪያ የሚንቀሳቀሱት አራቱ ብቻ ነበሩ።

አንዳንድ የሰብዓዊ መብት ተሟጋች ድርጅቶች ከገቢያቸው ከ10 በመቶ በላይ ከውጭ ለጋሾች ማሰባሰብ በማይችሉበት፣ ማለትም ተለይተው በተጠቀሱት ዘርፎች ለመንቀሳቀስ በሚያስችለው አገር-በቀል ማኅበርነት፣ አልያም ከገቢያቸው ከ10 በመቶ የበለጠውን ከውጭ ለጋሾች መሰብሰብ በሚፈቅደው፣ ነገር ግን ተለይተው በተጠቀሱት ዘርፎች መንቀሳቀስን በሚከለክለው በኢትዮጵያ ነዋሪ ማኅበርነት መመዝገብ ቀጥለዋል።

ሕጉን ሥራ ላይ ለማዋል ከወጡት በርካታ የማስፈፀሚያ ደንቦች አንዱ፣ የ70/30 ደንብ የሚባለው፣ ከአንድ ድርጅት የሥራ ማስኬጃ በጀት ውስጥ የአስተዳደራዊ ወጪን ጣሪያ በ30 በመቶ ገድቧል። ደንቡ የመምህራን፣ የግብርና እና የጤና ኤክስቴንሽን ሠራተኞች፣ እንዲሁም ሌሎች የመንግሥት የሥራ ኃላፊዎች ሥልጠናን እንደ "አስተዳደራዊ" ወጪ የሚፈርጅ ሲሆን፤ ለዚህም የሚያቀርበው መከራከሪያ፤ ሥልጠና በተጠቃሚዎች ላይ ቀጥተኛ ውጤት የለውም የሚል ነው። ይህም ሁኔታ ወደ ብዙ ሰዎች ለመድረስ የአሠልጣኞች-ሥልጠና ሞዴልን መጠቀም በሚመርጡ የልማት እርዳታ አጋሮች ሊሰጡ የሚችሉ የሥልጠና መርኃ-ግብሮችን ቁጥር ገድቧል። መንግሥት የዚህን ደንብ አፈፃፀም እንደየፕሮጀክቶች ባህሪ እና ተጨባጭ ሁኔታ በተናጠል እየገመገመ አስተናግዷል። በፌደራል ጉዳዮች ሚኒስቴር እና በለጋሽ አገራት ማኅበረሰብ ተወካይ በጋራ የሚመራ የሲቪል ማኅበረሰብ ዘርፍ የምክክር ቡድን በሕጉ አፈፃፀም

ሂደት የሚያጋጥሙ ተግዳሮቶችን ለመከታተልና በዚያም ዙሪያ ለመወያየት በየተወሰኑ ጊዜያት ስብሰባዎችን አካሄዷል።

መንግሥት አብዛኞቹ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች የፌደራል ማረሚያ ቤቶችን፣ ፖሊስ ጣቢያዎችን እና የፖለቲካ እስረኞችን እንዳይጎበኙ ከልክሏል። ህግ የተቀመጠው ክልከላ ከማይመለከታቸው እና በሰብዓዊ መብት ዙሪያ እንዲንቀሳቀሱ ከተፈቀደላቸው አራት ድርጅቶች ውስጥ አንዱ ታራሚዎቻችን ለመጎብኘት ተፈቀዶለታል። አንዳንድ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ታራሚዎች ምህረት የሚያገኙበትን ዕድል በማመቻቸት አዎንታዊ ሚና ተጫውተዋል።

መንግሥት የፀጥታ ችግር መኖሩን በመጥቀስ፤የሰብዓዊ መብት ድርጅቶች፣ መገናኛ ብዙሃን፣ የረድኤት ድርጅቶች እና የዲፕሎማቲክ ሚሲዮኖች ግጭት ወዳለባቸው አካባቢዎች እንዳይሄዱ ከልክሎ የነበረ ቢሆንም ክልከላዎቹ ቀንሰዋል። በተለይ በሶማሌ ክልል የሰብዓዊ ረድዔት አቅርቦት መሻሻል አሳይቷል። መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ችግር ወዳለባቸው አካባቢዎች በሚያደርጉት እንቅስቃሴ ዙሪያ መንግሥት የጠራ ፖሊሲ አልነበረውም። ይህም የክልል መንግሥት የሥራ ኃላፊዎችና ወታደራዊ መኮንኖች ወደ እነዚህ አካባቢዎች ለመግባት የሚቀርቡ ጥያቄዎችን ወደ ፌደራል መንግሥት እንዲመሩ አድርጓቸዋል። ጋዜጠኞች ግጭት ወዳለባቸው አካባቢዎች ከመግባታቸው በፊት እንዲመዘገቡ ይጠየቃሉ። የክልል ፖሊስ ወይም የአካባቢ ሚሊሽያዎች መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች አልፎ አልፎ በተለዩ ቦታዎች የሚያደርጉትን እንቅስቃሴ፣ የፀጥታ ችግርን እንደ ምክንያት በመጥቀስ፣ እንደገደቡ አንዳንድ ሪፖርቶች አመልክተዋል። አንዳንድ ኤጀንሲዎችም በጸጥታ ችግር የተነሳ የፕሮጀክት ሥራዎቻቸውን ውስን አድርገዋል።

አንዳንድ ሰዎች መንግሥታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች እና የሰብዓዊ መብት ጥሰቶችን ለመመርመር ከሚመጡ የውጭ መንግሥታት ተወካዮች ጋር ከተገናኙ ባለሥልጣናት የበቀል ርምጃ ይወስዱብናል የሚል ፍራቻ ነበረባቸው።

<u>የተባበሩት መንግሥታት እና ሌሎች ዓለምአቀፍ አካላት፡-</u> በተባበሩት መንግሥታት የማሰቃየት እና ሌሎች ጭካኔ የተሞላባቸው ኢሰብዓዊ ወይም አዋራጅ አያያዞች እና ቅጣቶችን የሚከታተሉ ልዩ ራፖርተር አገሪቱን ለመጎብኘት ያቀረቡት ጥያቄ ምላሽ አላገኘም።

**<u>የመንግሥት የሰብዓዊ መብት አካላት</u>**፡- የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብት ኮሚሽን የሰብዓዊ መብት ጥሰት አቤቱታዎችን በመመርመር ዓመታዊ እና ወቅታዊ ሪፖርቶችን አውጥቷል፡፡ ኮሚሽኑ ከ22 ዩኒቨርሲቲዎች እና ከሁለት የሲቪክ ማህበረሰብ ድርጅቶች ፤ እንዲሁም ከኢትጵያ የሕግ ባለሙያ ሴቶች ማኅበር እና ከኢትዮጵያ ክርስቲያን ጠበቆች ጋር በመተባበር 112 የሕግ ምክር የሚሰጡ ማዕከላትን አሳትፏል፡፡ ከዚህም ሌላ ኮሚሽኑ ከአክሱም፣ከወላይታ፣ከደብረ ብርሃንና ከጅጅጋ ዩኒቨርሲቲዎች ጋር የትብብር ስምምነት ተፈራርሟል፡፡

የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብት ኮሚሽን ለተወካዮች ምክር ቤት የ2006 ዓ.ም. ሪፖርት ባቀረበበት ወቅት በዓመቱ ከቀረቡለት 1,037 ከሰብዓዊ መብት ጥሰት ጋር ተያያዥ የሆኑ አቤቱታዎች 134ቱን ( ከጠቅላላው 13 በመቶ) መርምሮ ማጠናቀቁን ገልጿል፡፡ በተጨማሪም ኮሚሽኑ ለ463 ግለሰቦች የማማከር አገልግሎት ሰጥቻለሁ፤ 107 ጉዳዮችን በድርድር ፈትቻለሁ፤ 306 የሚሆኑ አቤቱታዎችን (ከጠቅላላው 30 በመቶ) ለሚመለከታቸው የመንግሥት አካላትመርቻለሁ ብሏል፡፡

የሕዝብ እንባ ጠባቂ ተቋም በአስፈጻሚው አካል ሥር ባሉ መሥሪያ ቤቶች ተፈጽመዋል የሚባሉ ከአስተዳደራዊ በደሎች ጋር የተያያዙ አቤቱታዎችን ተቀብሎ የመመርመር ሥልጣን አለው፡፡ ተቋሙ ከመስከረም 2003 እስከ መስከረም 2004 በአዲስ አበባ 2094 ያህል አቤቱታዎችን ተቀብሏል፡፡ ከእነዚህ ውስጥ በ784 አቤቱታዎች ላይ ምርመራ ያካሄደ ሲኾን፣ የተቀሩትን አቤቱታዎች በአማራጭ ዘዴዎች መፍትሄ እንዳስገኘላቸው ሪፖርት አድርጓል፡፡ አብዛኛዎቹ አቤቱታዎች ከማኅበራዊ ዋስትና፣ ከአሠሪና ሠራተኛ፣ እንዲሁም ከመኖሪያ ቤት እና ከንብረት-ነክ ውዝግቦች ጋር የተያያዙ ነበሩ፡፡ የእንባ ጠባቂ ተቋም አገር-አቀፍ መረጃ አላጠናቀረም፡፡

## ክፍል 6. አድልዎ፣ ማኅበራዊ ጥቃት እና ሕገ-ወጥ የሰዎች ዝውውር

ሕገ መንግሥቱ የዘር፣ የብሔር፣ የብሔረሰብ ወይም ሌላ ማኅበራዊ መሠረት፣ የቀለም፣ የፆታ፣ የቋንቋ፣ የሃይማኖት እና የፖለቲካ ወይም ሌላ አመለካከት፣ የንብረት፣ የልደት፣ ወይም የደረጃ ልዩነት ሳይደረግ ለሁሉም ሰዎች እኩል ጥበቃ እንደሚደረግ ይደነግጋል፡፡ ነገር ግን መንግሥት እነዚህን መብቶች በተሟላ ሁኔታ አላስከበራቸውም፤ ጥበቃም

አላደረገላቸውም። አካል ጉዳተኝነትን፣ ወሲባዊ ዝንባሌን ወይም ስርዓተ-ጾታዊ ማንነትን መሠረት አድርገው የሚፈጸሙ አድሎዎች በሕገመንግሥቱ አልተካተቱም።

**ሴቶች**

<u>አስገድዶ መድፈርና የቤት ውስጥ ጥቃት</u>፡- አስገድዶ መድፈር በሕግ የሚያስቀጣ ወንጀል ሲሆን፣ እንደ ወንጀሉ ክብደት ከ5 እስከ 20 ዓመት በሚደርስ እስራት ያስቀጣል። ሆኖም በትዳር ውስጥ የሚፈፀም አስገድዶ የመድፈር ድርጊትን ለመቆጣጠር በግልጽ የተቀመጠ ህግ የለም። መንግሥት ሕጉን በተሟላ ሁኔታ ተፈጻሚ አላደረገውም፤ የዚህም አንዱ ምክንያት ድርጊቱን ለሚመለከተው አካል ሪፖርት ያለማድረግ መጠነ-ሰፊ የሆነ ችግር ስላለ ነው። ይህን ወንጀል ከፈፀሙ ግለሰቦች መካከል ምን ያህሉ ክስ እንደተመሠረተባቸው፣ እንደተፈረደባቸው አልያም እንደተቀጡ የሚጠቁም መረጃ አልነበረም።

የቤት ውስጥ ጥቃት በህገ ወጥ ድርጊትነት ቢፈረጅም፤ መንግሥት አስገድዶ መድፈርንና የቤት ውስጥ ጥቃትን በሚመለከት ያሳየው የሕግ አፈፃፀም ወጥነት የጎደለው ነበር።

የቤት ውስጥ ጥቃት ሕገ-ወጥ ሆኖ ሳለ፣ በአስገድዶ መድፈር እና በቤት ውስጥ ጥቃት ላይ የተወሰደው የሕግ እርምጃ ወጥነት የጎደለው ነበር። ወንጀል ፈጻሚዎቹ እንዳደረሱት ጉዳት አስከፊነት፣ ከአነስተኛ የገንዘብ መቀጮ ጀምሮ ከ10 እስከ 15 ዓመት በሚደርስ እስራት ይቀጣሉ።

ምንም እንኳ ሴቶች ለፖሊስና ለፍርድ ቤቶች በማመልከት የሕግ ከለላ ማግኘት ቢችሉም፣ በተለይ በገጠር አካባቢዎች ያለው ማኅበረሰብ አመለካከት እና የመሠረተ ልማት አለመስፋፋት ብዙ ሴቶች ጉዳያቸውን ወደ ሕግ እንዳይወስዱ ገድቧቸዋል። በዚህ ረገድ መንግሥት ክስ የመሠረተባቸው አጥፊዎች ቁጥር ውሱን ነበር።

የቤት ውስጥ ጥቃት እና የአስገድዶ መድፈር ክሶች ብዙ ጊዜ ከመንተታቸውም ሌላ ቅድሚያ አልተሰጣቸውም። ጾታን መሠረት ካደረገ ጥቃት አኳያ በፍትህ ሥርዓቱ ውስጥ ከፍተኛ ክፍተት መታየቱ ቀጥሏል፤ የዚህም ምክንያት ደካማ የመረጃ አያያዝ እና ምርመራ ነበር። በሴቶች እና በወጣት ሴቶች ላይ ጾታን መሠረት ያደረገ ጥቃት ተፈጽሟል፤ ነገር ግን ከባህላዊ

ተቀባይነት፣ ከኃፍረት፣ ከፍርሃት ወይም የሕግ ጥበቃ እንዳለ ካለማወቅ የተነሳ ጥቃቶቹ ሪፖርት አልተደረጉም።

በተለይ ሕፃናት እና ሴቶች ላይ የተፈፀሙ የጥቃት ወንጀሎችን ለመዳኘት "ለሕፃናት ተስማሚ" የሆኑ ችሎቶች ተቋቁመዋል። የፖሊስ አባላት በሀገር በቀል መንግሥታዊ ያልሆኑ ደርጅቶች እና በሴቶች፣ሕጻናትና ወጣቶች ጉዳይ ሚኒስቴር አማካኝነት የቤት ውስጥ ጥቃትን በተመለከተ ሥልጠና እንዲወስዱ ተደርጓል። በኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብት ኮሚሽን ውስጥም የሴቶችና የሕፃናት መብቶቸ ኮሚሽነር ጽ/ቤት ነበር።

<u>**የሴት ልጅ ግርዛት**</u>፦ የሴት ልጅ ግርዛት ሕገ-ወጥ ተግባር ቢሆንም፣ መንግሥት ይህንን ድርጊት ለመከላከል አልያም የድርጊቱን ፈጻሚዎች ለመቅጣት ጠንካራ እንቅስቃሴ አላደረገም። መንግሥት ችግሩን ለመቅረፍ የተከተለው መንገድ ቅጣት ከመጣል ይልቅ ኅብረተሰቡን በማስተማር ላይ ያተኮረ ነው። ይህንን መንገድ ከሚከተሉ ሀገራት በተገኘ ጥናት ድርጊቱ በምስጢር እንዲስፋፋ በር ይከፍታል ከሚል ድምዳሜ ላይ ተደርሷል። (ክፍል 6፣ህፃናት ሥር ይመልከቱ)።

<u>**ሎሎች ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች**</u>፦ በስፋት የተፈፀሙት ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች የሴት ልጅ ግርዛት ፣ግግ ማስቧጠጥ፣ እንጥል መቁረጥ፣ የወተት ጥርስ መንቀል፣ ያለዕድሜ ጋብቻ እና በጠለፋ ማግባት ነበሩ።

በጠለፋ ማግባት ሕገ-ወጥ ድርጊት ቢሆንም፣ መንግሥትም ጠለፋን ለማስቀረት ሙከራዎች ቢያደርግም፣ ድርጊቱ በአንዳንድ ክልሎች እንደቀጠለ ነበር። "ፖፑሌሽን ካውንስል" በ 2002 ዓ.ም. በሰባት ክልሎች ላይ ባደረገው ጥናት 2.6 በመቶ የሚሆኑት ወጣት ሴት ባለትዳሮች ጋብቻ የፈጸሙት በጠለፋ እንደሆነ ተናግረዋል። ጥናቱ እንደሚያሳየው በደ.ብ.ብ.ሕ.ክ 12.9 በመቶ፣ በኦሮሚያ 4.4 በመቶ፣ በአፋር 3 በመቶ እንዲሁም በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል ከ1 በመቶ የማይበልጡ ሴቶች ወደ ትዳር የገቡት በጠለፋ ነው። የጋምቤላ እና ሶማሌ ክልሎች በጥናቱ አልተካተቱም። በጠለፋ አማካኝነት የሚከናወኑ አብዛኛዎቹ ጋብቻዎች በኃይል የሚፈፀሙ ወሲባዊ ግንኙነቶችን ያካተቱ ነበሩ፤ በአብዛኛው ጠለፋ በሚከናወንበት ጊዜ ሴቶች አካላዊ ጥቃት ይደርስባቸዋል። የጠለፋ ድርጊቶች በቤተሰቦች፣ በማኅበረሰቦች እና በጎሳ ቡድኖች መካከል ግጭቶችን ይቀሰቅሳሉ። ጠለፋን መሠረት ባደረገ ጋብቻ ተጎጂዋ ከጠላፊዋ ጋር ለመጋባት ከተስማማች ጠላፊው አይቀጣም።

<u>ወሲባዊ ትንኮሳ</u>፡- ወሲባዊ ትንኮሳ በስፋት ተስተውሏል፡፡ የወንጀል ሕጉ ድርጊቱን በሚፈፅሙ ላይ ከ18 እስከ 24 ወራት የሚደርስ የእስራት ቅጣት ይጥላል፡፡ ነገር ግን፣ ባለሥልጣናት ከትንኮሳ ጋር የተያያዙ ሕጎችን ተፈጻሚ አላደረጉም፡፡

<u>የሥነ-ተዋልዶ መብቶች</u>፡- ግለሰቦች እና ጥንዶች የልጆቻቸውን ብዛት፣ ምን ያህል አራርቀው መውለድ እንደሚኖርባቸው እና የሚወልዱበትን ጊዜ በነፃነት እና በኃላፊነት ስሜት የመወሰን እና ከአድልዎ፣ ከማስገደድ እና ከአመጽ ነፃ በሆነ መንፈስ ይህንኑ ለማድረግ የሚያስችል መረጃ እና ዘዴዎቹን የማወቅ መብት አላቸው፡፡ መንግሥት በመላ ሀገሪቱ የሥነ ተዋልዶ መብቶችን ደግፏል፤ለሥነ ተዋልዶ ጤና አገልግሎቶች ፍትሐዊ ተደራሽነትም ጠንክሮ ሠርቷል፡፡ የኦርቶዶክስና የእስልምና ሃይማኖቶች መሪዎች፣ እንደ አስፈላጊነቱ የቤተሰብ ዕቅድ አግልግሎትን ጨምሮ፣ ተከታዮቻቸው እነዚህን የጤና አገልግሎቶች እንዲጠቀሙ አበረታትተዋል፡፡ በዓመቱ የወሊድ መከላከያ ስርጭትን፣ አጠቃላይ የወላድነት አማካይን፣ የእናቶች ጤናና የአመጋገብ ሥርዓትን በተገቢው ሁኔታ ለመገንዘብ የሚረዳ አነስተኛ የሥነ ሕዝብና የጤና ዳሰሳ ጥናት ተካሂዶ ነበር፡፡ ጥናቱ እንዳመለከተው ከሆነ በአገር አቀፍ ደረጃ 40 በመቶ የሚሆኑ ያገቡ ሴቶች ዘመናዊ የወሊድ መቆጣጠሪያዎችን ይጠቀማሉ፡፡ ይህም ጥናቱ ከመካሄዱ ከሦስት ዓመታት በፊት ከነበረበት 27 በመቶ አማካይ የተገኘ ዕድገት ነው፡፡ ይኸው ጥናት ጨምሮ እንዳመለከተውም በወሊድ ወቅት በሠለጠኑ አዋላጆች የመገልገል ልማድ ከ10 በመቶ ወደ 16 በመቶ ከፍ ብሏል፡፡ መንግሥት ከተባበሩት መንግሥታት ኤጀንሲዎችና ከጌትስ ፋውንዴሽን ባገኘው ድጋፍ ሠርቶ ባጠናቀቀው ሞዴል፤ የእናቶች ሞት መጠን ከ10,000 ወላዶች 676 ከነበረበት ወደ 420 ዝቅ ማድረጉንና ከ1982 ዓ.ም. ወዲህ የእናቶች ሞትን በ70 በመቶ በመቀነስ የሚሊኒየሙን የልማት ግብ አሳክቷል፡፡ ጽንስ ማቋረጥ ሕገ-ወጥ ድርጊት ቢሆንም፤ በርካታ ያላካተታቸው ሁኔታዎች ነበሩ፡፡ ሕገ-ወጥና ጥንቃቄ በጎደለው አኳኋን ጽንስ በማስወረድ ዙሪያ ከተደረገው የሕግ ለውጥ ወዲህ፤ለበርካታ እናቶች ሞት መንስኤ ይሆን የነበረው ይህ ድርጊት መቀነሱ ተስተውሏል፡፡ በሁሉም የመንግሥት የጤና ተቋማት የእናቶችና የህፃናት ጤና አገልግሎቶች በነፃ የሚሰጡ ቢሆንም፤ራቅ ባሉ ያሀገሪቱ አካባቢዎች በሚያጋጥመው የመጓጓዣ ችግር የተነሣ አሁንም ጥራት ያለው አገልግሎት ተደራሽነት ሊረጋገጥ አልቻለም፡፡

<u>መድልዎ</u>፡- በሴቶች ላይ የሚፈፀም መድልዎ በግምት 85 ከመቶ ያህል የአገሪቱ ሕዝብ በሚኖርበት የገጠሩ ክፍል የጎላ ነበር፡፡ ሕጉም ቢሆን መድልዎን የሚያንፀባርቁ ደንቦችን

አካቷል። ባልን ሕጋዊ የቤተሰብ መሪ አድርጎ እውቅና መስጠቱ፣ እንዲሁም ዕድሜያቸው ከአምስት ዓመት በላይ ለሆኑ ሕፃናት ብቸኛ ሞግዚት ወይም አሳዳጊ አድርጎ መሰየሙ ለአብነት ይጠቀሳሉ። ፍርድ ቤቶች የቤት ውስጥ ጥቃትን ፍች ለማጽደቅ በቂ ምክንያት አድርገው አላዩም። የቱንም ያህል ረጅም ዓመታት ያስቆጠረ ትዳር ቢሆን፣ ብዙ ልጆች ቢወልዱም፣ በርካታ ንብረቶችን በጋራ ቢያፈሩም፣ ትዳር የሚፈርስበት ሁኔታ ከተፈጠረ ሕጉ ለሴቶች ያስቀመጠው ለሦስት ወራት ብቻ የገንዘብ ድጋፍ የማግኘት መብትን ነው። በልማዳዊ ሕግ ለተፈፀመ ጋብቻ የሚሰጠው የሕግ ዕውቅና ውሱን ነበር። ልማዳዊ ሕግ ባል ለቤተሰቡ የገንዘብ ድጋፍ እንዲያደርግ የሚያስገድደው የሕግ አግባብ ስለሌለው ሴቶችና ሕፃናት አንዳንዴ ችግር ላይ የወደቁበት ሁኔታ ተፈጥሯል። ባህላዊ ፍርድ ቤቶች ኢኮኖሚያዊ እና ማህበራዊ ግንኙነቶችን በተመለከተ ባህላዊ ሕጎችን መተግበር ቀጥለዋል።

ሕገ-መንግሥቱ መሬት የመንግሥት እንደሆነ ደንግጓል። ወንዶችም ሆኑ ሴቶች በውርስ ሊያስተላልፉ የሚችሉት በመሬት የመጠቀም መብት አሏቸው። የመሬት ሕግ ከክልል ክልል ይለያያል። ሁሉም የፌደራል እና የክልል የመሬት ሕጎች ሴቶች የመንግሥት መሬት ማግኘት እንዲችሉ ሁኔታዎችን አመቻችተዋል። የውርስ ሕጎችም ባሎቻቸው የሞቱባቸው ሴቶች በትዳር አብረው ሲኖሩ ያፈሩትን የጋራ ንብረት መውረስ እንደሚችሉ ደንግገዋል።

በከተሞች አካባቢ ሴቶች ሥራ የማግኘት ዕድላቸው ከወንዶች አንፃር አናሳ ሲሆን፣ ባሉት የሥራ ዘርፎችም ለተመሳሳይ ሥራዎች ተመሳሳይ ክፍያ አይሰጣቸውም ነበር። በተጨማሪም ባለው ልማዳዊ አስተሳሰብ ወይም አመለካከት የተነሳ ሴቶች የትምህርት ደረጃቸው ዝቅተኛ በመሆኑ በጥሩ ደመወዝ እንዳይቀጠሩ፣ ብድር እንዳያገኙና የራሳቸውን የንግድ ሥራ እንዳይሰሩ ወይም እንዳይመሩ ተገድበዋል።

የትምህርት ሚኒስቴር እንዳመለከተው፣ በመጀመሪያ ዲግሪ እና በድህረ-ምረቃ ትምህርት የሴቶች ተሳትፎ እያደገ የመሄድ ዝንባሌውን በመቀጠል በ2003/04 የትምህርት ዘመን ከነበረበት 144,286፣ በ2004/05 የትምህርት ዘመን ወደ 172,237 አድጓል።

**ሕፃናት**

**<u>የልደት ምዝገባ</u>፡-** ሕጻናት ዜግነታቸውን የሚያገኙት ከወላጆቻቸው ነው። ሁሉም ሕፃናት ሲወለዱ መመዝገብ እንዳለባቸው ሕጉ ይደነግጋል። በሆስፒታል የተወለዱ ሕፃናት ሲመዘገቡ፣

ከሆስፒታል ውጪ የተወለዱ አብዛኞቹ ሕፃናት ግን አልተመዘገቡም፡፡ ብዙዎቹ ሕፃናት በተለይ በገጠር አካባቢ የሚወለዱት በመኖሪያ ቤት ውስጥ ነበር፡፡

**ትምህርት፡-** በፖሊሲ ደረጃ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ዕድሜያቸው ለትምህርት ለደረሱ ሕፃናት በነፃ እንደሚሰጥ ተደንግጓል፡፡ ሆኖም ግን የአገሪቱን ወጣቶች ተቀብለው የሚያስተምሩ በቂ ትምህርት ቤቶች በተለይ በገጠር አካባቢዎች አልነበሩም፡፡ ለትምህርት ቤት የሚያስፈልጉ ቁሳቁሶች ዋጋ ከፍተኛ በመሆኑ ብዙ ቤተሰቦች ልጆቻቸውን ወደ ትምህርት ቤት እንዳይልኩ መሰናክል ሆኗል፡፡ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ግዴታ እንደሆነ የሚደነግግ ሕግም አልነበረም፡፡ ትምህርት ለመከታተል የተመዘገቡ ተማሪዎች ቁጥር ከሰለጠኑ መምህራን ቁጥር በላይ በከፍተኛ ፍጥነት አድጓል፡፡ የመንግሥት አካላትን፣ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችንና ለጋሾችን በማቀናጀት መንግሥት በ2001 ዓ.ም. 5,322 የመጀመሪያ ደረጃና 715 ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶችን አሠርቷል፡፡

**በሕፃናት ላይ የሚፈጸም ጥቃት፡-** በሕፃናት ላይ የሚፈጸም ጥቃት በስፋት ተስተውሏል፡፡ የአፍሪካ ሕፃናት ፖሊሲ መድረክ በ2005 ዓ.ም. ያካሄደው ጥናት እንደሚያሳየው፤ በሕፃናት ላይ ወሲባዊ ጥቃቶችን የሚፈጽሙ ጥፋተኞች ላይ በመንግሥት የሚመሠረቱ ክሶች ጨምረዋል፡፡ ለሕፃናት ምቹ የሆኑ በተለይም በሕፃናት እና በሴቶች ላይ የሚደርሰውን ጥቃት የሚዳኙ ችሎቶች ተቋቁመዋል፡፡ በኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብት ኮሚሽን የሴቶች እና ሕጻናት ጉዳዮች ኮሚሽነር ጽ/ቤት ተቋቁሟል፡፡

**ያለዕድሜና የግዳጅ ጋብቻ፡-** ሕጋዊ ጋብቻ ለመፈፀም ወንዶችና ሴቶች ዕድሜያቸው 18 ዓመት መድረስ እንደሚገባው ሕጉ ይደነግጋል፣ ይሁን እንጂ ህጉ ወጥነት ባለው ሁኔታ ተግባራዊ አልተደረገም፡፡ አንዳንድ በገጠር የሚገኙ ቤተሰቦች ህጉ ስለመኖሩ ግንዛቤ አልነበራቸውም፡፡ በበርካታ ክልሎች በዕድሜ የገፉ ወንዶች ወጣት ሴቶችን የማግባት ሁኔታ ያለ ሲሆን፤በዚህ ልማዳዊ ድርጊት ላይም ከፍተኛ ተቃውሞና ትችት እንደቀጠለ ነው፡፡ መንግሥት ያለዕድሜ ጋብቻ ችግርን ለመቅረፍ ጥፋተኞችን ከመቅጣት ይልቅ በማስተማርና በሽምግልና ነገሮችን በመፍታት ላይ አተኩሯል፡፡

በ2003ቱ የሥነ-ሕዝብና ጤና ጥናትመሠረትዕድሜያቸው ከ 20-49 የሆኑ ሴቶች አማካይ የመጀመሪያ ጋብቻ የሚፈጽሙበት ዕድሜ 17.1 ዓመት ነበር፡፡ የመጀመሪያ ጋብቻ የሚፈጸምበት ዕድሜ ከፍ እያለ መጥቷል፡፡ ዕድሜያቸው ከ20-24 በሆኑ ሴቶች ላይ በ1998

በተደረገው ጥናት አማካይ የመጀመሪያ ጋብቻ የሚፈጸምበት ዕድሜ 16.5 ሲሆን፤ በጥናቱ ከተካተቱና ዕድሜያቸው ከ45-49 ከሆኑ ሴቶች መካከል 39 በመቶ የሚሆኑት በ15 ዓመታቸው ጋብቻ ፈጽመዋል። ዕድሜያቸው ከ15-19 ከሆኑ ወጣት ሴቶች መካከል 8 በመቶ ያህሉ ብቻ አግብተዋል።

ለአቅመ ሄዋን ያልደረሱ ሕፃናት በተለይ በአማራና ትግራይ ክልሎች በሰባት ዓመታቸው ሳይቀር ጋብቻ ፈጽመዋል። የሕፃናት ጋብቻ በአማራ ክልል በስፋት የሚስተዋል ሲሆን ፤ በክልሉ በተደረገ የሥነ-ሕዝብና ጤና ጥናት በ1997 ዓ.ም 14.7 ዓመት የነበረው አማካይ የመጀመሪያ ጋብቻ የሚፈጸምበት ዕድሜ በ 2003 ወደ 15.1 ዓመት ከፍ ብላዕል። የአማራ እና በመጠኑም ቢሆን የትግራይ ክልላዊ መንግሥታት ካለዕድሜ ጋብቻ ጋር ተያይዘው በሚያጋጥሙ ችግሮች ላይ ወጣት ሴቶችን ለማስተማር ሞክረዋል።

<u>የሴት ልጅ ግርዛት</u>፡- የሴት ልጅ ግርዛት/ብልት ትልተላ ሕገ-ወጥ መሆኑ ቢደነገግም፤ መንግሥት ሕጉን አላስፈፀመም፤ ጥፋተኞችንም አልቀጣም። በ2001 ዓ.ም. የተደረገው የ"ፖፑሌሽን ካውንስል" ጥናት ግርዛት እንደቀነሰ ቢያመለክትም፤ አብዛኛዎቹ ወጣት ሴቶች በአንድ ወይም በሌላ መንገድ ለግርዛት ተዳርገዋል። በጥናቱ ከተሳተፉ ሴቶች መካከል ዕድሜያቸው ከ21 እስከ 24 ከሆኑት ውስጥ 66 በመቶው ግርዛት እንደተፈጸመባቸው የገለጹ ሲሆን፤ ዕድሜያቸው ከ15 እሰከ 17 ከሆኑት ውስጥ ግን 56 በመቶው ተመሳሳይ ድርጊት ተፈጽሞባቸዋል። ጥናቱ ከዳሰሳቸው ሰባት ክልሎች እጅግ ከፍተኛ የግርዛት መጠን የታየው በአፋር (90.3 በመቶ)፣ በኦሮሚያ (77.4 በመቶ)፣ እንዲሁም በደ.ብ.ብ.ሕ.ክ. (74.6 በመቶ) ነው።

ከጠቅላላው ሕዝብ 15 በመቶ ያህሉ በሚኖርበት የከተማ አካባቢ የግርዛት ድርጊት በጣም አነስተኛ ነበር። ወጣት ሴቶች በተወለዱ በሰባት ቀናቸው በተለይ "ቂንጥር" የሚባለውን የብልታቸውን ክፍል በግርዛት ሳቢያ እንዲያጡ ተደርጓል። ለአቅመ ሔዋን ሲደርሱ ደግሞ እጅግ አደገኛ የሆነው የብልት መሰፋት ተፈጽሞባቸዋል። የወንጀለኛ መቅጫ ሕጉ "ቂንጥር" የተባለውን የብልት ክፍል በመቁረጥ ግርዛት በሚፈጽሙ ባህላዊ ገራዥች ላይ ቢያንስ የሦስት ወር እስራት፣ ወይም የ500 ብር (25 የአሜሪካ ዶላር) የገንዘብ መቀጮ ይጥላል። እጅግ አደገኛ በሆነ ሁኔታ ግርዛት የሚያከናውኑትን ደግሞ ከአምስት እስከ አስር ዓመት በሚደርስ እስራት ይቀጣል። ነገር ግን የሴት ልጅ ግርዛትን በተመለከተ አንድም ክስ አልቀረበም። መንግሥት የሴት ልጅ ግርዛትን ለማስቀም በመንግሥት ትምህርት ቤቶች፣ በጤና ኤክስቴንሽን መርሃ

ግብሮች እና በመገናኛ ብዙኃን ትምህርት ሰጥቷል። መንግሥት የመረጠውን ግንዛቤ የመፍጠርና ቅጣት ያለመጣል መንገድ በመከተል ዓለም አቀፍ ለጋሾችና የግል ድርጅቶች ማኅበረሰቡን በማስተማር የሴት ልጅ ግርዛትን ለመቀነስ ንቁ ተሳትፎ አድርገዋል።

**ሌሎች ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች**:- በወጣት ሴቶች ላይ የሚፈጸም ማኅበራዊ ጥቃት አስቸጋሪነቱ እንደቀጠለ ነው። የሴት ልጅ ግርዛት፣ ያለዕድሜ ጋብቻ፣ በጠለፋ ማግባት፣ የምግብና የሥራ ክልከላዎች በወጣት ሴቶች ላይ ከሚፈጸሙ ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች መካከል ጥቂቶቹ ነበሩ።

**የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ**:- በፈቃደኝነት ወሲባዊ ግንኙነት ለመፈፀም ዝቅተኛው የዕድሜ ገደብ 18 ዓመት ቢሆንም፣ ባለስልጣናት ሕጉን ተፈጻሚ አላደረጉም። ለአቅመ አዳም/ሄዋን ካልደረሰ/ች ህፃን ጋር ወሲባዊ ግንኙነት መፈጸም ከ3 እስከ 15 ዓመት የሚደርስ ቅጣት እንደሚያስከትል በሕግ ተደንግጓል። ለአቅመ አዳም/ሔዋን ባልደረሱ ሕፃናት ላይ አስጸያፊ ወሲባዊ ደርጊት ሲፈፀም የሚያሳዩ ምስሎችን ያሰራጨ ሰው በአንድ ዓመት እስራትና በ10,000 ብር (500 የአሜሪካን ዶላር) የገንዘብ መቀጮ እንደሚቀጣ ተደንግጓል። በተጨማሪም ሕጉ ትርፍ ለማግኘት ሲባል ለአቅመ-አዳም/ሄዋን ያልደረሱ ሕፃናትን ለወሲብ ድርጊት ማሰማራትና የወሲብ ንግድ እንዲጀምሩ መገፋፋትን ይከለክላል። ነገር ግን የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ፣ በተለይ በከተሞች አካባቢ ቀጥሎ ነበር።ዕድሜያቸው 11 ዓመት የሆኑ ወጣት ሴቶች ለወሲብ ንግድ እንዲሰማሩ መመልመላቸው ተነግሯል። ከእነዚህ ወጣት ሴቶች ጋር ግብረ ሥጋ ግንኙነት ለመፈጸም የሚፈልጉት ወጣት ሴቶቹ በግብረ ሥጋ ግንኙነት ከሚተላለፉ በሽታዎች ነፃ ናቸው የሚል እምነት ስለነበራቸው ነበር። ወጣት ሴቶች በሆቴሎች፣ ቡና ቤቶች፣ በመዝናኛ ስፍራዎች እና ገጠር በሚገኙ የከባድ መኪና ማቆሚያ ጣቢያዎች በወሲብ ንግድ ተበዝብዘዋል። አንዳንድ ወጣት ሴቶች በራሳቸው ቤተሰቦች ተገፋፍተው ወደ ወሲብ ንግድ እንደገቡ ሪፖርቶች አመልክተዋል።

**ሕፃናትን ወይም የአካል ጉዳት ያለባቸውን ሕጻናት መግደል**:- በኂላ ቀር አስተሳሰብ እና ባዕድ አምልኮ ምክንያት ሕፃናትን መግደል በደቡብ ኦሞ ሸለቆ አካባቢ ባሉ ጎሳዎች መተግበሩ ቀጥሏል። የአካባቢ መስተዳድሮች ማኅበረሰቡን በማስተማር ድርጊቱን ለማስቆም ጥረት አድርገዋል።

**የተፈናቀሉ ሕፃናት**:- የሠራተኛና ማኅበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር የ2002 ሪፖርት እንደሚያመለክተው፣ በግምት 150,000 ሕፃናት በጎዳና ላይ የሚኖሩ ሲሆን፣ ከእነዚህ ውስጥ

60,000 የሚሆኑት በዋና ከተማዋ ይገኛሉ። እንደ ሚኒስቴሩ ሪፖርት ከሆነ በወላጆች ህመም እንዲሁም በቤተሰብ የገቢ አነስተኛነት ምክንያት ቤተሰቦች ልጆቻቸውን መርዳት አለመቻላቸው ችግሩን አባብሶታል። እነዚህ ሕፃናት በቡድን ሆነው ይለምናሉ፤ ወይም መደበኛ ያልሆነ ሥራ ይሠራሉ።

በ2002 "ፖፑሌሽን ካውንስል ያንግ አደልትስ" (Population Council Young Adults) ባደረገው ጥናት በጎዳና ላይ ከሚኖሩና ከሚሰሩ ወንዶች ልጆች መካከል 82.3 በመቶ የሚሆኑት ትምህርት ይማሩ ነበር ወይንም ለመማር ተመዝግበዋል። 26.4 በመቶው ከወላጆቻቸው አንዱን ያጡ ሲሆን፤47.2 በመቶ የሚሆኑት ሁለቱንም ወላጆቻቸውን ያጡ ናቸው። 72 በመቶ የሚሆኑት በሕይወታቸው በአንድ ወቅት በክፍያ ሥራ ላይ ተሰማርተዋል። በጎዳና ላይ ያሉ ሕፃናት ቁጥር ብዙ ከመሆኑ የተነሳ ወላጅ አልባ ሕፃናትን የሚንከባከቡ መንግሥታዊና የግል ድርጅቶች ድጋፍ ማድረግ አልቻሉም።

**<u>በተቋማት የሚረዱ ሕፃናት</u>፡-** በተባበሩት መንግሥታ የሕፃናት ፈንድ የ2004 ሪፖርት መሠረት በሀገሪቱ ውስጥ በግምት 4.5 ሚሊዮን ወላጅ አልባ ሕፃናት ይገኛሉ። አብዛኛዎቹ ከዘመዶቻቸው ጋር የሚኖሩ ነበሩ። በመንግሥት የሚተዳደሩ የወላጅ አልባ ሕፃናት ማሳደጊያ ተቋማት የተጨናነቁ እና ንጽህና የጎደላቸው ነበሩ። ከገንዘብ እጥረት የተነሳ ሆስፒታሎችና የሕፃናት ማሳደጊያ ተቋማት ለወላጅ አልባ ሕፃናት ትኩረት አልሰጡም። በተቋማት ያሉ ሕፃናት በቂ የጤና ክብካቤ አላገኙም።

**<u>ዓለም አቀፍ የሕፃናት ጠለፋ</u>፡-** አገሪቱ የ1972ቱ ዓለም አቀፍ የሕፃናት ጠለፋ የሲቪል ገጽታዎች የሔግ ስምምነት አባል አይደለችም። ኢትዮጵያን በሚመለከት ያለውን ሙሉ መረጃ ለማግኘት ቀጥሎ የተመለከተውን የአሜሪካ የውጭ ጉዳይ መሥሪያ ቤት የድረገፅ አድራሻ ይጠቀሙ፡-travel.state.gov/content/childabduction/english/country/ethiopia.html.

**ፀረ-ሴማዊነት**

የአይሁድ ማኅበረሰብ አባላት ቁጥር በግምት 2000 ነበረ። ፀረ-ሴማዊ የሆኑ ድርጊቶች መፈፀማቸውን የሚዘግቡ ሪፖርቶች አልነበሩም።

## ሕገ-ወጥ የሰዎች ዝውውር

የአሜሪካ የውጭ ጉዳይ መሥሪያ ቤት የሚያወጣውን ሕገ-ወጥ የሰዎች ዝውውር ሪፖርት በwww.state.gov/j/tip ድረ-ገጽ ላይ ይመልከቱ።

## አካል ጉዳተኞች

ሕገ መንግሥቱ ለአካል ጉዳተኞች እኩል መብት አይሰጥም። የአካልና የአእምሮ ጉዳተኞች በሥራ ቅጥር ወቅትና ህንፃዎችን ተደራሽ በማድረግ ረገድ መድልዎ እንዳይደረግባቸው ሕጉ ይከለክላል። መስማት ለተሳናቸው ሰዎች መኪና ማሽከርከር በሕግ የተከለከለ ነው።

በቅጥር ወቅት አካል ጉዳትን መሠረት ያደረገ መድልዎ እንዳይፈጸም ሕጉ ይከለክላል። በተጨማሪም ቀጣሪ መሥሪያ ቤቶች ለአካል ጉዳተኞቸ አስፈላጊ የሥራ ወይም የሥልጠና ሁኔታዎችን ማመቻቸት እንደሚገባቸው ይደነግጋል። በሴት የአካል ጉዳተኞች ላይ ያለውን ተጨማሪ ጫናም ሕጉ ከግምት አስገብቷል። መንግሥት ሕጉን ለማስፈጸም የወሰዳቸው እርምጃዎች ውስን ነበሩ። ለምሳሌ ያህል መስማት ለተሳናቸው የመንግሥት ሠራተኞች አስተርጓሚዎችን መድቧል። (ክፍል 7 "መ" ን ይመልከቱ)።

ምንም እንኳ የህንፃዎችን የተደራሽነት ደረጃ የተመለከቱ ዝርዝር ደንቦች ባይወጡም፣ የሚገነቡ ህንፃዎች እና የመፀዳጃ ክፍሎች ለአካል ጉዳተኞች ተስማሚ በሆነ መልኩ እንዲገነቡ ሕጉ ደንግጓል። ይሁን እንጂ ህንፃዎችና የመጸዳጃ ክፍሎች በአብዛኛው ለአካል ጉዳተኞች ተደራሽ አልነበሩም። የቤት አከራዮች አካል ጉዳተኞች የመጀመሪያ ወለል ላይ እንዲከራዩ ማስመረጥ ይጠበቅባቸዋል። ይህም ተግባራዊ ሆኗል።

በትምህርትና በሥራ ቅጥር ሴት የአካል ጉዳተኞች ከወንዶቹ የበለጠ ተጎጂዎች ነበሩ። "ፖፑሌሽን ካውንስል ያንግ አዳልትስ" (Population Council Young Adult Survey) በ2002 በወጣቶች ላይ ባደረገው ጥናት የወጣት አካል ጉዳተኞች የትምህርት ተሳትፎ የአካል ጉዳት ከሌለባቸው ወጣቶች ዝቅተኛ እንደነበር አመልክቷል። በጥናቱ መሠረት የአካል ጉዳተኛ ወጣት ሴቶች የትምህርት ተሳታትፎ ከወንድ አካል ጉዳተኞች ተሳትፎ ያነሰ ነበር። የአካል ጉዳት ካለባቸው ወጣት ሴቶች መካከል 23 በመቶ የሚሆኑት ትምርት ቤት ገብተዋል። በሌላ በኩል የአካል ጉዳት ከሌለባቸው ወጣት ሴቶች መካከል 48 በመቶ እንዲሁም ከወንዶች 55 በመቶ ትምህርት ቤት ገብተዋል። በጥቅል ሲታይ ጥናቱ ካካተታቸው የአካል ጉዳተኛ ወጣቶች

መካከል 47.8 በመቶ በአካል ጉዳት ሳቢያ ትምህርት ቤት መግባት እንዳልቻሉ ተናግረዋል። የአካል ጉዳተኛ ወጣት ሴቶች የአካል ጉዳት ከሌለባቸው ወጣት ሴቶች ይበልጥ ለአካላዊና ወሲባዊ ጥቃት ተጋልጠው ነበር። ወሲብ ከፈጸሙ የአካል ጉዳተኛ ወጣት ሴቶች መካከል 33 በመቶ ያህሉ የግዳጅ ወሲብ እንደተፈጸመባቸው ተናግረዋል። በተመሳሳይ ጥናትመሠረትከወንድ የአካል ጉዳተኞች መካከል 6 በመቶ ያህሉ ጥናቱ ከመደረጉ ሶስት ወራት በፊት ባለው ጊዜ ድብደባ ተፈጽሞባቸዋል። በአንጻሩ ጥናቱ ካካተታቸው የአካል ጉዳት ከሌለባቸው ወጣቶች መካከል 2 በመቶ ያህሉ ድብደባ ተፈጽሞባቸዋል።

መስማትና ማየት ለተሳናቸው አካል ጉዳተኞች የተቋቋሙ በርካታ ትምህርት ቤቶች፣ እንዲሁም የአእምሮ ዕድገት ውሱንነት ችግር ላለባቸው ሕፃናትና ወጣቶች የሥልጠና ማዕከላት ተዘጋጅተዋል። ከዘጠኙ የክልል መንግሥታት በአምስቱ ሰው ሰራሽ የአካል ጉዳተኞች መርጃ መሳሪያዎች ማምረቻ ማዕከላት ነበሩ።

የሠራተኛ እና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ከአካል ጉዳተኝነት ጋር ተያይዘው በሚነሱ ችግሮች ላይ ያተኮሩ ተግባራትን አከናውኗል። እንደሌሎች ሲቪክ ማህበራት ሁሉ ብሔራዊ ማየት የተሳናቸው ማህበር፣ ብሔራዊ መስማት የተሳናቸው ማኅበር እና ብሔራዊ የአካል ጉዳተኞች ማኅበር በበጎ አድራጎት ድርጅቶች እና ማኅበራት አዋጅ ምክንያት አሉታዊ ተጽዕኖ ደርሶባቸዋል።

**ብሔር/ዘር/ አናሳ ጎሳዎች**

በአገሪቱ ከ80 በላይ ብሔሮች/ብሔረሰቦች አሉ። ከጠቅላላው ህዝብ ወደ 35 በመቶ የሚሆነውና ከፍተኛውን ቁጥር የያዘው የኦሮሞ ብሔረሰብ ነው። የፌደራል ሥርዓቱ ድንበሮችን የዋና ዋና ብሔረሰቦችን አሰፋፈር መሠረት በማድረግ የለየ ነው። አብዛኛዎቹ የፖለቲካ ፓርቲዎች በዋናነት ብሔረሰብን መሠረት ያደረጉ ነበሩ።

በዓመቱ ውስጥ በብሔረሰቦች መካከል የተነሱ ግጭቶች ጉዳት እና ሞት አስከትለዋል። ለምሳሌ በ2006 ዓ.ም. በሚያዝያ መገባደጃ እና በግንቦት ወር መባቻ፤የአዲስ አበባ ከተማ ተስፋፍቶ በዙሪያው የሚገኙ የኦሮሚያ ክልል ከተሞችን ያጠቃልላል በሚል የወጣውን የተቀናጀ የጋራ ልማት የተሰኘ መርሀ ግብር በመቃወም በመላው ኦሮሚያ የሚገኙ ዩኒቨርስቲዎች የተቃውሞ ሰልፎች ተካሂደዋል። ሚያዝያ 22 ቀን 2006 ዓ.ም. በአምቦ በተካሄደው ሰላማዊ የተማሪዎች የተቃውሞ ሰልፍ ወደ ሁከት ተለውጦ ቢያንስ ስምንት ሰዎች ለሞት ተዳርገዋል። ሂዩማን

ራይትስ ዋች የዐይን እማኞችን ጠቅሶ እንደዘገበው "የመንግሥት የፀጥታ ኃይሎች በሰላማዊ ሰልፉ ተሳታፊዎች ላይ ጥይት ተኩሰዋል።"

በምዕራብ የአገሪቱ ክፍል በሚገኘው የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል ባለሥልጣናት 8,000 የሚሆኑ በክልሉ ነዋሪ የሆኑ የአማራ ተወላጆችን ከቤታቸው አፈናቅለዋል። ከተፈናቃዮች አንዳንዶቹ በብሔራቸው ምክንያት የፖሊስ ድብደባ እና ዛቻ እንደደረሰባቸው ተናግረዋል። የክልሉ ፕሬዚደንት የማፈናቀል እርምጃው ስህተት እንደሆነ በይፋ ገልጸው ተፈናቃዮቹ እንዲመለሱ ጥሪ አድርገዋል። የክልሉ መንግሥት ባለስልጣናትም እንዲሁ ተፈናቃዮቹ ለወደመባቸው ንብረት እና ለደረሰባቸው ጉዳት ካሳ እንደሚከፈል ገልጸዋል። ባለሥልጣናት በማፈናቀሉ ሂደት ተሳትፎ ነበራቸው የኗቸውን በርካታ የአካባቢ አስተዳደር ባለሥልጣናት ከመንግሥት ኃላፊነት ያነሷቸው ሲሆን፤ ከነዚህም በአንዳንዶቹ ላይ የወንጀል ክስ መስርተውባቸዋል።

## ማኅበረሰባዊ በደሎች፣ መድልዎ፣ እና ጾታዊ ማንነትን እና ወሲባዊ ዝንባሌን መሠረት ያደረጉ ጥቃቶች

በአገሪቱ ሕግ መሠረት በፈቃደኝነት የሚፈፀም የተመሳሳይ ጾታ ግንኙነት ሕገ-ወጥና ከሦስት እስከ 15 ዓመት እስራት የሚያስቀጣ ወንጀል ነው። የተመሳሳይ ጾታ ዝንባሌ ባላቸው ግለሰቦች ላይ መድልዎ እንዳይፈጸም የሚከለክል ሕግ የለም። እንዲህ ዓይነት ዝንባሌ ባላቸው ወንዶች እና ሴቶች ላይ ጥቃቶች መፈፀማቸውን የሚገልጹ አንዳንድ ሪፖርቶች ነበሩ። ሆኖም እነዚህን ጥቃቶች ከፍርሃት የተነሳ ወይም በቀል፣ መድልዎና መገለል ይደርስብናል በሚል ስጋት በተጎጂዎች የቀረቡ ሪፖርቶች ውስን ነበሩ። የጥላቻ ወንጀልን የሚመለከቱ ሕግጋት ወይም የተመሳሳይ ጾታ ዝንባሌ ባላቸው ግለሰቦች ላይ ጥቃቶች ሲፈጸሙ አስፈላጊውን ዕርዳታ ለማድረግ የሚያስችል በወንጀል ፍትህ አስተዳደር ውሰጥ ያለ አሠራር የለም። በተመሳሳይ ፆታ መካከል የሚደረግ የወሲብ ግንኙነት በሀገሪቱ ህገ-ወጥ በመሆኑና ሊደርስባቸው የሚችለውን የከፋ ማሕበራዊ መገለል በማሰብ መሰል ወሲባዊ ዝንባሌ ያላቸው ራሳቸውን ይፋ አያደርጉም። የተመሳሳይ ጾታ ግንኙነት የሚፈጽሙ ማኅበረሰብ አባላት መብት ተሟጋቾች ክትትል እንደሚደረግባቸው እና አልፎ አልፎም ለደህንነታቸው እንደሚሰጉ ተናግረዋል።

አዲስ አበባ የሚገኘው የኤድስ መረጃ ማዕከል የተመሳሳይ ጾታ ዝንባሌ ያላቸው ሴቶችና በርካታ ወንዶች ማንነታቸውን በመግለጽ የሚደርስባቸውን መገለል ለመሸሽ እንዴት

ባህሪያቸውን መቀየር እንደሚችሉ ምክር በመሻት ስልክ ይደወሉ እንደነበር ሪፖርት አድርጓል። በርካታ የተመሳሳይ ጾታ ዝንባሌ ያላቸው ወንዶች ስጋት፣ ግራ መጋባት፣ የማነነት ቀውስ፣ ድብርት፣ ራስን ማግለል፣ የሃይማኖት ግጭት እና ራስን ለማጥፋት የመሞከር ስሜት እንደተሰማቸው ተናግረዋል።

**በኤች.አይ.ቪና ኤድስ ታማሚዎች ላይ የሚደርስ ማኅበራዊ መድሎ**

ኤች.አይ.ቪ/ኤድስ በደማቸው ያለ ወይም በበሽታው የተጎዱ ዜጎች በትምህርት፣ በሥራ እንዲሁም በማህበራዊ ኑሮ የሚደርስባቸው መድልዎ እና መገለል ቀጥሏል። እነዚህ ግለሰቦች አገልግሎት ለማግኘት መቸገራቸውን ተናግረዋል። ይህን በተመለከተ የተለያዩ መረጃዎች ቢኖሩም የችግሩን ስፋት የሚያሳይ ስታቲስቲካዊ መረጃ አልተገኘም።

## ክፍል 7. የሠራተኛ መብቶች

### ሀ. የመደራጀት ነፃነት እና በኅብረት የመደራደር መብት

ሠራተኞች በሠራተኛ ማህበራት እንዲደራጁ፣በማህበራት እንዲታቀፉ፣ህጋዊ የሥራ ማቆም አድማ እንዲያደርጉ፣ በኅብረት እንዲደራደሩ ሕገ-መንግስቱም ሆነ ሕጉ ይፈቅዳል። እነዚህ መብቶች አገሪቱ ባወጣቻቸው ሌሎች ሕግጋት ምክንያት ተግባራዊ እንዳይሆኑ ተገድበዋል። ሕጉ በተለይ በሥራ አስኪያጅ ደረጃ ያሉ ተቀጣሪዎች፣ መምህራን፣ የጤና ክብካቤ ሠራተኞች፣ ዳኞች፣ ጠበቆች እና የደህንነት አገልግሎት ሠራተኞችን ጨምሮ የመንግሥት ሠራተኞች ማህበር እንዲያቋቁሙ አይፈቅድላቸውም። የቤት ሠራተኞች፣ ጊዜያዊ ተቀጣሪዎች፣ እና የትርፍ ጊዜ የግብርና ሠራተኞችም እንዲሁ ማህበር እንዲያቋቁሙ ሕጉ አይፈቅድላቸውም።

የሠራተኛ ማኅበር ለመመሥረት ቢያንስ አሥር አባላት ያስፈልጋሉ። ምንም እንኳ ሁሉም ማህበራት የመመዝገበ መብት እንዳላቸው ሕጉ ቢደነግግም፤ መንግሥት ያስቀመጣቸውን መስፈርቶች ያላሟሉ ማህበራትን ላይመዘግብ ይችላል። ሠራተኞች በቅጥራቸው ከአንድ በላይ የሠራተኛ ማኅበር አባል እንዲሆኑ አይፈቀድም። አንድ የሠራተኛ ማኅበር ግልጽ በሆነ ሁኔታ የፖለቲካ እንቅስቃሴ ማራመድ እንደሌለበት ህጉ ይደነግጋል። የአስተዳደር ኃላፊዎች አንድ የሠራተኛ ማህበር ፖለቲካን በመሰሉ የተከለከሉ ተግባራት መሳተፉን ጠቅሰው ምዝገባው

እንዲሰረዝ ለፍርድ ቤት እንዲያመለክቱ ሕጉ ይፈቅዳል፡፡ አሠሪዎች በሠራተኛ ማኅበራት ላይ መድልዎ እንዳይፈጽሙና በሠራተኛ ማህበር ውስጥ በመሳተፉ ምክንያት የተባረረ ሠራተኛ ቢኖር ወደ ሥራው እንዲመለስ ሕጉ የሚያስገድድ ቢሆንም፤ ቀጣሪው ወይም አሠሪው ራሱ የሚቆጣጠረው የሠራተኛ ማህበር እንዳያቋቁም ወይም ድጋፍ እንዳያደርግ ሕጉ አይከለክልም፡፡

ግልጽ በሆነ ሁኔታ የሠራተኞችን በነጻነት የመደራጀት መብት የሚገድቡ ወይም የመገደብ አቅም ያላቸው ሌሎች ሕግጋትና ደንቦች፤ የበጎ አድራጎትና ሲቪክ ማኅበራት አዋጅ፣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 168/2001 (የበጎ አድራጎትና ሲቪክ ማኅበራት አዋጅን ለማጠናከር የወጣ) እንዲሁም አዋጅ ቁጥር 652/2001 (የጸረ-ሽብርተኝነት ሕግ) ናቸው፡፡ በዓለም አቀፉ የሥራ ድርጅት የ"ኮንቬንሽኖች" እና ምክረ-ሃሳቦች ትግበራ ኮሚቴ የበጎ አድራጎት እና ማህበራት አዋጁ መንግሥት በሠራተኞች የመደራጀት፣ የመመዝገብ፣ የውስጥ አስተዳደርና ማኅበርን የማፍረስ ጉዳዮች ውስጥ ጣልቃ እንዲገባ ሥልጣን ይሰጣል ሲል ገልጧል፡፡ የጸረ-ሽብርተኝነት አዋጁም እንዲሁ በሰላማዊ መንገድ ሃሳብን የመግለጽ ነጻነትንና የመደራጀት መብታቸውን በተግባር ለሚያውሉ የመቅጫ መሳሪያ ሊሆን እንደሚችል ተመልክቷል፡፡

የኅብረት ድርድር መብት እንዲከበር ሕጉ ጥበቃ ቢያድርግም፤ ይህ መብት በከፍተኛ ደረጃ ተገድቦ ነበር፡፡ የኅብረት ስምምነትን ለማሻሻል ወይም በአዲስ ለመተካት የሚደረግ ድርድር ስምምነቱ ከማብቃቱ ከ3 ወራት በፊት ሊጠናቀቅ ይገባል፡፡ ይህ ካልሆነ የደመወዝና የጥቅማ ጥቅም ህጉ ተግባራዊ ሊሆን አይችልም፡፡ የመንግሥት ትምህርት ቤት መምህራንን ጨምሮ የመንግሥት ሠራተኞች የሙያ ማኅበራትን መመሥረት፣ እንዲሁም አባል መሆን ይችላሉ፤ ነገር ግን ለተሻለ ክፍያና የሥራ ሁኔታ መደራደር አይችሉም፡፡ በተጨማሪም የመንግሥት ዘርፍ የአሠሪና ሠራተኛ ግጭት የእርቅ አፈጻጸም በግሉ ዘርፍ ካለው የበለጠ ገዳቢ ነው፡፡ ሕጉ በሠራተኞችም ሆነ በአሠሪዎች የውስጥ አደረጃጀት፣ አሠራርና አስተዳደር ጉዳዮች ጣልቃገብነት በቂ ከለላ አያደርግም፡፡

ሠራተኞች መብታቸውን ለማስጠበቅ የሥራ ማቆም አድማ ማድረግ እንደሚችሉ በሕገ መንግሥቱና በሕግ የተደነገገ ቢሆንም፤ የሥራ ማቆም አድማ ማድረግን አስቸጋሪ የሚያደርጉ ውስብስብና ጊዜ ወሳጅ ሥነ-ሥርዓቶች አሉ፡፡ ጉዳት የደረሰባቸው ሠራተኞች የሥራ ማቆም አድማ ከማድረጋቸው በፊት ከቀጣሪው መሥሪያ ቤት ጋር በድርድር ጉዳዩን በእርቅ እንዲፈቱ ሕጉ ይጠይቃል፡፡ ሆኖም እነዚህ ድንጋጌዎች ቀጣሪው ድርጅት ሠራተኛውን ከሥራው እንዲያግድ መብት ይሰጡታል፡፡ የሥራ ማቆም አድማ ለማድረግ የሠራተኛውን 2/3ኛ ድጋፍ

ማግኘት ያስፈልጋል። ጉዳዩ ወደ ፍርድ ቤት ወይም የሠራተኛ ማህበርን ለሚመለከት ቦርድ ካልቀረበ ሠራተኛው ከላይ የተጠቀሱትን አማራጮች ሳይከተል የሥራ ማቆም አድማ የማድረግ መብት አለው። ይህ የሚሆነው ግን ቢያንስ ከአስር ቀናት በፊት ለሌላኛው ወገንና ለሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ሲያሳውቅ እንዲሁም ጉዳዩን በድርድር ለመፍታት ጥረት ሲያደርግ ነው።

በአየር ትራንስፖርት፣ በከተማ አውቶቡስ፣ በኤሌክትሪክ ኃይል አቅርቦት፣ በነዳጅ ማደያ፣ በሆስፒታልና መድሃኒት ቤቶች፣ በእሳት አደጋ መቆጣጠሪያ፣ በቴሌኮሙኒኬሽን እና በከተማ ጽዳት በመሳሰሉት እጅግ ጠቃሚ ማህበራዊ አገልግሎት በሚሰጡ ተቋማት የሚሠሩ ሠራተኞች የሥራ ማቆም አድማ ማድረግ እንደማይችሉ በሕግ ተደንግጓል። ነገር ግን እነዚህ ከላይ የተዘረዘሩት የሥራ ዘርፎች በዓለም አቀፉ የሥራ ድርጅት ጠቃሚ ማህበራዊ አገልግሎቶች ተብለው ከተቀመጡት በቁጥር ይበዛሉ። አድማ ባደረጉ ሠራተኞች ላይ የሚደረግ የበቀል እርምጃን ሕጉ ይከለክላል። ሆኖም ግን በህገወጥ የሥራ ማቆም አድማ ላይ የሚሳተፉ ማኅበራትና ሠራተኞች በፍትሐ ብሔር ወይም በወንጀለኛ ህግ ሊጠየቁ እንደሚችሉ ሕጉ ይደነግጋል። እጅግ ጠቃሚ ማኅበራዊ አገልግሎት በሚሰጡ ዘርፎች ውስጥ የሚሰሩ ሠራተኞች የሥራ ማቆም አድማ እንዲያደርጉ ያስተባበሩ የሠራተኛ ማኅበራት እንዲፈርሱ ሊወሰን ይችላል።

የቤት ሠራተኞችን ጨምሮ መደበኛ ባልሆነው የሥራ ዘርፍ የተሰማሩ ሠራተኞች በአሠሪና ሠራተኛ ሕግ መሠረት በማኅበር ሊደራጁ አይችሉም። በዓመቱ መንግሥት ባጋጠመው የሰው ኃይል እጥረት ሳቢያ ሕግጋትን በሚፈለገው ደረጃ ተፈጻሚ ማድረግ አልቻለም። የክስ ሂደቶችም መዘግየትና ይግባኝ የበዛባቸው ነበሩ።

የመደራጀትና በኅብረት የመደራደር መብቶች አልተከበሩም። ምንም እንኳ መንግሥት ማህበራት እንዲደራጁ የፈቀደ ቢሆንም፤ ዋነኞቹ የሠራተኛ ማኅበራት በመንግሥት የተቋቋሙና በራሱ ቁጥጥር ሥር የሚገኙ ነበሩ። መንግሥት ላለፉት አራት በላይ ዓመታት እንዳደረገው ሁሉ፤ ብሔራዊ የመምህራን ማህበር ያቀረበውን የምዝገባ ጥያቄ ተመሳሳይ ማኅበር መኖሩን እንደምክንያት በማቅረብ ጥያቄውን ውድቅ ማድረጉን ቀጥሏል። ከዚህ ሌላ መምህራን ማህበር ያቀረበው የምዝገባ ማመልከቻ የበጎ አድራጎትና ሲቪክ ማሕበራት አዋጅንመሠረትያላደረገ መሆኑ ተጠቅሷል።በ2003 ዓ.ም ኤጁኬሽን ኢንተርናሽናል ለዓለም አቀፍ የሥራ ድርጅት ባቀረበው ሪፖርት መንግሥት በብሔራዊ የመምህራን ማህበር አባላት ላይ በሚያደርገው

ክትትልና ወከባ አባላቱ ለዘመናት የቆሙለትን ነጻ ማህበር የማቋቋም ዓላማ እንዲተው እንዳስገደዳቸው ገልጿል። በመጋቢት 2004 ዓ.ም. በዓለም አቀፉ የሥራ ድርጅት የመደራጀት ነጻነት ኮሚቴ በብሔራዊ መምህራን ማህበር ላይ የሚፈጸመው የመደራጀት መብት ጥሰት፣ በማህበሩ የውስጥ ጉዳዮች ጣልቃ መግባት፣ ማስፈራራት፣ ሠራተኞችን ከሥራ ማባረርና እንዲሁም አባላትን ማሰር እና ማዋከብ እንዳሳሰበው አመልክቷል። በመጋቢት ወር 2005 ዓ.ም. የዓለም አቀፉ የሥራ ድርጅት ልዑካን ቡድን በኢትዮጵያ የሥራ ጉብኝት ባደረገበት ወቅት መንግሥት ብሔራዊ የመምህራን ማኅበርን በሲቪክ ማኅበራት አዋጅ አማካይነት እንደሚመዘግበው ከሥራና ማኅበራዊ ጉዳዮች ሚኒስቴር ጋር ጋር የጋራ መግባባት ላይ መድረሳቸውንና በመንግሥት በኩል ቀርጠኝነትና ዝግጁነት መታየቱን ገልጿል። ኮሚቴው መንግሥት ያለ አንዳች ተጨማሪ መዘግየት ብሔራዊ የመምህራን ማኅበሩ እንዲቋቋም መነትጎቱን የቀጠለ ሲሆን፤የመንግሥት ሠራተኞች መብታቸው ተከብሮ የፈለጉትን ማኅበር መመሥረትና መቀላቀል የሚያስችላቸው የሲቪል ሰርቪስ ሪፎርም እንዲያካሂድም ጥሪ አቅርቧል። በዓመቱ የዓለም አቀፉ የሥራ ድርጅት የባለሙያዎች ኮሚቴ መንግሥት ብሔራዊ የመምህራን ማኅበርን በሲቪክ ማኅበራት አዋጅ መሠረት ለመመዝገብ "ዝግጁና ቁርጠኛ" እንደነበር ገልጿል።

ምንም እንኳን ዜጎች በኅብረት የመደራደር መብትን በነፃነት እንዲተገብሩ መንግሥት የፈቀደ ቢሆንም፤ ተወካዮች የክፍያ ድርድር የሚያደርጉት በተቋም ደረጃ ብቻ ነበር። ቀጣሪዎች በአብዛኛው ለመደራደር ፈቃደኛ አልነበሩም። በመደበኛ የኢንዱስትሪ ዘርፍ ያሉ የሠራተኛ ማኅበራት የአሠሪና ሠራተኛ ህግን ሥራ ላይ ለማዋል የተወሰነ ጥረት አድርገዋል።

ሕጉ በማህበራት ውስጥ የሚንቀሳቀሱ ሠራተኞች መገለል እንዳይደርስባቸው የሚከለክል ቢሆንም፤ ቀጣሪዎች በሠራተኛ ማኅበር ውስጥ በንቃት የሚንቀሳቀሱ ሠራተኞችን ከሥራ እንደሚያባርሯቸው ማህበራቱ ሪፖርት አድርገዋል። ቻይናውያን አሠሪዎች በአጠቃላይ ሠራተኞች ማኅበር እንዲያቋቁሙ አልፈቀዱም። አልፎ አልፎም የሠራተኛ ማኅበር መሪዎችን አዛውረዋል፣ ከሥራ አባርረዋል እንዲሁም የማኅበራት መሪዎችን በማስፈራራት ወይንም አባላት ከማኅበሩ እንዲወጡ ጫና አድርገዋል የሚሉ ሪፖርቶች ቀርበዋል። ሠራተኞች አለአግባብ ከሥራ መባረራቸውን በመግለጽ በፍርድ ቤት የሚመሰርቱት ክስ ፍርድ ቤቶች ባለባቸው የሥራ ጫና የተነሳ ጉዳዮቻቸው እልባት የሚያገኙት ከዓመታት በኋላ ነበር።

በሠራተኛ ማኅበራት ውስጥ የሚንቀሳቀሱ ሠራተኞችን ያላግባብ ከሥራ ያባረሩ ቀጣሪዎች ሠራተኞቹን ወደ ሥራ ገበታቸው እንዲመልሷቸው የታዘዙ ሲሆን፤ በተግባርም ሠራተኞቹን ወደሥራ መልሰዋል። የሥራ ማቆም አድማ አድራጊዎች ላይ የሚወሰደውን የበቀል እርምጃ ህግ ቢከለክልም፣ አብዛኛዎቹ ሠራተኞች መንግሥት ይህን ከለላ ተግባራዊ ያደርጋል የሚል እምነት አልነበራቸውም። በሀገሪቱ ካለው ከፍተኛ የሥራ አጥነት ችግርና በፍርድ ቤት የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳዮች የሚወስዱትን ረጅም ጊዜ ከግምት በማስገባት አንዳንድ ሠራተኞች በሥራ ማቆም አድማዎች ወይም በሌሎች የሠራተኛ አድማዎች ላይ ለመሳተፍ እንደሚፈሩ የሠራተኛ ማህበራት ኃላፊዎች ተናግረዋል። ጸረ-ማህበር እንቅስቃሴዎች የነበሩ ቢሆንም፤ ሪፖርት የተደረጉት አልፎ አልፎ ነበር።

## ለ. የግዳጅ ሥራ ክልከላ

በሕፃናት ላይ የሚፈጸም የግዳጅ ሥራን ጨምሮ ሌሎች የግዳጅ ሥራዎችን ሕጉ ይከለክላል። ነገር ግን ፍርድ ቤቶች የግዳጅ ሥራን እንደ ቅጣት እርምጃ እንዲወስዱ ይፈቅዳል። የግዳጅ ሥራ ክልከላን መንግሥት በበቂ ሁኔታ ተፈፃሚ አላደረገም። የግዳጅ ሥራ በተግባር ተፈጽሟል። አዋቂዎችና ሕፃናት በጎዳና ላይ ንግድ፣ በልመና፣ በሽመና ሥራ ወይም በግብርና ሥራ በግድ እንዲሠማሩ ተደርገዋል። ከዚህ ሌላ ሕፃናት በግዳጅ የቤት ውስጥ ሠራተኛ ሆነው እንዲሠሩ ተደርገዋል። በተለይ በገጠር አካባቢዎች ሰዎች ለተበደሩት ገንዘብ ምትክ በግዳጅ የሽመናና የሸክላ ሥራዎችን በመሥራት፣ በእረኝነት፣ እንዲሁም ሌሎች የግብርና ሥራዎችን በማከናወን ለአበዳሪዎች የሚሰሩበት ሁኔታ ተስተውሏል።

የአሜሪካ የውጭ ጉዳይ መሥሪያ ቤት በሕገ-ወጥ የሰዎች ዝውውር ላይ ያወጣውን ሪፖርት በwww.state.gov/j/tip ላይ ይመልከቱ።

## ሐ. የሕፃናት ጉልበት ብዝበዛና የሥራ ቅጥር ዝቅተኛ ዕድሜ

ለቀን ሥራ ወይም ደመወዝ ለሚከፈልበት ሥራ የቅጥር ዝቅተኛ (የመነሻ) ዕድሜ 14 ዓመት እንደሆነ በሕግ ተደንግጓል። ይህ ዝቅተኛ የመነሻ ዕድሜ ግን በራሳቸው የተቀጠሩ ሕፃናት ወይም ያለክፍያ በሚሠሩ ሕጻናት ላይ ተፈፃሚነት የለውም። ዕድሜያቸው ከ14 እስከ 18

ዓመት የሆኑ ታዳጊዎች አደገኛ በሆኑ እና ሌሊት መሥራት በሚጠይቁ ሥራዎች ላይ መሰማራት እንደሌለባቸው የሚደነግጉ ሕግጋት አሉ፡፡ አደገኛ ሥራዎች ተብለው በህጉ የተዘረዘሩት በማሽኖች የሚከናወኑ የፋብሪካ ሥራዎች ወይም የሕፃናትን ጤና አደጋ ላይ የሚጥሉ ማናቸውም ሥራዎች ናቸው፡፡ ከተከለከሉ የሥራ ዘርፎች መካከል የመንገደኞች ትራንስፖርት፣ የኤሌክትሪክ ኃይል ማመንጫዎች፣ የከርሰምደር ሥራዎች፣ የመንገድ ጽዳት እና ሌሎች ዘርፎች ይገኛሉ፡፡ ከ16 ዓመት በታች የሆኑና በሙያ ት/ቤት በመማር ላይ ያሉ ወጣቶች አደገኛ በሚባሉ ሥራዎች ላይ እንዳይሰማሩ በመከልከሉ የተነሳ፤ የሕግ ጥበቃ እንደማይደረግላቸው ሕጉ በግልጽ ደንግጓል፡፡ በ14 እና በ18 ዓመት የዕድሜ ክልል ውስጥ ያሉ ልጆች በቀን ከሰባት ሰዓታት በላይ እንዳይሠሩ እንዲሁም ከምሽቱ 4 ሰዓት እስከ ንጋቱ 12 ሰዓት፣ በህዝብ በዓላት፣ በእረፍት ቀናት ወይም የትርፍ ሰዓት ሥራዎችን መሥራት እንደሌለባቸው ህጉ ይደነግጋል፡፡

መንግሥት ተቆጣጣሪ ባለሙያዎች የሌሉት በመሆኑ ሕጉን በአግባቡ ተግባራዊ አላደረገም፡፡ ትግበራቸውን ለመከታተል የተመደበው በጀት ውስን ከመሆኑም በላይ በአግባቡ ባለመተግበራቸው የተጣሉ ቅጣቶች እጅግ በጣም ውስን ነበሩ፡፡ ምንም እንኳ የጎንደር ዩንቨርሲቲ በ2003 የሥራ ኢንስፔክተሮች ስልጠና የጀመረ ቢሆንም፤ በአገሪቱ ያለው የተቆጣጣሪዎች ቁጥር አነስተኛ በመሆኑ ምክንያት የሥራ ቦታ ደህንነት እና ጤና ነክ ጥንቃቄዎችን በአግባቡ ማስፈጸም አልተቻለም፡፡ ይህም እንደ ግንባታው ዘርፍ ባሉ የተከለከሉ ዘርፎች የሚሰሩ ህጻናት ቁጥር እንዲጨምር አድርጓል፡፡አስከፊ የሕጻናት ጉልበት ብዝበዛን ለማስቆም አገር አቀፍ የድርጊት መርሀ ግብር በ2004 ዓ.ም. መጨረሻ ላይ ተፈርሞ ነበር፡፡

የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ነጻ ቢሆንም፤ ግዴታ ባለመሆኑ በተለይ በገጠር አካባቢዎች የትምህርት ተሳትፎ ዝቅተኛ ነበር፡፡ ትምህርት ቤት የመግባትን አስፈላጊነትን ለማስገንዘብ በመንግሥትና መንግሥታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች ቅንጅት ሕፃናት በስፋት በእርሻ ሥራ በተሰማሩባቸው አካባቢዎች ማህበረሰብን ማዕከል ያደረጉ የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራዎች ተከናውነዋል፡፡ በዓመቱ መንግሥት በግብርናው ዘርፍ የሕፃናትን ችግር ለመቅረፍ በማሰብ የግብርና ሥራዎችን ዘመናዊ ለማድረግ፣ እንዲሁም ትምህርት ቤቶችን ለመገንባት ጥረት አድርጓል፡፡

የሕፃናት ጉልበት ብዝበዛ ከባድ ችግር ሆኖ ቆይቷል፡፡ በገጠርም ይሁን በከተማ ሕፃናት ሥራ የሚጀምሩት ገና በልጅነታቸው ነበር፡፡ ሕፃናት በተለይ ከእጅ ወደ አፍ በሆነ የእርሻ ሥራ፣ በባሕላዊ ሽመና፣ በዓሳ ማስገር፣ በቤት ውስጥ ሰራተኝነት ተሰማርተው ነበር፡፡ በግንባታ ሥራ ላይ ቁጥራቸው በርካታ የሆነ ሕጻናት ተሰማርተው ነበር፡፡ በገጠር ያሉ ሕፃናት በተለይ ወንዶቹ በእረኝነት፣ በጥቃቅን ንግድ፣ በእርሻ ሥራ፣ በአረም እና በሰብል መሰብሰብ ሥራዎች ተሰማርተው የነበረ ሲሆን፣ ሴት ሕጻናት ደግሞ በማገዶ ለቀማና በውሃ መቅዳት ሥራዎች ተሳትፈዋል፡፡ ሕፃናት በወርቅ ማምረት ተሰማርተው ነበር፡፡ በአነስተኛ የወርቅ ማዕድን ቁፋሮ የሚሰሩ ሕጻናት በራሳቸው ወርቅ ፍለጋ ላይ ተሰማርተው ነበር፤ ብዛት ያለው ውሃ ተሸክመዋል፡፡ ወላጅ አልባ ሕፃናትን ጨምሮ በከተማ ያሉ ልጆች በቤት ውስጥ ሥራዎች ለረጅም ሰዓታት እንዲሰሩ ስለሚደረግ ትምህርታቸውን በአግባቡ ለመከታተል አልቻሉም፡፡ በከተማ ያሉ ሕፃናት በግንባታ፣ በማምረቻ ኢንዱስትሪዎች፣ በጫማ መጥረግ፣ በልብስ ስፌት፣ በሽክም ሥራ፣ በታክሲ ረዳትነት፣ በመኪና ጥበቃ፣ በሕዝብ ማመላለሻዎች እና በጥቃቅን ንግዶች እንዲሁም አልፎ አልፎ በእረኝነት ሥራ ላይ ተሰማርተው ነበር፡፡ አንዳንድ ሕፃናት በጥቂት ክፍያ ወይም ያለክፍያ ወይንም አስተማማኝ የስራ ላይ ደህንነት ጥበቃ በሌለበት አደገኛ አካባቢ ለረዥም ሰዓታት እንዲሰሩ ተደርገዋል፡፡ የጉልበት ሥራ የሚሠሩ ሕፃናት ብዙውን ጊዜ በአሰሪዎቻቸው የአካል፣ የወሲብና የሞራል ጥቃት ደርሶባቸዋል፡፡

*ተጨማሪ መረጃ አስከፊዎቹ የሕፃናት ጉልበት ብዝበዛ ጥናት ግኝቶች የሚለውን የሥራ ሚኒስቴር ሪፖርት ከ*www.dol.gov/ilab/programs/ocft/tda.htm. *ማግኘት ይችላሉ፡፡*

### *መ. ከሥራ ሁኔታ ወይም ከሙያ ጋር ተያያዥ የሆነ መድሎ*

ሕጉ ዘርን፣ ብሔርን፣ ብሔረሰብን፣ ፆታን፣ የጋብቻ ሁኔታን፣ ሃይማኖትን፣ የፖለቲካ አመለካከትን፣ነፍሰጡርነትን፣ የማኅበራዊና የኢኮኖሚያዊ ኑሮ ደረጃን፣ ወይም አካል ጉዳተኝነትን መሠረት ያደረገ መድሎ እንዳይደረግ በጥብቅ ይከለክላል፡፡ አካል ጉዳተኛ የሆኑ ሴቶች ተጨማሪ ጫና እንዳለባቸውም ሕጉ ያሳውቃል (በክፍል 6 ሥር የተቀመጠውን ይመልከቱ)፡፡ ወሲባዊ ዝንባሌ፣ጾታዊ ማንነት፣ እና የኤች አይ ቪ-ኤድስ ታማሚዎች ልዩ ከለላ አልተደረገላቸውም፡፡ መንግሥት ሕጉን ለማስፈፀም የወሰደው እርምጃ ውስን ነው፡፡

ከሥራ ቅጥር እና ከሙያ ጋር በተያያዘ ሴቶች ለመድሎ ተዳርገዋል፡፡ ከወንድ አቻዎቻቸው ጋር ሲነፃፀር ሴቶች አነስተኛ የመቀጠር ዕድል ያላቸው ከመሆኑም በላይ፤ ለተመሳሳይ የሥራ መደብ የሚያገኙት ክፍያም ለወንዶች ከሚከፈለው ያነሰ ነው፡፡

በስደት ላይ ያሉ ሰዎችም በሥራ ላይ መድሎ አጋጥሟቸዋል (በክፍል 7 ሠ ሥር የተቀመጠውን ይመልከቱ)፡፡

## ሠ. ተቀባይነት ያላቸው የሥራ ሁኔታዎች

በሀገር አቀፍ ደረጃ ዝቅተኛ የደመወዝ ክፍያ ተብሎ የተቀመጠ የገንዘብ መጠን የለም፡፡ አንዳንድ የመንግሥት ተቋማትና የልማት ድርጅቶች ግን በራሳቸው ዝቅተኛ የደመወዝ መጠን ወስነዋል፡፡ ትልቁን ቁጥር የያዙት የመንግሥት ሠራተኞች ሲሆኑ፣ ዝቅተኛው የወር ደመወዛቸው 420 ብር (21 የአሜሪካን ዶላር) ነበር፡፡ የመጨረሻው ዝቅተኛ የገቢ መጠን 315 ብር (15.75 የአሜሪካን ዶላር) መሆኑን መረጃዎች ያመለክታሉ፡፡

ከአጠቃላይ የህዝቡ ብዛት አነስተኛ ቁጥር ያለው የወር ደመወዝተኛ ሲሆን፤ የሚኖረውም በከተሞች አካባቢ ነው፡፡ መደበኛ ባልሆነው የሥራ ዘርፍ የሚከፈለው ወርሃዊ ደመወዝ ለሰው ልጅ መሠረታዊ ፍላጎቶችን ለማሟላት ከሚያስፈልገው በታች ነበር፡፡

አንድ ሠራተኛ በሳምንት ውስጥ ቢበዛ ለ48 ሰዓታት መሥራት እንዳለበት፣ እንዲሁም በሳምንት የ24 ሰዓታት እረፍት፣ የትርፍ ጊዜ ክፍያና ከመጠን ያለፈ የትርፍ ሰዓት ሥራ ማሠራትን የሠራተኛ ህጉ ይከለክላል፡፡ በዓመት ውስጥ ደመወዝ የሚከፈልባቸው 13 የህዝብ በዓላት አሉ፡፡ በልማት ድርጅቶችና በመንግሥት የፋይናንስ ተቋማት የሚሠሩ ሠራተኞች የትርፍ ሰዓት ሥራ ክፍያ የማግኘት መብት፣ እንዲሁም የመንግሥት ሠራተኞች ትርፍ ሰዓት የሠሩበትን የማካካሻ ሰዓት የማግኘት መብት እንዳላቸው ተቀምጧል፡፡ መንግሥት፣ ኢንዱስትሪዎችና የሠራተኛ ማኅበራት የሥራ አካባቢ ጤናና ደህንነት መስፈርቶች ላይ ተደራድረዋል፡፡ መሠረታዊ የሠራተኛ ማኅበር እንዲያቋቁሙ ያልተፈቀደላቸው የቤት ሠራተኞች፣ ወቅታዊና ጊዜያዊ የእርሻ ዘርፍ ሠራተኞች የሥራ አካባቢ ጤናና ደህንነት ጥበቃ አላገኙም፡፡

የሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር የቁጥጥር መምሪያ የስራ ላይ ጤናና ደህንነት መስፈርቶች ተግባራዊ መሆናቸውን የመቆጣጠር ኃላፊነት አለበት። በ2005 ዓ.ም. የሥራ ተቆጣጣሪዎች በሀገሪቱ 380 ከነበረበት ወደ 291 ዝቅ ብሏል። እንደሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ይህ ቁጥር ዝቅ ሊል የቻለው በበጀት እጥረትና በሠራተኞች ከሥራ ገበታ መልቀቅ የተነሣ ነው። የሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ባለበት ውሱን የአስተዳደር አቅም፤የመብት ጥሰት አቤቱታዎችን የመቀበል፤ የመመርመርና የመከታተል ድክመት እና ዝርዝር የሆነ የስራ አካባቢ ጤናና ደህንነት ክትትል መመሪያዎች አለመኖር፣ መስፈርቶቹ በተግባር እንዳይውሉ መሰናክል ሆኗል። በተጨማሪም የሚተላለፉት ቅጣቶች ዝቅተኛ በመሆናቸው የመብት ጥሰቱን ሊገቱት አልቻሉም።

ለጊዜያዊ የግብርና ሠራተኞች የሚከፈለው ካሳ፣ ጥቅማጥቅሞችና የሥራ ሁኔታ በሠራተኛ ማኅበር ከታቀፉ ቋሚ የግብርና ሠራተኞች እጅግ ያነሰ ነበር። መንግሥት ሕጉን ተፈጻሚ ለማድረግ ብዙ አልተንቀሳቀሰም። በመደበኛው ዘርፍ የሚሠሩት አብዛኛዎቹ ሠራተኞች በሳምንት 39 ሰዓታት ሠርተዋል። ነገር ግን፣ በርካታ የውጭ ዜጎች፣ ስደተኞች እና መደበኛ ባልሆነ ዘርፍ የሚሰሩ ሠራተኞች በሳምንት ከ48 ሰዓታት በላይ ሠርተዋል።

ምንም እንኳን ሠራተኞች አደገኛ ከሆኑ የሥራ ሁኔታዎች ራሳቸውን በማራቃቸው ምክንያት የቅጥር ኮንትራታቸው መቋረጥ እንደሌለበት ሕጉ ቢደነግግም፤ አብዛኛዎቹ ሠራተኞች ይህን ካደረጉ ከሥራ ልንባረር እንችላለን ብለው ይፈራሉ። የሀገሪቱ የኢኮኖሚ መሠረት በሆነው የግብርና ዘርፍ ውስጥ አደገኛ የሥራ ሁኔታዎች ተስተውለዋል። እንዲሁም በማደግ ላይ ባሉት የግንባታና የኢንዱስትሪ ዘርፎች በተመሳሳይ አደገኛ የሥራ ሁኔታዎች እና የጉልበት ብዝበዛዎች ተስተውለዋል።